# የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ።

ከዮሐንስ ሳንድቬድ ።

መካነ ኢየሱስ ሥነ ጽሑፍ ክፍል ።

አዲስ አበባ ፲፱፻፷፫ ዓ.ም.
በቦሌ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

መጀመሪያ በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. ታተመ ።
ሁለተኛ በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም. ታተመ ።

# ማውጫ ።


ገጽ

መቅድም ። ........................................ 5

ምዕራፍ አንድ ።

ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት .............. 7

ምዕራፍ ሁለት ።

የሐዋርያት ዘመን ቤተ ክርስቲያን.......... 16

፩· በኢየሩሳሌም ።
፪· በሰማርያ ።
፫· ፈሪሳዊው ሳውል ክርስቲያን ሆነ ።
፬· የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ተቋቋመች ።
፭· የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰብ ብኩ በርናባስና ጳውሎስ ተላኩ ።
፮· በኢየሩሳሌም ስለ ተደረገው ጉባዔ።
፯· ጳውሎስ የወንጌል ሥራውን ቀጠለ ።
፰· ጳውሎስ የክርስቶስ እስረኛ ሆኖ እስከ ሮሜ ደረሰ ።

ምዕራፍ ሦስት ።

በሮሜ ክርስቲያኖች ስለ እምነታቸው ተሠዉ። 43
ኔሮ ቄሣር ።

ምዕራፍ አራት ።

በክርስቲያኖችና በአረማውያን መካከል የነበረው ልዩነት እንዴት ነው? ................. 47

ምዕራፍ አምስት ።

ታላላቅ ስደቶችና ሰማዕታት ። ............... 53

፩· በዶሚቲያኑስ ዘመነ መንግሥት ስለ ሆነው ስደት ። Domitian
፪· እግናቲዮስ ። Ignatius
፫· ፖሊካርጵ ። Polycarp
፬· ዩስቲኑስ ። Justin Martyr
፭· ጴርጴቱአ ።
፮· በዴሲዩስ ዘመነ መንግሥት ስለ ሆነው ስደት ።
፯· ዲዮክሌቲያኑስ ያመጣው ከባድ ስደት ።

ምዕራፍ ስድስት ።
ቤተ ክርስቲያንን ያስፋፉ ሁኔታዎች እን
ዴት ያሉ ናቸው? ........................ 72

ምዕራፍ ሰባት ።
በስደት ጊዜ ፈርተው ክርስቶስን የካዱትን
ቤተ ክርስቲያን እንዴት አደረገቻቸው?.. 80

ምዕራፍ ስምንት ።
ለክርስቲያኖች ሙሉ ነጻነት ተሰጣቸው.. 82

ምዕራፍ ዘጠኝ ።
ዩሊያኑስ ከሐዲ ........................ 84

ምዕራፍ አሥር ።
ክርስትና በኢትዮጵያ ስለ መግባቱ ....... 86

ምዕራፍ አሥራ አንድ ።
የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሥርዐትና እም
ነት ። ........................................ 93

ምዕራፍ አሥራ ሁለት ።
የስሕተት ትምህርቶች ። ..................... 100
ሀ፣ የስሕተት ትምህርቶች በሐዋርያት ዘመን ።
ለ፣ የስሕተት ትምህርቶች ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ።

ምዕራፍ አሥራ ሦስት ።
የጥንት ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት መጎ
ለጫዎች ። ................................ 108

ምዕራፍ አሥራ አራት ።
ባሕታውያንና መነኰሳት .................. 113

ምዕራፍ አሥራ አምስት ።
የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች.......... 116
ሀ፣ ኢሬኔዎስ ። ለ፣ ተርቱሊያኑስ ።
ሐ፣ አምብሮሲዩስ ። መ፣ አውግስጢኖስ ።
ሠ፣ የሌሎች መምህራን ታሪክ በአጭሩ ።

ምዕራፍ አሥራ ስድስት ።
መደምደሚያ ። ............................ 13[illegible]

# መቅድም ።

## ስለ መጽሐፉ ይዞታ ።

የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተሰኘችው ይህች አነሥተኛ መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ፩፻ ዓ.ም. ገደማ ያለውን ታሪክ ታወሳለች ።

ቤተ ክርስቲያን በዓለም ውስጥ እንዴት እንደ ተመሠረተች ፣ በሐዋርያትም ዘመን እንዴት እንዳደ ገች ፣ የጥንት ዘመን ክርስቲያኖችም በሃይማኖታቸው ምክንያት እንዴት እንደ ተቸገሩና በስደት መካከል እስከ መጨረሻ እንዴት እንደ ጸኑ በዚህ ታሪክ ተተ ርኰአል ። ይህም ብቻ ሳይሆን ክርስቲያኖች ቢሰደዱም የክርስትና ሃይማኖት አስደናቂ በሆነ ፍጥነት እየተስፋፋ መሄዱን ይተርካሉ ።

ቀጥሎም ክርስትና በኢትዮጵያ የገባው በጥንት ቤተ ክርስቲያን ዘመን ስለ ሆነ ለዚህ ታሪክም የራሱ ምዕ ራፍ ይገኝበታል ።

ስለ ጥንት ቤተ ክርስቲያን መምህራንም አንባቢ ጥናት ለማድረግ እንዲችል የሕይወታቸው ታሪክ በአ ጭሩ ተጽፎ ይገኛል ።

በተለይም የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ለክርስቲያን ሁሉ መምሪያና አብነት እንደ መሆኑ መጠን የዘመናችን ክርስቲያኖች ቢያጠኑት ይጠ ቅማል ። የጥንት ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛ አድርጋ የተቀበለችው ትምህርት ምን ምን እንደሚል ከታሪኩ ጋር ተያይዞ ተጽፎአል ።

ሰው ግን እውነተኛውን ሃይማኖት ይዞ እንዲኖር ከስሕተት የተጠበቀ መሆን አለበት ። ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ የስሕተት መምህራን እየተነሡ ምዕመናንን ያስ ቸግሩ እንደነበር ታሪክ ይናገራል ። ክርስቲያን እውነ ትን ይዞ ከሐሰት እንዲርቅ ይህን ታሪክ ትምህርት አድ ርጎ ሊጠቀምበት ያስፈልገዋል ።

በአጭሩ ፣ ታሪክ እንደ አስተማሪ የሚቆጠር ነው። ስለዚህ ጥናት የምናደርገው ባለፉት ዘመናት የሆነውን ነገር ለማወቅ ብቻ ሳይሆን ትምህርት እንድንቀስም በት ነው ።

ቀላልና አጭር በሆነ አጻጻፍ የተዘጋጀች ይህች መጽሐፍ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለተራ ምዕምናንም ጭምር ይህን የመሰለ ጥቅም እንድትሰጥ ተስፋ በማድረግ ለአንባቢያን አቅርቤአለሁ ።

«የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ ፥ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው ። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው ።»

ዕብ. ፲፫ ፥ ፯—፰ ።

አዋሳ በመጋቢት ወር ፲፱፻፸፭ ዓ. ም.

ዮሐንስ ሳንድቬድ ።

ምዕራፍ አንድ ።

# ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት ።

## ፩ ፤ ማን ነው ?

ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። በክርስቲያኖችም እምነት ጀማሪዋ ከመሆኑም በላይ እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ የቤተ ክርስቲያን ራስና መሪ ሆኖ ይኖራል ።

ማቴዎስ ፥ ማርቆስ ፥ ሉቃስና ዮሐንስ የተባሉት ፥ ወንጌላውያን ተብለው የተሰየሙት አራት ሰዎች የሕይወቱን ታሪክ ጽፈዋል ። ታሪኩን ወረድ ብለን በአጭሩ እንጽፋለን ። አንባቢ በሰፊው ሊያጠናው ቢፈልግ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሊያገኘው ይችላል ።

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ያስተማረውን ትምህርት ለማብራራት ሲሉ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን የጻፉ ሌሎችም አሉ ። እነርሱም የጻፉት ትምህርታዊ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠራቅሞ ይገኛል ። ወደፊት በአጭሩ እናየዋለን ።

በመጀመሪያው የኢየሱስን ትምህርት ተምረው የተቀበሉት ሰዎች መምህራቸውን እውነተኛ ሰው ሆኖ አገኙት ። በብሉይ ኪዳን ዘመን ነቢያት ሁሉ የተናገሩት የትንቢት ቃል በእርሱ ሁኔታ ፍጻሜ ያገኘ ነው የማለት እምነት ስለ ነበራቸው፤—እግዚአብሔር የቀባው ወይም መሢሕ ኢየሱስ ነው እያሉ ያስተምሩ ነበር ። ሰው ከመሆኑም በላይ ግን እውነተኛ አምላክ መሆኑንም እስከ መረዳት ደረሱ ። ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ይሉት ነበር ። ዓለምን ከኃጢአትና ከመከራ ሁሉ ለማዳን ከእግዚአብሔር ተልኮ የመጣ እርሱ ነው እያሉ ይመሰክሩ ነበር ።

ይህን ሁሉ ወደፊት መመልከታችን አይቀርም ። ስለዚህ ለጊዜው እንለፈውና ወንጌላውያን እንደ ጻፉት የኢየሱስን የሕይወቱን ታሪክ እናጥና ።

## ፪ ፡ ልደቱ ።

የሮሜ መንግሥት ቄሣር በግዛቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች በሙሉ ስም ስማቸው ተጽፎ እንዲመዘገቡ ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር ።

በአይሁድ አገር በናዝሬት ከተማ ከዳዊት ቤትና ወገን የሆነ ዮሴፍ የተባለ ሰው ይኖር ነበር ። እርሱም ማርያም የተባለችውን ልጃገረድ አጭቶ ኖሮ እንዲጻፉ ይዞአት ወደ አገሩ ወደ ቤተ ልሔም መጣ ። ማርያምም ከዮሴፍ ጋር ሳትገናኝ በድንግልናዋ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ፀንሳ ነበር ። በቤተ ልሔምም በቆዩበት ወቅት የመውለጃዋ ጊዜ ደርሶ ወንድ ልጅ ወለደች ። ወንጌ ላዊው ሉቃስም እንደ ጻፈው የእግዚአብሔር መልአክ በገለጠላቸው መሠረት ለሕፃኑ ልጅ ኢየሱስ የሚለውን ስም አወጡለት ። ሉቃ. ፪ ። ማቴ. ፩ ።

## ፫ ፡ ልጅነቱ ።

በአገር ውስጥ ንጉሥ ተወልዶአል የሚል ወሬ ተሰማ ። በሮሜ መንግሥትም ሥር የአይሁድን አገር ይገዛ የነበር ሄሮድስ ደነገጠ ። ዙፋኔን እንዳይወርስብኝ በማለት ሕፃኑን ኢየሱስን ሊገድለው ፈለገ ። ከዚህም የተነሣ ዮሴፍ ማርያምንና ሕፃኑን ይዞ ወደ ግብጽ አገር ሸሸ ። ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ ።

ንጉሡ ከሞተ በኋላ ወደ ትውልድ አገሩ ተመልሶ በገሊላ ክፍለ አገር ወደምትገኝ ወደ ናዝሬት ከተማ መጣ ። ከማርያምና ከሕፃኑም ጋር በዚያ ተቀመጠ ።

ስለ ኢየሱስ የልጅነት ታሪክ ብዙ እውቀት የለ ንም ። ይኸውም ስላልተጻፈልን ነው ። ሆኖም ሉቃስ ከጻፈልን ታሪክ እንደምንረዳው ብላቴናው ኢየሱስ በዮሴፍና በማርያም ቤት በሰላም አደገ ። አስተዋይም ልጅ ሆነ ። እግዚአብሔርን የሚፈራ ፣ ለወላጆቹም የሚ ታዘዝ ፣ ቃላቸውንም የሚያከብር ልጅ ነበር ።

የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ በፋሲካ በዓል ወራት በዓሉን ለማክበር ከዮሴፍና ከእናቱ ከማር ያም ጋር ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ ተፈቀደለት ። በዓሉም አልፎ ወደ ቤት ለመመለስ በመንገድ ላይ ሳሉ በመን ገደኞች መካከል ቢያጡት ሊፈልጉት ወደ ኢየሩሳሌም

እንደ ገና ሄዱ ። በቤተ መቅደስም በመምህራን መካከል አገኙት ።

ጥያቄ ሲጠይቃቸው ፥ ለጥያቄአቸውም መልስ ሲሰጥ የሰሙት ሁሉ ከማስተዋሉ የተነሣ ተገረሙ ።

ቢሆንም ገና ልጅ ነውና ከዮሴፍና ከእናቱ ከማርያም ጋር ወደ ቤቱ ወደ ናዝሬት ተመለሰ ። ይታዘዝላቸውም ነበር ። በቁመትም ብቻ ሳይሆን በጥበብም በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር ። ሉቃ. ፪ ።

## ፬ ፤ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ።

የልጅነት ዘመን አልፎ ኢየሱስ በዕድሜ ወጣት ሆነ ። ከወጣትነትም አልፎ ሙሉ ሰው እስከ መሆን ደረሰ ። በእነዚህ ባለፉት ዓመታት ውስጥ የሆነውን ታሪክ ግን ወንጌላውያን አልጻፉልንም። ከዚህም የተነሣ ስለ ኢየሱስ ወጣትነት ፥ እንዲሁም ሙሉ ሰው እስኪሆን ድረስ በናዝሬት ስላሳለፋቸው ዓመታት ብዙ እውቀት የለንም ። ሆኖም በእንጨት ጸራቢው ወይም በአናጢው በዮሴፍ ቤት ውስጥ መቀመጡን እናውቃለን ። ብዙዎች ልጆች ባሉበት ቤት አድጎአል ማለት ነው ። ማቴ. ፲፫ ፥ ፶፭—፶፮ ።

ኢየሱስ በይፋ ለሕዝብ ከመገለጡ በፊት በይሁዳ አገር አንድ ስመ ጥሩ ሰባኪ ተነሥቶ ነበር ። ይኸውም መጥምቁ ዮሐንስ ነው ። በይሁዳ ምድረ በዳ የንስሐን ስብከት ሲሰብክ በብዙ ሺህ የሚቈጠር ሕዝብ ወደ እርሱ ይጎርፍ ነበር ። ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከዮሐንስ ይጠመቁ ነበር ።

ኢየሱስም ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ከሆነው በኋላ ሊጠመቅ ወደ ዮሐንስ መጣ ።

የዮሐንስ ጥምቀት ግን ለኃጢአተኞች የሚሆን ነውና ኢየሱስ በሥራው ከሌላ ሰው ሁሉ የተለየ መሆኑን ስለ ተገነዘበ ሊያጠምቀው አልወደደም ። «እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? አለው ። ኢየሱስ ግን ፦— አሁንስ ፍቀድልኝ ፤ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል» ባለው ጊዜ መጥምቁ ተስማምቶ አጠመቀው ።

ከተጠመቀ በኋላ አይተውት የማያውቁት ነገር ታየ ፤ ተሰምቶም የማይታወቅ ልዩ ነገር ተሰማ ። ወንጌላዊው እንደሚተርከው የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ርግብ በኢየሱስ ላይ ሲወርድ ታየ ። ከሰማያትም ፦ በእርሱ ደስ የሚየለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምፅ መጣ ።

እግዚአብሔር አብ ስለ አንድ ልጁ ሲመሰክር መጥምቁ ዮሐንስ በዚያን ጊዜ ለመስማት በቃ ። ማቴ. ፫ ።

## ፭ ፤ የኢየሱስ ስብከትና ትምህርት ።

ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ ከተጠመቀ በኋላ በሕዝብ መካከል ስብከት ጀመረ ። በከተማ በባላገርም ሰው ከኃጢአቱ እንዲመለስና በወንጌል እንዲያምን ይሰብክ ነበር ። የመጥምቁን የዮሐንስን ስብከት ቀጠለ ማለት ነው ። በመጥምቁና በኢየሱስ መካከል ግን አንድ ልዩነት መኖሩን የወንጌል ታሪክ ያስረዳናል ። ይኸውም መጥምቁ ዮሐንስ ፦ እነሆ ፣ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እያለ ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ ኢየሱስ ብቻ የሰበከ ሲሆን ኢየሱስ ፦ እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ፣ ወደ እኔ ኑ ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ እያለ ስለ ራሱ የሰበከ በመሆኑ ነው ። ዮሐ. ፩ ፣ ፳፱ ። ማቴ. ፲፩ ፣ ፳፰ ።

ኢየሱስ በስብከቱ ኃጢአተኞችን ወደ ራሱ ይጠራ ነበር ። የኃጢአታቸውን ስርየት የሚያገኙት ከእርሱ ነውና ። ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን የተባሉት የዘመኑ መንፈሳውያን መሪዎች ኃጢአተኞች የሚሉአቸውን ይንቁ ነበር ። ኢየሱስ ግን ለኃጢአተኛ ሁሉ እያዘነለት በስብከቱ ወደ ራሱ ሊያቀርበው ይሞክር ነበር ።

ከዚህም በላይ እግዚአብሔር ከጥንት ዘመን ጀምሮ ለሰው የገለጠውን ቃል መሠረት በማድረግ ኢየሱስ ያስተምር ነበር ። ለዚህም በማቴዎስ ወንጌል ከምዕራፍ ፭—፯ ያለው የተራራ ስብከት የተባለው ትምህርት ጥሩ ማስረጃ ሊሆን ይችላል ። ትምህርቱም ጣፋጭና ልብን የሚማርክ ስለ ሆነ በብዙ ሺህ የሚቈጠር ሕዝብ ለመስማት ወደ እርሱ ይጐርፍ ነበር ። እንደ ዘመኑ

መምህራን ሳይሆን በኃይልና በሥልጣን ስለሚያስተምር ብዙዎቹ በማድነቅ ይሰሙታል ።

ፈሪሳውያንና ጻፎች ግን ኢየሱስን አይወድዱትም ነበር ። ካለመውደድም አልፈው ይጠሉት ጀመር ። ይኸውም በመንፈሳዊ ረገድ ያሳዩትን ስንፍና ስለ ዘለፈ፤ ዓለማዊነታቸውንም ስለ ገለጠባቸው ነው ። ማቴ. ፳፫። ከዚህም ሌላ እነርሱን ትቶ ኢየሱስን ይከተል የነበረው ሕዝብ በርከት ያለ በመሆኑ በምቀኝነት ዓይን ሳይመለከቱት አልቀሩም ። ዮሐ. ፲፪ ፡ ፲፱ ።

ስለ ዓለም መጨረሻ ሁኔታዎችም ስለ ፍርድም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አስተምሮአል ። አሁን ያለን በት ዓለም ያልፋል ። እግዚአብሔር ግን በቦታው አዲ ስና ፍጹም የሆነ ዓለም ይተካል ። ማቴ. ፳፬ — ፳፭ ።

## ፮ ፤ ተአምራቱ ።

አራቱ ወንጌላውያን እንደ ተረኩልን ሁሉ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል መምህር ከመሆኑም በላይ ተአም ራትን ለመሥራት ልዩ ኃይል ነበረው ። የዘመኑ ሕዝብ እስኪደነቅ ድረስ ልዩ ልዩ ተአምራታዊ ሥራዎችን በመሥራት ክብሩን ገልጦአል ።

በእጅ በመዳሰስ ወይም አንድ ቃል በመናገር የዕ ውሮችን ዓይን ከፍቶአል ። ሽባዎችንም ፈውሶአል ። ለምጻሞችም በእርሱ ኃይል ከደዌአቸው ነጽተዋል ። በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ በመጠቀም አምስት ሺህ ሰዎችን በበረሀ የመገበበት ጊዜ አለ ። እንዲያውም ሙታንን በማስነሣት በሞት ኃይል ሥልጣን ያለው መሆኑን በግልጥ አሳይቶአል ። ዲዳዎች እንዲናገሩ አድ ርጎአል ። ደንቆሮችም እንዲሰሙ ጆሮአቸውን ከፍቶ አል ። በርኩስ መንፈስ የተያዙትን አድኖአል ።

ይህንን ሁሉ ለማድረግ ያበቃው ለተቸገሩት ሁሉ የተሰማው ፍቅር ነው ። ችግር ለጸናበት ሁሉ ከልብ ያዝንለት ነበር ። የረድኤት እጁንም ይዘረጋለት ነበር ። ዝናውንም የሰሙት ሁሉ ፡—ሁሉን ነገር ደኅና አድር ጎአል እስኪሉ ድረስ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር ። ኢየሱስም በተመላለሰበት ሁሉ ይከተሉታል ። ማር. ፯ ፡ ፴፯ ።

## ፲ ፤ ደቀ መዛሙርትን ጠራ ።

ኢየሱስ ብቻውን አይሠራም ነበር ። የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሕዝብ ሁሉ እንዲዳረስ ገና ከአገልግሎቱ መጀመሪያ አንሥቶ ከእርሱ ጋር ሆነው ሕዝቡን እንዲ ያስተምሩ ደቀ መዛሙርትን ለይቶ ጠራ ። ከማስተማርም ሌላ ድውዮችን እንዲፈውሱ ፤ አጋንንትንም እንዲያወጡ ሥልጣን ሰጣቸው ።

በመጀመሪያ የተጠሩት አሥራ ሁለት ናቸው ። ማር. ፫ ። ከዚያም በኋላ ሌሎችን ሰብዓ ደቀ መዛሙርት መርጦ ወንጌልን እንዲሰብኩ ላካቸው ። በእነርሱም አገልግሎትና ምስክርነት የእግዚአብሔር ቃል የኢየሱ ስም ዝና በብዙ ስፍራ ተሰምቶ ተሰራጭቶአል ። ሉቃ. ፲ ።

## ፲፩ ፤ መከራ ተቀበለ ተሰቅሎም ሞተ ።

ኢየሱስ በስብከቱና በተአምራቱ ለአገሩ ሕዝብ ያስገኘው በረከት ሰፊ ቢሆንም ሰው ስለ እርሱ የሚያ ደርገው አስተያየት በጣም የተለያየ ነበር ።

ግማሾቹ የቸርነት ሥራውን ሁሉ በመመልከት ፦ ደግ ሰው ነው እያሉ ያመሰግኑት ነበር ። ሌሎች ግን ከዚህ በመለየት ፦ አይደለም ፤ ሕዝቡን ያሳስታል ይሉ ነበር ። ዮሐ. ፯ ፥ ፲፪ ። በሥራው የተደሰቱ ሲኖሩ ያልተደ ሰቱበትም ይኖራሉ ማለት ነው ። ጥላቻቸውም እየባሰ ሄደ ። በተለይም የሕዝቡ መሪዎች የሆኑት የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች በጠላት ዓይን ይመለከቱት ነበር ። በተንኰልም ሊያስይዙት ሊገድሉትም ተማከሩ።

ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት አንዱ ከካህናት አለቆች ገንዘብ ተቀብሎ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ ቃል ገባላቸው ። እንዳሰቡትም ሆነላቸው ። በይሁዳ አስቆሮቱ መሪነት ኢየሱስ ተገኘና ተያዘ ።

በሐሰትም ተከስሶ ገዢ ወደ ሆነው ወደ ጴንጤና ዊው ወደ ጲላጦስ ለፍርድ ቀረበ ። ገዢውም ሕዝቡን ለማስደሰት ሲል እንዲሰቅሉት ፈቀደላቸው ።

ኢየሱስ ተሰቅሎ ሞተ።ደቀ መዛሙርቱም ተበታ ተኑ ። በትምህርቱና ተአምራታዊ በሆኑ ሥራዎቹ በሕዝብ

መካከል ብዙ አድናቆትን ያተረፈ ፥ ሰዎችም በብዙ ሺህ የሚከተሉት ኢየሱስ በሕይወቱ መጨረሻ ላይ እንደ ወንበዴ ተቈጥሮ አሳፋሪ በሆነ አሟሟት ሞተ ።

ታላቅ ነቢይ ነው ፥ ሊያድነን የመጣ እርሱ ነው እየተባለ ይታመንበት የነበር አስደናቂ ሰው የወጠነው ነገር በዚህ መፍረሱ ነውን? ፍሬ ቢስ ሆኖ ይቀር ይሆን? የሆነውን ታሪክ ለተከተለ ሰው ኢየሱስ የጀመረው ነገር ያልተሳካ መስሎ ይታይ ይሆናል ። መልካል በሆነ አጀማመር ጀመረ ፥ ፍጻሜው ግን አሳዛኝ ይመስላል ።

እርሱ ራሱ ግን ከመሞቱ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ አንድ ነገር ነግሮአቸው ነበር ። ከሞትሁ በኋላ በሦስተኛው ቀን ከሙታን እነሣለሁ ብሎአል ። ይህ ቃል ግን በመጀመሪያ ምሥጢሩ አልገባቸውም ነበር ። ሆኖም በሞተበት በሦስተኛው ቀን የሆነውን ነገር ባዩትና በሰሙት ጊዜ አስቀድሞ የነበራቸውን ቃል በመገረም አስታወሱት ።

## ፱ ፤ ከሙታን ተነሣ ።

ኢየሱስ ከሞተ በኋላ ከዓለት በተወቀረ መቃብር ውስጥ ተቀበረ ። የመቃብሩም መግቢያ በር በትልቅ ድንጋይ ተዘጋ ። አራቱ ወንጌላውያን ማቴዎስ ፥ ማርቆስ ፥ ሉቃስና ዮሐንስ በታሪካቸው ላይ እንደ ጻፉት ግን በተቀበረበት በሦስተኛው ቀን ጥቂቶች ሴቶች መቃብሩን ለማየትና አስከሬኑን በሽቱ ለመቀባት ወደ መቃብሩ ስፍራ ቢመጡ ድንጋዩን ከመቃብሩ መግቢያ ተንከባሎ አገኙት ። መቃብሩም ባዶ ነው ።

የኢየሱስን ሥጋ በቦታው አላገኙትም ። የእግዚአብሔር መልአክ ግን ተገልጦላቸው ፥— በዚህ የለም ፥ ከሙታን ተነሥቶአል አላቸው ።

ሴቶቹም በፍርሃትና በድንጋጤ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው ያዩትንና የሰሙትን ነገር ቢነግሩአቸው ለጊዜው ከእውነት የራቀ ወሬ መስሎአቸው ሊያምኑት አልቻሉም ። በኋላ ግን ኢየሱስ በተለያዩ ጊዜአት ሕያው ሆኖ ራሱን ለደቀ መዛሙርቱ መግለጡን ወንጌላውያን በጽሑፋቸው መስክረውልናል ።

መግደላዊት ማርያም የተባለችው ሴት በግልጽ አይታዋለች ። ለአሥራ አንዱ ደቀ መቀመዛሙርትም ታይቶአል ። ጴጥሮስም አይቶታል ። ከደቀ መዛሙርቱም ሁለት ሌሎች ኤማሁስ ወደ ተባለችው ከተማ ለመሄድ በመንገድ ላይ ሳሉ ኢየሱስ በመንገድ ላይ ተገናኝቶአቸው አነጋግሮአቸዋል ። ሌሎችም ያዩት አሉ ሲሉ የመጀመሪያ ዘመን ክርስቲያኖች ጸሐፊዎች ጽፈዋል ። ማቴ. ፳፰ ። ማር. ፲፮ ። ሉቃ. ፳፬ ። ዮሐ. ፳—፳፩ ።

ከዚህም ሁሉ የተነሣ የመጀመሪያ ዘመን ክርስቲያኖች የኢየሱስን ተሰቅሎ መሞት ብቻ ሳይሆን ከሙታን መነሣቱንም በደስታ ይመሰክሩ ጀመር ።

## ፲ ፡ ሕዝቦች ሁሉ ቃሉን እንዲማሩ ደቀ መዛሙርቱን ስለ ማዘዙ ።

ኢየሱስ በምድር ላይ በተመላለሰበት ዘመን ቃሉ የተሰበከው በአይሁድ አገር ብቻ ነው ። ይህ ቃል ግን ለሁሉም የሚያስፈልግ ነውና በሕዝቦች ሁሉ መካከል እንዲሰበክ ፈቃዱ መሆኑን ገና ለመጀመሪያዎች ደቀ መዛሙርት ገልጦላቸው ነበር ። ወደ አሕዛብ ሁሉ ሄደው እርሱ ያዘዛቸውን ሁሉ እንዲያስተምሩአቸውና በጥምቀት ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉአቸው ሥልጣናዊ በሆነ ቃል ላካቸው ። ማቴ. ፳፰ ። ሉቃ. ፳፬ ።

አስገራሚ የሆነ ትእዛዝ ነው ።

ለመሆኑ ፡ የዓለምን ሕዝቦች ሁሉ የኢየሱስ ተከታዮች እንዲያደርጉአቸው የታዘዙት እነዚያ አሥራ አንዱ የአይሁድ አገር ሰዎች እንዴት ያሉ ነበሩ? ከፍተኛ ትምህርት ያገኙ ሰዎች አልነበሩም ። በኅብረተሰብ ውስጥ የኑሮአቸው ደረጃ ስም ስማቸውን የሚያስጠራ መጠነኛ ነበር ። ግማሾቹ ዓሣ በማጥመድ የዕለት ገቢአቸውን ያገኙ ነበር ። የመንግሥት ሹመትም አልነበራቸውም ። በመጀመሪያ በባለ ሥልጣኖች መካከል ታዋቂነት እንኳን አልነበራቸውም ።

ይህን የመሰሉ ተራ ሰዎች በትምህርታቸው ዓለምን ሊለውጡ ምን ተስፋ አላቸው? የሚሞክሩት ነገር ከንቱ ልፋት አይሆንባቸውምን?

ከንቱ ልፋት እንዳልሆነባቸው ወደ ፊት የምንመለከተው ታሪክ አስረጂ ሊሆን ይችላል ።

## ፲፭ ፡ ስለ ዕርገቱ ።

ወንጌላዊው ሉቃስ በጻፈው የሐዋርያት ሥራ በተሰኘው መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ በኢየሱስ ምድራዊ ታሪክ መጨረሻ ስለ ሆነው ነገር ለማንበብ እንችላለን ።

ከሙታን ከተነሣ በኋላ አርባ ቀን ለደቀ መዛሙርቱ እየታያቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ያስተምራቸው ነበር ። ሲያስተምራቸውም የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እስኪወርድላቸው ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ ነገራቸው ። የመንፈስን ኃይል ከለበሱ በኋላ በኢየሩሳሌም ፣ በይሁዳም ፣ በሰማርያም ፣ እስከ ምድርም ዳርቻ ድረስ ምስክሮቹ ይሆናሉ ።

ይህን ቃል ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አለ ። ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው ። ከዚያም በኋላ አላዩትም ። ደቀ መዛሙርቱ ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ ግን ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ታዩአቸው ። እነርሱም ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ እንዳዩት ተመልሶ እንደሚመጣ ነገሩአቸው ። ይህንንም ግሩም ተስፋ አግኝተው በደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ። የሐዋ. ምዕ. ፩ ።

## ጥያቄዎች ።

፩. የኢየሱስን የሕይወቱን ታሪክ የጻፉልን ሰዎች እነ ማን ናቸው?

፪. በመጀመሪያ በኢየሱስ ያመኑበት ማን ሆኖ አገኙት?

፫. ኢየሱስ ከተወለደ በኋላ ዮሴፍና ማርያም ይዘውት ወደ ግብጽ አገር የወረዱት በምን ምክንያት ነው?

፬. ኢየሱስ ምን እያለ ይሰብክ ነበር?

፭. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ለምን ጠራ?

፮. በዕርገቱ ከደቀ መዛሙርቱ ከመለየቱ አስቀድሞ ኢየሱስ ምን ብሎ አዘዛቸው?

፯. ከሞተ በኋላ በሦስተኛው ቀን ከሙታን መነሣቱን በዓይናቸው አይተው የመሰከሩለት እነ ማን ናቸው?

## ምዕራፍ ሁለት ።

# የሐዋርያት ዘመን ቤት ክርስቲያን

## ፩ ፤ በኢየሩሳሌም ።

### ሀ ፡ የቃሉ መስፋፋት ።

በመጀመሪያ በኢየሱስ አምነው ክርስቲያኖች የሆኑ አይሁድ ነበሩ ። እነዚህ አዲሶች ምዕመናን በማኅበር አንድነት የኖሩት ኢየሱስ ራሱ ባስተማረበት በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ ነው ። እርሱም በሥጋ ከተለያቸው በኋላ ወዲያው ጸሎት ለማድረግ ይሰበሰቡ ጀመር ። የሐዋ. ፩ ፡ ፲፬ ። በይሁዳ አስቆሮቱ ፈንታ አንድ ሐዋርያ ለመምረጥ የተሰበሰቡት መቶ ሀያ የሚያህሉ ሰዎች ነበሩ ። የሐዋ. ፩ ፡ ፲፭ ።

በመካከላቸው የጠነከረ አንድነት ተፈጥሮ በእውነተኛ ፍቅር እየተዋደዱ በንብረታቸውም በገንዘባቸውም ይረዳዱ ነበር ። በሁኔታቸው ሰውን በጣም የሚያስደስቱ ናቸው ። ከዕለት ወደ ዕለትም አዲሶች ምዕመናን ለቤተ ክርስቲያኒቱ ይጨመራሉ ። የሐዋ. ፪ ፡ ፵፬—፵፯ ።

ሐዋርያትም የወንጌል ስብከታቸውን የጀመሩት በኢየሩሳሌም ነው ። በተለይም በዓለ ኀምሳ የተባለው የአይሁድ በዓል ተከብሮ በዋለበት ጊዜ ሐዋርያት ያደረጉት ስብከት እዚህ ላይ መጠቀስ አለበት ።

ወደ ልዩ ልዩ አገር ፈልሰው የነበር አይሁድ በዓሉን ለማክበር በብዛት ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዘው ነበር ። ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ሆኖ ለእነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል በሰበከ ጊዜ ብዙዎቹ ንስሐ ገብተው በኢየሱስ አመኑ ። በዚያም ቀን ተጠምቀው ለቤተ ክርስቲያን የተጨመሩ ሦስት ሺህ የሚያህሉ ናቸው ። የሐዋ. ፪ ።

በጠቅላላው በሐዋርያት ስብከትና ትምህርት የእግዚአብሔር ቃል እየሰፋ ሄደ ። በኢየሩሳሌምም የደቀ መዛሙርት ቍጥር እጅግ በዛ ። ከተራ ሕዝብም መካከል ብቻ ሳይሆን በቤተ መቅደስ ከሚያገለግሉ ካህናት መካከል እንኳን ብዙ ሰዎች ለክርስቶስ ሃይማኖት ታዛዦች ሆኑ ። የሐዋ. ፮ ፡ ፯ ።

ለ ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ታስረው በተአምራት ተፈቱ ።

ወንጌል ሲስፋፋ ተቃዋሚዎች መነሣታቸው አይቀርም ። ጴጥሮስና ዮሐንስ በኢየሩሳሌም ሕዝቡን ስላስተማሩና ፤— ኢየሱስ ከሙታን ተነሥቶአል ፣ ሕያው ነው እያሉ ይሰብኩ ስለ ነበር የካህናት አለቆች ፣ የመቅደስ አዛዥ ሰዱቃውያንም ተበሳጭተው ያዙአቸውና በወኅኒ ቤት አኖሩአቸው ። በመዛትም በማስፈራራትም ሁለተኛ በኢየሱስ ስም እንዳይናገሩ ለመከልከል ሞከሩ።

ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን ዛቻቸውን ሳይፈሩ ፤— ሰውን ከመስማት ይልቅ እግዚአብሔርን መስማት ፣ ለእርሱም መታዘዝ እንደሚገባን ይሰማናል ። እኛም በበኩላችን ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም ብለው መለሱላቸው ። ከፈቱአቸውም በኋላ የወንጌል ስብከታቸውን ቀጠሉ ። በእጃቸውም ብዙዎች ድውያን ተፈወሱ ።

የሕዝቡ መሪዎችም ይህን ሁሉ አይተው ቅንዓት አደረባቸውና እንደ ገና ሐዋርያትን አሰሩአቸው ። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር በተአምራት ከእስራት አዳናቸው ። መልአክ በሌሊት የወኅኒ ቤቱን በር ከፍቶ ዘበኞች ሳያውቁና ሳያዩ ወደ ውጭ አወጣቸው ። እንዳዘዛቸውም እንደ ገና ሄደው የሕይወትን ቃል ለሕዝቡ ለመንገር ወደ ቤተ መቅደስ አመሩ ።

ካህናትና ሽማግሌዎችም ሰምተው በበለጠ ተቈጥተው ወደ ሸንጎ ቢያመጡአቸው ሐዋርያት እንደ ገና፤— ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል በማለት በምንም ዓይነት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መመስከራቸውን ሊተው እንደማይችሉ ሊነግሩአቸው ቻሉ ።

በዚያን ጊዜ ተገረፉ ። ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን ስለ ኢየሱስ ስም ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቈጠሩ ደስ እያላቸው ከሸንጎው ፊት ወጡ እንጂ ኀዘን ወይም ፍርሃት ምንም አልተሰማቸውም ። የሐዋ. ም. ፫—፭ ።

ሐ ፣ እስጢፋኖስ በሰማዕትነት ሞተ ።

በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ሰባት ዲያቆናት ነበሩ ። የቤተ ክርስቲያኒቱ መበለቶች ሌሎችም ችጋረ

ኞች ከዕለት ወደ ዕለት የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ እንዲያገኙ ይጠነቀቁላቸው ነበር ።

ከእነዚህ አንዱ እስጢፋኖስ ነው ። በዲቁና ከማገል ገሉም በላይ በጥበብና በመንፈስ ስለ ኢየሱስ ይመሰክር ነበር ። በዚህ ምክንያት ሰዎች ጠልተውት ፥— በሙሴና በእግዚአብሔር ላይ የስድብን ነገር ሲናገር ሰምተነዋል የሚለውን የሐሰትን ክስ ሰነዘሩበትና አስያዙት ። ወደ ፍርድ ሸንጎም አቀረቡት ። ሊቀ ካህናቱም በጉዳዩ ቢጠ ይቀው መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመኑን ከመግለጡም በላይ እነርሱን ባለማመ ናቸው ሲወቅሳቸው ሰምተው ንዴታቸው ከመጠን ያለፈ ሆነ ። ጥርሳቸውንም አፋጩበት ። ከከተማም ወደ ውጭ አውጥተው በድንጋይ ወግረው ገደሉት ።

እስከዚህ ድረስ ቢጠሉትም ግን እስጢፋኖስ እስከ ሞት ድረስ ወደዳቸው ። ነፍሱን ከመስጠቱ በፊት ጌታ ሆይ ፥ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው ብሎ ጸለየ ላቸው ።

ስለ እምነቱ ተወግሮ በመሞቱ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሰማዕታት መጀመሪያ የሚለውን የክብር ስም አትርፎአል ።

መሞቱን በተመለከቱትና በተስማሙበት ሰዎች መካከል ሳውል የተባለ አንድ ወጣት ነበር ። የእርሱን ታሪክ ወደ ፊት በሰፊው ልንሰማው እንችላለን ። የሐዋ. ፮—፯ ።

መ ፥ ሐዋርያው ያዕቆብ በሰይፍ ሞተ ።

ጥቂት ጊዜ ካለፈ በኋላ ንጉሡ ሄሮድስ ክርስቲያ ኖችን ያሳድዳቸው ጀመር ። ከአሥራ ሁለቱ አንዱን ያዕ ቆብን የዮሐንስን ወንድም በሰይፍ ገደለው ። አይሁድም በዚህ ነገር መደሰታቸውን አይቶ ጴጥሮስንም ያዘው ። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ግን ጴጥሮስ ተአምራታዊ በሆነ መንገድ በመልአክ እጅ ከእስራት ተፈታ ። የሐዋ. ፲፪ ።

## ፪ ፤ በይሁዳና በሰማርያ ።

### ሀ ፡ የቃሉ መስፋፋት በስደት መካከል ።

የወንጌል ጠላቶች እስጢፋኖስን በመግደል ብቻ አልታገሡም ። በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ላይ ስደትን አስነሡ ። ምዕመናንም በጣም ተጨነቁ ። ሐዋርያት ብቻ በኢየሩሳሌም ውስጥ እስኪቀሩ ድረስ ወንዶችም ሴቶችም ከስደቱ የተነሣ ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ ።

ተበትነው ግን ምን ያደርጋሉ? ተይዘው እንዳይታሰሩ ፤ መከራም እንዳያዩ በየቤቱ ወይም በየዋሻው ለመሸሸግ ይሞክራሉ ወይ? አይደለም ። ሉቃስ በታሪኩ ላይ እንደሚያስረዳን በተበተኑበት ሁሉ ያመኑበትን ቃል ይሰብኩ ነበር ። በፍርሃት ተይዘው ስለ ኢየሱስ ዝም አላሉም ። በደስታ በተቀደሰ ድፍረትም ይመሰክሩ ነበር ። በምስክርነታቸውም የወንጌል ቃል ወደ ብዙ አገር ደረሰ ። ስለዚህ ያዩት መከራ ለወንጌል ሥራ ጠቃሚ እንጂ የሚጐዳ ሆኖ አልተገኘም ለማለት ያስደፍራል ።

ከተሰደዱት መካከል አንዱ ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ከተማ መጣ ። በዚያም የወንጌልን ቃል ሲሰብክ የከተማው ሰዎች በአንድ ልብ ያዳምጡ ነበር ። በፊልጶስም እጅ ብዙ ተአምራት ተደረገ ። ከዚህም ሁሉ የተነሣ የከተማው ሕዝብ ከመጠን በላይ ተደሰተ ። የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ተቀበሉ ።

ፊልጶስና ሌሎቹም በወንጌል ምክንያት ባይሰደዱ ኖሮ ግን ምናልባት ቃሉ እንዲህ በቶሎ አይስፋፋም ነበር ። የሐዋ. ፰ ፡ ፩—፳፭ ።

### ለ ፡ ኢትዮጵያዊው አምኖ ተጠመቀ ።

ፊልጶስ ወንጌልን በሰማርያ ከሰበከ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ወደ ደቡብ ጋዛ ወደሚባለው አገር እንዲጓዝ አዘዘው ። አገሩ በረሀ ነው ።

በዚያም ከአንድ መንገደኛ ጋር ተገናኘ ። መንገደኛው ህንደኬ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ ነው ። ለእግዚአብሔር ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳ

ሌም መጥቶ ነበር ። አሁን ደግሞ በሰረገላው ተቀምጦ ወደ አገሩ በመመለስ ላይ ነው ።

ፊልጶስ ወደ ሰረገላው ቀርቦ መንገደኛው መጽሐፍ ሲያነብ ሰማ ። ያነበበውም ቃል በትንቢተ ኢሳይያስ በምዕራፍ ፶፫ የዓለምን ኃጢአት ተሸክሞ ስለ ሞተው ሰው የተጻፈው ክፍል ነው ።

ፊልጶስ ፡— የምታነበውን ቃል ታስተውለዋለህን? ብሎ ጠየቀው ። እርሱም ፡— የሚመራኝና የሚያስረዳኝ ሰው ሳይኖር እንዴት ይቻለኛል? ብሎ መለሰለት ።

በዚያን ጊዜ ወንጌላዊው የቃሉን ምሥጢር በማብራራት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ መሆኑን ገለጠለት ። የሰውን ኃጢአት ተሸክሞ የሞተ ፣ ነቢዩም ትንቢት የተናገረለት እርሱ ፣ ኢየሱስ ነው ።

ወንጌላዊው ስለ ጥምቀትም ሳያስረዳው አልቀረም ። ጃንደረባውም መንገደኛ ነውና ወደ አገሩ ሊገባ ነው ። በዚያም ሊያጠምቀው የሚችል ሰው የለም ። ስለዚህ ውኃ ወዳለበት ስፍራ ከደረሱ በኋላ ፊልጶስን ፡— እዚህ ውኃ አለ ፣ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምን ነገር አለ? ብሎ ቢጠይቀው ፡— በፍጹም ልብህ ብታምን ይቻላል ሲል መለሰለት ።

ኢትዮጵያዊውም ሰው ፡— ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ የሚል መልስ ሰጠ ። ፊልጶስም ይህን ሰምቶ ከእርሱ ጋር ወደ ውኃ ወርዶ አጠመቀው ። ጃንደረባው ደስ ብሎት ወደ አገሩ ተመለሰ ።

ኢትዮጵያ የተባለች አገር በዘመናችን በዚህ ስም ከምትጠራው አገር የተለየች ትሆናለች ። በጥንት ዘመን በሰሜን በኩል የዛሬይቱ ኢትዮጵያ አዋሳኝ የነበረች የኖባ ኢትዮጵያ ሳትሆን አትቀርም ። መናገሻ ከተማዋም መርዌ ትባል ነበር ። ስለ ትውልድ አገሩ ግን እርግጠኞች ለመሆን አልቻልንም ።

ሆኖም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚያስረዳን በቀን ብዛት የወንጌል መልእክተኞች ወደ አፍሪካ ክፍለ ዓለም ብዙዎች ሆነው መጡ ። የክርስቶስንም ወንጌል ሰምተው የተቀበሉትና ያመኑበት በሺህና በሚልዮን የሚቈጠሩ ሆኑ ።

ከሁሉም አስቀድሞ አምኖ ክርስትና የተነሣው ግን በሐዋርያት ዘመን ከፊልጶስ የተማረው ፆ የንግሥት ህንደኬ አገልጋይና አዛዥ ነው ። በአፍሪካ ክፍለ ዓለም የመጀመሪያ የወንጌል ፍሬ እርሱ ነው። የሐዋ.፰፥፳፮—፵።

ሐ ፣ ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት ።

ከፍ ብለን እንደ ተመለከትነው ጴጥሮስ በሺህ ለሚቈጠሩ አይሁድ ወንጌልን ሰብኮ ነበር ። ከአይሁድ ወገን ያልሆኑት አሕዛብስ? እነርሱ ወንጌልን መስማት አያስፈልጋቸውምን? ያስፈልጋቸዋል ቢባል ፣ ሊነግራቸው ከአይሁድ ወገን የሆነ ፣ ኦሪትንም የተማረ ሐዋርያ ወደ አሕዛብ ቤት ሊገባ ይችላልን?

በዘመኑ ስለዚህ ጉዳይ የተጠራጠሩ ብዙዎች ነበሩ። አይሁድ ኦሪትን ተምረው ነበር ። ግዝረትም አላቸው ። አረማውያንን ግን እንደ ርኩሳን ይቈጥሩአቸው ስለ ነበር ከእነርሱ ጋር ግንኙነት የላቸውም ።

የጴጥሮስም ሁኔታ ከዚህ የተለየ አልነበረም ። እግዚአብሔር ግን በራእይ ተገልጦለት ፦— እኔ ያነጻሁትን አንተ እንደ ርኩስ ነገር ልትቈጥረው አይገባህም ብሎ ተናገረ ።

በዚህ መካከል ከአሕዛብ ቤት ሁለት ሰዎች ጴጥሮስን ሊፈልጉት መጡ ። ነገሩም ለጴጥሮስ ገባው ። ወንጌልን ለመስበክ ወደ አሕዛብ ቤት ለመግባት እችላለሁ ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብሎ ተረዳ ። ከሁለቱም ሰዎች ጋር ተነሥቶ ሄደ ።

ሁለቱ መልእክተኞች ተልከው የመጡት ቆርኔሌዎስ ከተባለው ሰው ቤት ነው ። እርሱም በቂሣርያ የሚኖር የመቶ አለቃ ነበር ። በእግዚአብሔር ፈቃድ ጴጥሮስ ወደዚህ ሰው ቤት ተመርቶ በቤቱ ውስጥ ለነበሩት ሁሉ የክርስቶስን ወንጌል ሰበከላቸው ። እነርሱም አምነው ተቀበሉት ። መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው ። በኢየሱስ ክርስቶስም ስም ተጠመቁ ። ሁሉም የደኅንነትን የምሥራች ስለ ሰሙ ከመጠን በላይ ተደሰቱ ።

ጴጥሮስም ተደስቶ ፦— አሁንስ እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያደላ ገብቶኛል ፤ በአሕዛብ ሁሉ እርሱን የሚፈራውንና ጽድቅን የሚያደርገውን እንደሚቀበል ተረድቼአለሁ አለ ። የሐዋ. ፲ ።

ጥያቄዎች ።

፩. ጴጥሮስና ዮሐንስ በኢየሱስ ስም እንዳይሰብኩ በተከለከሉ ጊዜ ምን ብለው መለሱ?
፪. ከሁለተኛው እስራት የተፈቱት በማን እጅ ነው?
፫. የመጀመሪያ ሰማዕት ተብሎ የተጠራው ማን ነው?
፬. ንጉሥ ሄሮድስ ጴጥሮስን ያስያዘው ምኑን ተመል ከቶ ነው?
፭. የኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች ተሰድደው ወደ ልዩ ልዩ አገር ከተበተኑ በኋላ ምን አደረጉ?
፮. እኛስ ከእነዚያ ክርስቲያኖች ታሪክ ምን ምን ልንማር እንችላለን?
፯. ኢትዮጵያዊው ሰው ከብሉይ ኪዳን ያነበበው ክፍል የትኛው ነው?
፰. ኢትዮጵያዊውን ስለ ኢየሱስ ያስተማረው ማን ነው?
፱. አይሁድ በመጀመሪያ ከአሕዛብ ጋር ስለ ምን ግን ኙነት አያደርጉም ነበር?
፲. እግዚአብሔር ስለ አሕዛብ ለጴጥሮስ ምን ገለጠለት

## ፫ ፤ ፈሪሳዊው ሳውል ክርስቲያን ሆነ ።

ሳውል ክርስቲያኖችን ጠላ ።

ከወጣትነቱ ጀምሮ የኦሪትን ትምህርት ተምሮ ነበር ። የኦሪት አዋቂ ሆነ ። ፈሪሳዊም ተባለ ። የክርስቲ ያኖችም ትምህርት ትልቅ ስሕተት መስሎ ስለታየው እነርሱን ለማጥፋት በቈራጥነት ተነሣ ። እስጢፋኖስ ተወግሮ ሲሞት አይቶአል ፤ መሞቱንም ወደደ ። ይህም ሳይበቃው ቀርቶ በተገኙበት ሁሉ በኢየሱስ ያመኑትን ወንዶችና ሴቶች ይዞ ወደ ወኅኒ ቤት እየጐተተ እንዲ ታሰሩና እንዲጐሳሉ ያደርግ ነበር ።

አንድ ቀን ግን ክርስቲያኖችን ለመያዝ ከኢየሩሳ ሌም ተነሥቶ ወደ ደማስቆ ለመድረስ በመንገድ ላይ ሳለ ፈጽሞ ያላሰበው ነገር ገጠመው ። በድንገት ከፀሐይ ብሩህነት የበለጠ ብርሃን አየ ። ሳውልም ከድንጋጤ የተነሣ በምድር ላይ ወደቀ ። ድምፅም ሰማ ።

ሳውል ፤ ሳውል ፤ ለምን ታሳድደኛለህ? የሚል ድምፅ ነበር ።

ጌታ ሆይ ፡ ማን ነህ? ብሎ ጠየቀ ሳውል ።

አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ፤ የመውጊያውን ብረት ብትቃወመው ለአንተ ይብስብሃል ብሎ መለሰለት።

አስደናቂና አስፈሪ የሆነ ነገር መስሎ ታየው ። በኃይልና በግርማ በመንገድ ላይ የተገናኘው እርሱ የጠላው ኢየሱስ ራሱ ነው ።

ሳውል ይህን ተገንዝቦ ተሸነፈ ። ኢየሱስንና ተከታዮቹን ማሳደድ ከንቱ ነገር መሆኑን ተረዳ ። ንስሐም ገባ። መጸለይም ጀመረ ።

ከታየው ብርሃን ኃይል የተነሣ ለጊዜው ታውሮ ነበር ። ሐናንያ የተባለው የደማስቆ አገር ክርስቲያን ግን እጁን በጫነበት ጊዜ ዓይኑ እንደ ገና ተከፈተ ። ተነሥቶም ተጠመቀ ።

## ስለ ክርስቶስ ይመሰክር ጀመር ።

የኢየሱስን ተከታዮች ይጠላ የነበር ሳውል ራሱ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ሆነ ። ወዲያውም ስለ ኢየሱስ ይመሰክር ጀመር ። በመጀመሪያ ግን ክርስቲያኖች ይፈሩት ነበር ። እኛን ለመግደል የፈለገው በእውነት ከእኛ እንደ አንዱ ሆኖአልን? እያሉ ይጠራጠሩ ነበር ።

ነገር ግን የሰሙት ታሪክ ውሸት አይደለም ። በእርግጥ ሳውል ተለውጦአል ። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ፡ ሰውን ለማዳን የመጣ ነው የሚለውን እምነት ተቀብሎአል ።

ታሪኩን የሰሙት ክርስቲያኖች ሁሉ ተገረሙ ፡ ተደሰቱ ፡ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ ።

ጳውሎስ ክርስቶስን የሕይወቱ ጌታ አድርጎ ከተቀበለው በኋላ በበርናባስ ተመርቶ ከሐዋርያት ጋር እንዲተዋወቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ ። በዚያም በድፍረት በኢየሱስ ስም ይናገር ነበር ። ያላመኑት አይሁድ ግን ሊገድሉት ስለ ፈለጉ በእምነት ወንድሞቹ የሆኑ ሰዎች ወደ ቂሣርያ ፡ ከዚያም ወደ ትውልድ አገሩ ወደ ጠርሴስ እንዲደርስ ሰደዱት ። ለጊዜውም በዚያ ኖረ ። የሐዋ. ፱።

በዚህ ሁሉ መካከል በይሁዳ ሁሉና በገሊላ አገርም በሰማርያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ፡ እያደጉም ሄዱ ። ምዕመናንም እግዚአብሔርን በመፍራት ፡ በመንፈስ ቅዱስም በመጽናናት በረቱ።የሐዋ. ፱።

## ፬ ፤ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ተቋቋመች ።

እስጢፋኖስ በሞተበት ጊዜ በተጀመረው ስደት ምክንያት በኢየሩሳሌም የነበሩ ብዙዎች ክርስቲያኖች ወደ ልዩ ልዩ አገር መበተናቸውን ከዚህ በፊት ሰምተ ናል ። ከእነርሱም መካከል እስከ ቆጵሮስ ፥ እስከ ፊንቄም አገር ፥ ከዚያም አልፈው እስከ አንጾኪያ ድረስ የደረሱ አሉ ። በተበተኑበትም ሁሉ ያለ ፍርሃት የጌታን የኢየ ሱስን ቃል ይናገሩ ነበር ።

አንጾኪያ የሶርያ ክፍለ አገር ዋና ከተማ ናት ። በስፋትም በሕዝብም ብዛት ከሮሜና ከእስክንድሪያ ቀጥላ ሦስተኛ የሮሜ መንግሥት ከተማ ስለ ሆነች ትልቅ ናት ። በዚህች ከተማም ብዙዎች ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ተመለሱ ።

ምዕመናን ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያኖች ተብለው የተጠሩት በአንጾኪያ ከተማ ነው ። የሐዋ. ፲፩ ፥ ፳፮ ። ይህንን ስም ያወጡላቸው የአገሩ አሕዛብ ናቸው ። ይህም ሲሰድቡአቸውና ሲያፌዙባቸው ነው ። ክርስቶስ የሚለ ውን ስለሚያመልኩ ክርስቲያኖች ይሉአቸው ነበር ። ሩቅ ባልሆነ ጊዜ ውስጥ ግን ክርስቲያን የሚለው ስም የስድብ ስም መሆኑ ቀርቶ በኢየሱስ ያመነ ሁሉ የሚ ጠራበት የተለመደ መጠሪያ ሆነ ።

የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ደስ በሚያሰኝ አኳኋን እየተስፋፋችና እየበረታች ሄደች ። ወረድ ብለን እንደ ምናየውም በሐዋርያት ዘመን በወንጌል ሥራ በኩል ትልቅ አገልግሎት ያበረከተች ቤተ ክርስቲያን ሆነች ። የሐዋ. ፲፩ ፥ ፲፱—፴ ።




ይህ ካርታ ሐዋርያው ጳውሎስ ከበርናባስ ጋር ሆኖ በመጀመሪያው የወንጌል ስብከት ጉዞው ላይ የተጓዘበትን መንገድ ያሳያል ። በነጥቦች የተመለከቱትን መስመሮች ይመልከቱ ።

በሐዋርያት ሥራ በምዕራፍ ፲፫ እና ፲፬ እንደ ምናነበው ጳውሎስና በርናባስ በመንፈስ ቅዱስ ለወንጌል ሥራ ከተለዩ በኋላ ከሶርያው አንጾኪያ ተነሥተው በመጀመሪያ ወደ ሴሌውቅያ ወርደው መርከብ አግኝተው ወደ ቆጵሮስ ተሻገሩ ። በዚያም ከስልማና ወደ ጳፉ በእግር ተጓዙ ። ከዚያም እንደ ገና በመርከብ ተሳፍረው ወደ ጴርጌን መጡ ፤ ከዚያም ወደ ጵስድያው አንጾኪያ በእግር መጡ ፤ በኋላም ወደ ኢቆንዮን ፤ ወደ ልስጥራም ፤ ወደ ደርቤንም ተጓዙ ። በጉዞአቸው እስከዚህ ድረስ ደርሰው በመጡበት መንገድ ተመለሱ ። እንደ ገናም ከጴርጌን በመርከብ ተሳፍረው ወደ አንጾኪያ መጡ ። የመጀመሪያውም ጉዞ ፍጻሜ ሆነ ።

## ፩ ፤ የእግዚአብሔር ቃል እንዲሰብኩ በርናባስና ጳውሎስ ተላኩ ።

በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል በርናባስና ሳውል ይቈጠሩ ነበር ። ለሳውል ሌላ ስም ተሰጥቶት ጳውሎስ እየተባለ ይጠራ ጀመር ።የሐዋ.፲፫፥፱።

የቤተ ክርስቲያኒቱ ምዕመናን በጾምና በጸሎት ጌታን ሊያመልኩ ተሰብስበው ሳሉ መንፈስ ቅዱስ ፦— በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ ።

ሁለቱም በአሕዛብ መካከል ወንጌልን እንዲሰብኩ በጾምና በጸሎት ተለዩ ። በአሕዛብ መካከል የወንጌል ሥራ በሰፊው የተጀመረው በዚያን ጊዜ ነው ለማለት እንችላለን ። እግዚአብሔር በመልእክተኞቹ ተጠቅሞ በቃሉ ኃይል ግሩም የሆኑትን ሥራዎች ሠርቶአል።

### ሀ ፡ በቆጵሮስ አገረ ገዢው አመነ ።

በርናባስና ጳውሎስ በጕዞአቸው ላይ በመርከብ ቆጵሮስ ወደ ተባለችው ደሴት መጡ ። በብዙ ስፍራም የእግዚአብሔርን ቃል ሰበኩ ። ተራ ሕዝብም ብቻ ሳይሆን ሰርግዩስ ጳውሎስ የሚባለው አገረ ገዢውም የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ፈለገ ። ካጠገቡ ግን የሐዋርያትን ስብከት የተቃወመ ኤልማስ የተባለ ጠንቋይ አለ ። እርሱም ገዢውን ከማመን ሊያጣምመው ስለ ፈለገ ጳውሎስ ተቈጣውና ፦— እነሆ ፥ የጌታ እጅ በአንተ ላይ ናት ፥ ዕውር ትሆናለህ እስከ ጊዜውም ፀሐይን አታይም ብሎ በተናገረ ጊዜ እግዚአብሔር የጠንቋዩን ዓይን አሳወረው ።

አገረ ገዢውም የሆነውን ነገር በመገረም ተመልክቶ የጌታን ትምህርት አመነ ። የሐዋ. ፲፫ ፥ ፩—፲፪ ።

ለ ፤ በጵስድያ አንጾኪያ አይሁድ ተቃውመው ሐዋርያ ትን አባረሩ ።

ከቆጵሮስ ተነሥተው በመርከብ ወደ ትንሽዋ እስያ ተሻገሩ ። ወደ ጵስድያም አገር በደረሱ ጊዜ አንጾኪያ በተባለች ከተማ የአይሁድን ምኵራብ አገኙ ። ይህች ከተማ በሶርያ አገር ከምትገኘው አንጾኪያ ከተባለችው የተለየች ናት ። ሐዋርያት ወደ አይሁድ ምኵራብ ገብ ተው የክርስቶስን ወንጌል ሰበኩ ።

በመጀመሪያው ሰንበት አይሁድ በትዕግሥት መል እክታቸውን ሰሙ ። በሁለተኛው ሰንበት ግን ለመስማት በጣም ብዙ ሕዝብ ስለ ተሰበሰበ በአይሁድ ቅንዓት ሞላባቸውና እየተሳደቡ ጳውሎስ የተናገረውን ቃል ተቃወሙ ።

ጳውሎስ ግን ፡— አይሁድ እንደ መሆናችሁ መጠን የእግዚአብሔርን ቃል አስቀድማችሁ መስማት የሚገ ባችሁ እናንተ ነበራችሁ ። ነገር ግን ከዚህ ቃል የሚገ ኘውን የዘላለምን ሕይወት ከናቃችሁት እኛ ወደ አሕ ዛብ እንሄዳለን አላቸው ። ብዙዎች አሕዛብም ቃሉን ሰምተው በደስታ ተቀበሉት ። ወንጌልም በአካባቢው ሁሉ ተስፋፋ ።

ቢሆንም የወንጌል ጠላቶች የሆኑት አይሁድ መቃ ወማቸውን አልተውም ። ኃይል ያላቸውን ሰዎች መኳን ንትንም አስነሥተው ሐዋርያት ከአገር እንዲወጡ አስ ገደዱአቸው ። ወደ ሌላ አገርም መንገዳቸውን ቀጠሉ ። የሐዋ. ፲፫ ፤ ፲፫—፶፪ ።

ሐ ፤ ሰዎች በብዛት አመኑ ፤ ድውያንም ተፈወሱ ።

ሐዋርያት ኢቆንዮን ወደ ተባለችው ከተማ መጡ ። በዚያም የእግዚአብሔርን ቃል ሰብከው ብዙዎች ሰዎ ችን አሳመኑ ። ጌታም በእጃቸው ብዙ ተአምራት በማድ ረጉ የቃሉን እውነተኛነት መሰከረ ።

አሁንም ግን ምቀኛና ክፉ ሰው ተነሣባቸው ። አይሁድም አሕዛብም ተባብረው ሊያንገላቱአቸውና ሊወግሩአቸው አሰቡ ። ጳውሎስና በርናባስ ይህንን አይ ተው ወደ ሊቃኦንያ ሸሹ ። በዚያም ያለ ፍርሃትና ያለ መሰልቸት ወንጌልን ሰበኩ ።

ልስጥራ በተባለ አገር እግሩ የሰለለ አንድ ሰው ነበር ። ይህም ሰው ጳውሎስ ሲናገር ሰማና እስከ ማመን ደርሶ ነበር ። ሐዋርያውም ይህን ተገንዝቦ ሕመምተኛ ውን በጌታ ኃይል ፈወሰው ። የአገሩ ሕዝብ ያልተማሩ አረማውያን ናቸውና ይህንን ተአምራት ባዩ ጊዜ፡— አማልክት ሰዎችን መስለው ወደ እኛ ወርደዋል እያሉ ተገረሙ ። ኮርማዎችንም አምጥተው ሊሠውላቸው ፈለጉ።

ሐዋርያት ግን ፡— ተው ፤ እኛ እንደ እናንተ ሰዎች ነን ፤ አማልክት አይደለንም ፤ ወደ እግዚአብሔርም እንድትመለሱ ወንጌልን እንሰብክላችኋለን ብለው ጮኹና እንዳይሠውላቸው አስተውአቸው ። የሐዋ. ፲፬ ፤ ፩—፲፰።

መ ፤ ጳውሎስ ተወገረ ።

የወንጌል ጠላቶች አሁንም ማስቸገራቸውን አልተ ውም ። ሐዋርያት ወደ ነበሩበት ስፍራ ተከታትለው መጡ ። የአገሩንም ሕዝብ አባብለው አስነሥተው ጳውሎስን ያዙና በድንጋይ ደበደቡት ። በኃይል ስለ ወገሩት ራሱን ስቶ በመሬት ላይ ወደቀ ። የሞተም መስ ሎአቸው ከከተማ ወደ ውጭ ጐተቱት ። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርት ደርሰውለት ሲከብቡት ሳሉ ተነሥቶ እንደ ገና ወደ ከተማ ገባ ።

በማግሥቱም ከበርናባስ ጋር ደርቤን ወደ ተባለ ችው ከተማ ሄደ ። በዚያም ሁለቱም የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክ ብዙዎች ሰዎችን ወደ እምነት መንገድ መለሱ ። የሐዋ. ፲፬ ፤ ፲፱—፳፩ ።

ሠ ፤ የጳውሎስና የበርናባስ የወንጌል ስብከት ጉዞ ተፈጸመ።

በደርቤን የእግዚአብሔርን ቃል ከሰበኩ በኋላ ፡— ወደ መጣንበት ስፍራ ሁሉ ተመልሰን በክርስቶስ ያመ ኑትን ሰዎች ብናጽናናቸውና ብናበረታታቸው ጥሩ ነው በማለት አዲሶቹን አብያተ ክርስቲያናት ጐበኙአ ቸው ። እነዚያ ክርስቲያኖች ያመኑት በብዙ መከራ መካከል ስለ ሆነ ሐዋርያት ፤ ወደ እግዚአብሔር መንግ ሥት በብዙ መከራ መግባት ያስፈልገናል እያሉ ያደ ፋፍሩአቸው ነበር ።

ከዚያም በኋላ እንደ ገና በመርከብ ተሳፍረው ወደ መጡበት ወደ አንጾኪያ ተመለሱ ። የሐዋ. ፲፬፡፳፪—፳፰።

## ፮ ፤ በኢየሩሳሌም ስለ ተደረገው ጉባዔ ።

ወንጌልን ሰምተው በክርስቶስ ያመኑት አሕዛብ ተገዝረው የሙሴን ሕግ መጠበቅ ያስፈልጋቸዋልን? አዎን ፣ ያስፈልጋቸዋል ብለው የተከራከሩ አይሁድ ነበሩ። ከአሕዛብ ወገን ወደ እግዚአብሔር የተለመሱት ሁሉ እንደ እኛ እንደ አይሁድ የሙሴን ሥርዓት ካልጠበቁ ሊድኑ አይችሉም ማለታቸው ነው ።

እነ ጳውሎስና በርናባስ ግን ሊደግፉአቸው አልቻ ሉም ። ስለ ጉዳዩም እንዲወያዩ ሐዋርያት ሁሉ የተገኙ በት በኢየሩሳሌም ጉባዔ ተደረገ ። በጉባዔውም ላይ ጴጥሮስ ፣ በርናባስና ጳውሎስም በአሕዛብ መካከል ያዩ ትን ተአምራታዊ ነገር ሁሉ ሊተርኩ ቻሉ ። አሕዛብ ሳይገዘሩ ፣ የሙሴንም ሥርዓት ሳይጠብቁ በክርስቶስ በማ መንና የጥምቀትን ጸጋ በመቀበል ብቻ እንዴት እንደ ዳኑ ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ እንዴት እንዳገኙ ለጉባዔው ተካፋዮች ነገሩአቸው ።

በጉባዔው ላይ የነበሩት ሁሉ ይህን ሰምተው ፡— የሙሴን ሥርዓት ሳይጠብቁ እግዚአብሔር አሕዛብን እንደ ተቀበለ ሰምተናልና ክርስቲያኖች እንዲባሉ እንደ አይሁድ መሆን አያስፈልጋቸውም ብለው ተስማሙ ።

ከአሕዛብ ወገን ለሆኑት ክርስቲያኖችም ደብዳቤ እንዲጻፍ ወሰኑ ። በደብዳቤውም ላይ ፡— ለጣዖት ከተሠዋ ፣ ከደምም ፣ ከታነቀም ፣ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው ነገር በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና ፤ ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላች ሁ ፤ ጤና ይስጣችሁ የሚሉትን አጽናኝ ቃላት ጻፉላቸው።

ክርስቲያኖች በተለይ ከደምና የታነቀውን እንስሳ ከመብላት እንዲርቁ የመከሩአቸው በአካባቢአቸው ያሉ ትን እንደ አሪት ሕግ የሚኖሩትን አይሁድ በሁኔታቸው እንዳያሳዝኑአቸው በማሰብ ነው ። የሐዋ. ፲፭ ።

ከአሕዛብ ወገን የተገኙት ክርስቲያኖች የደብዳቤ ውን ቃል በሰሙ ጊዜ ተጽናኑ ፣ ደስም አላቸው ።

### ጥያቄዎች ።

፩. ጳውሎስ ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት እምነቱ እን ዴት ነበር?

፬. የክርስቶስ ተከታይ እንዲሆን ያነሣሣው ምንድር ነው?
፫. ስለ አንጾኪያ ከተማና ቤተ ክርስቲያን ምን ምን ያውቃሉ?
፬. በጳውሎስ የመጀመሪያ የወንጌል ስብከት ጉዞ ላይ ከእርሱ ጋር የሄደ ማን ነው?
፭. የሰርግዮስ ጳውሎስ ታሪክ በአጭሩ እንዴት ነው?
፮. ሐዋርያት በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰ ብኩ ከሌሎች ሁሉ አብልጠው ሊቃወሙአቸው የተነሡ እነማን ናቸው?
፯. ጳውሎስና በርናባስ የእግዚሬብሔርን ቃል የሰበኩት በስንት አገሮች ነው?
፰. በኢየሩሳሌም የሐዋርያት ጉባዔ ለምን ተደረገ?
፱. በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በጉባዔው ላይ ምን ተወሰነ?

## ፯ ፤ ጳውሎስ የወንጌል ሥራውን ቀጠለ ።

### ሁለተኛው ጉዞ ።

ሀ ፤ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ።

ከኢየሩሳሌም ጉባዔ በኋላ ጳውሎስ ሲላስን ይዞ ሁለተኛውን የስብከት ጉዞ ጀመረ ። በመንገድ ላይ ጢሞቴዎስን አግኝቶ እርሱም በወንጌል ሥራ እንዲያ ብራቸው አደረገ ።

ጉዞውን የጀመሩት በትንሽዋ እስያ ውስጥ ያሉትን አገሮች በመጎብኘት ነበር ። በሄዱበትም አገር ሁሉ ወን ጌልን ሲሰብኩ ሳሉ አምነው የተቀበሉት ከዕለት ወደ ዕለት ለቤተ ክርስቲያን ይጨመሩ ነበር ።

መንገዳቸውን ወደ ምሥራቅ አገሮች ለመቀጠል አስበው ነበር ። እግዚአብሔር ግን ወደ ምዕራብ እንዲ ሄዱ በመንፈሱ መራቸው ። ይኸውም በሌሊት ለጳው ሎስ ራእይ በማሳየቱ ነው ።

በስተ ምዕራብ በባሕር ማዶ መቄዶንያ በሚባለው አገር አንድ ሰው ቆሞ ፦ ወደ መቄዶንያ ተሻገርና እርዳን እያለ ሲለምነው በራእይ ታየው። ሐዋርያትም ወደዚያ እንዲሄዱ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን በዚያን ጊዜ ተረዱና በመርከብ ተሳፍረው ወደ መቄዶ

ንያ ተሻገሩ ። ወደ ፊልጵስዩስም ከተማ ደረሱ ። የሐዋ. ፲፮ ፥ ፩—፲፪ ።

ልድያ አመነች ።

ከከተማ ትንሽ ወጣ ብሎ ሴቶች የሚሰበሰቡበት አንድ የጸሎት ስፍራ ነበር ። በእነርሱም መካከል ልድያ የሚሉአት የቀይ ሐር ነጋዴ ነበረች ። እርስዋም ከሐዋ ርያት ቃሉን በናፍቆት ትሰማ ነበር ። ጌታም ልብዋን ከፈተላትና በኢየሱስ አመነች ። በቤትዋም ካሉት ሰዎች ጋር ተጠመቀች ።

በመቄዶንያ አገር የመጀመሪያ የወንጌል ፍሬ ሆና የተገኘች ልድያ ናት ። የሐዋ. ፲፮ ፥ ፲፫—፲፭ ።

በፊልጵስዩስ ወኅኒ ቤት ስለ ሆነው ተአምራት ።

ጳውሎስና ሲላስ በፊልጵስዩስ ውስጥ ሳሉ የሮሜ ሰዎች ተነሥተው ፦— ከተማችንን ያናውጣሉ ፤ ለእኛም ያልተፈቀደልንን ልማዶች ይናገራሉ ብለው ከሰሱአ ቸው ። በገዢዎችም ትእዛዝ ታስረው ተደበደቡ ። በኋ ላም ወደ ወኅኒ ቤት ተጨመሩ ። እንዳያመልጡም እግራቸው በግንድ ተጣብቆ ተጠረቀ ።

ጳውሎስና ሲላስ ግን በመንፈቀ ሌሊት እየጸለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ያመሰግኑ ነበር ። በዚህም መካ ከል እግዚአብሔር አስደናቂ የሆነ ተአምራት ሠራላቸው ።

ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ ። ሰውም ሳይነካቸው የወኅኒ ቤቱ ደጆች ተከፈቱ።የእስረኞቹም እስራት ተፈታ።

የወኅኒ ቤቱ ጠባቂ ከእንቅልፍ ነቅቶ የሆነውን ነገር ባየ ጊዜ ፤ እስረኞች ሁሉ ያመልጡብኛል ብሎ ደነገጠና ራሱን ለመግደል አሰበ ። ጳውሎስ ግን ፦— ሁላችንም እዚህ አለንና በራስህ ላይ ክፉ ነገር አታድ ርግ ብሎ ጮኸበት ።

እርሱም ይህንን ሰምቶ ወደ ፊት መጣና ፦—ጌቶች ሆይ ፤ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል ብሎ ቢጠይ ቃቸው ፦— በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰቦችህም ትድናላችሁ አሉት ። በዚያን ጊዜ ወን ጌልን ተቀበለ ። እርሱም ቤተ ሰቦቹም ተጠመቁ ። በእግ ዚአብሔር ስላመነ ከቤተ ሰዎቹ ጋር በጣም ተደሰተ ። የሐዋ. ፲፮ ፥ ፳—፴ ።

ከፍ ብሎ የሚታየው ታሪክ እንደሚያስረዳን የሐዋርያት መታሰር እንኳን የእግዚአብሔርን የማዳኑን ሥራ ሊያግደው አልቻለም ። እግዚአብሔር ሥራውን ለመሥራት ሁልጊዜ መንገድ አለው ።

## ለ ፣ ተሰሎንቄ ፣ አቴና ፣ ቆሮንቶስ ።

ሐዋርያት በፊልጵስዩስ ከእስራት ከተፈቱ በኋላ ጕዞአቸውን ቀጠሉ ። የጌታን ቃል ለመስበክ ወደ ተሰሎንቄ ደረሱ ። አይሁድ ቢያስጨንቁአቸው ግን የአገሩ ክርስቲያኖች ወንድሞች ጳውሎስንና ሲላስን በሌሊት ቤርያ ወደ ተባለችው ከተማ ሰደዱአቸው ። በዚያም የአገሩ ሕዝብ በተሻለ መንፈስ ቃሉን ሰምተው ተቀበሉት ።

ከዚያም ጳውሎስ ወደ ገናናዋ ከተማ ወደ አቴና ደርሶ በብዙዎች አዋቂዎችና ፈላስፋዎች ፊት የእግዚአብሔርን ቃል ሰበከ ።

ለጊዜው በትዕግሥት ሰሙት ። የሙታን ትንሣኤ አለ ባላቸው ጊዜ ግን ግማሾቹ አፌዙበት ፣ እውነትም አልመሰላቸውም ። እኩሌቶቹ ግን ፡— ስለዚህ ነገር ሁለተኛ እንሰማሃለን አሉት ። በሰሙትም መካከል እስከ ማመን የደረሱ አሉ ።

ከአቴና ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ መጣ ። ብዙዎች ሰዎችም የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው አምነው ተጠመቁ ።

በአጭሩ ፣ ሐዋርያት በደረሱበት ስፍራ ሁሉ ቃሉን በናፍቆት የሰሙትና ያመኑበት በርከት ያሉ ናቸው ። ሐዋርያትም ምዕመናንም ከደስታቸው ብዛት የተነሣ እግዚአብሔርን አመሰገኑ ።

ወንጌልን ለማስፋፋት መከራ ማየታቸው የማይቀር ነገር ሆነ ። ስለ ጌታ ብለው ግን ሁሉንም በደስታ ሊያሳልፉ ቻሉ ።

በመጨረሻም በቆሮንቶስ በመርከብ ተሳፍሮ በኤፌሶን በኩል አልፎ ወደ መጣበት አገር ተመለሰ ። የሁለተኛውም ጕዞ ፍጻሜ ሆነ ። የሐዋ. ም. ፲፯—፲፰ ፡ ፳፪ ።




ይህ ካርታ ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለተኛው የወንጌል ስብከት ጉዞ ላይ የተጓዘበትን መንገድ ያሳያል ። በነጥቦች የተመለከተውን መስመር ይመልከቱ ። ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፲፭ ፥ ፴፮ ጀምሮ እስከ ምዕራፍ ፲፰ ፥ ፳፪ ያለው ታሪክ እንደሚያመለክተው ጳውሎስ ከሲላስና ከሌሎች የመንገድ ጓደኞቹ ጋር ቀጥሎ ያሉትን አገሮች ጐብኝቶአል ።

፩· ከኢየሩሳሌም እስከ ሶርያና እስከ ኪልቅያ ።
፪· ከኪልቅያ እስከ ደርቤን ።
፫· ከደርቤን እስከ ልስጥራ ።
፬· ከልስጥራ እስከ ኢቆንዮን ።
፭· ከኢቆንዮን እስከ አንጾኪያ ።
፮· በፍርግያና በሚስያ አልፎ ከአንጾኪያ እስከ ጢሮአዳ።
፯· ከጢሮአዳ እስከ ፊልጵስዩስ ።
፰· ከፊልጵስዩስ እስከ ተሰሎንቄ ።
፱· ከተሰሎንቄ እስከ ቤርያ ።

፲. ከቤርያ እስከ አቴና ።
፲፩. ከአቴና እስከ ቆሮንቶስ ።
፲፪. ከቆሮንቶስ እስከ ኤፌሶን ።
፲፫. ከኤፌሶን ወደ ቂሣርያ ።
፲፬. ከቂሣርያ ወደ ኢየሩሳሌም ።

## ሦስተኛው ጕዞ ።

ሀ ፣ በገላትያና በፍርግያ ።

በሦስተኛው ጕዞ ላይ ከአንጾኪያ ተነሥቶ አስቀ ድሞ በገላትያና በፍርግያ አገሮች አለፈ ። በደረሰበትም ሁሉ የክርስቶስን ደቀ መዛሙርት በእግዚአብሔር ቃል ያጸና ነበር ። የሐዋ. ፲፰ ፣ ፳፫ ። በእነዚህም አገሮች ካለፈ በኋላ ወደ ኤፌሶን መጣ ።

ለ ፣ ጳውሎስ በኤፌሶን ።

የወንጌል መስፋፋት ።

የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ጳውሎስ ብዙ ጊዜ በኤፌሶን ቆየ ። በመጀመሪያ ወደ አይሁድ ምኵራብ እየሄደ ሦስት ወር ያህል ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ያስተምር ነበር ።

በኋላ ግን ሰዎች የክርስቶስን መንገድ ሊሰድቡ ተነሡ ። አለማመናቸውን ገለጡ ። ከዚህም የተነሣ ጳው ሎስ በምኵራብ ማስተማሩን አቋርጦ ጢራኖስ በሚሉት ሰው ትምህርት ቤት ወይም አዳራሽ ደቀ መዛሙርቱን እየሰበሰበ ያስተምር ጀመር ። ይህንንም ሲያደርግ ሁለት ዓመት ያህል በኤፌሶን ቆየ ። በእስያም የኖሩት አይሁድና የግሪክ ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል እስኪሰሙ ድረስ ትምህርቱ ተስፋፋ ። የሐዋ. ፲፱ ፣ ፳—፲ ።

ሐዋርያው ካስተማረው ትምህርት በጌታ ስምም ካደረገው ተአምራት የተነሣ በኢየሱስ እስከ ማመን የደረሱ ብዙዎች ናቸው ። ኃጢአታቸውንም ለመናዘዝ መጡ ። በእነርሱም መካከል አስማተኞችም ነበሩ ። የክርስቶስን ቃል በሰሙ ጊዜ የነበሩበትን የጨለማ ሥራ ለመተው ሲሉ የአስማት መጽሐፋቸውን አምጥ ተው በሰው ሁሉ ፊት አቃጠሉት ። ዋጋውም ቢታሰብ

አምሳ ሺህ ብር ሆኖ ተገኘ ፣ የሚል ቃል በታሪኩ ላይ ተጽፎ ይገኛል ። የሐዋ. ፲፱ ፣ ፲፭—፳ ።

ይህ ግሩም የሆነ ታሪክ እንደሚያስረዳን የጌታ ቃል በኃይል ይስፋፋና ያሸንፍ ነበር ።

አንጥረኞች ያስነሡት ሁከት ።

የቃሉን መስፋፋት ለመከልከል ፣ ለወንጌልም ሥራ እንቅፋት ለመሆን የተነሣው ሰዎች አሁንም አልጠፉም ። በኤፌሶን ከተማ ትልቅ ሁከት ተፈጠረ ። ምክንያቱም እንዲህ ነው ።

በዚህች ከተማ አሕዛብ አርጤምስ የተባለችውን ጣዖት ያመልኩ ነበር ። ለእርስዋም ክብር ሲሉ በከተማ ውስጥ ትልቅና ደማቅ የሆነ ቤተ መቅደስ ተሠርቶ ነበር ። ድሜጥሮስ የሚሉት አንድ ብር ሠሪ የአርጤምስን ቤተ መቅደስ ምስሎች በብር እየሠራ ለአንጥረኞች በመሸጥ ብዙ ገንዘብ ያተርፍ ነበር ።

የጳውሎስ ስብከት የጣዖትን አምልኮ የሚያፈርስና የሚያስቀር መሆኑን ይህ ድሜጥሮስ ሳይገነዘብ አልቀረምና የአገሩ ሕዝብ ወደ ፊት አርጤምስን ሳያከብሩአት ቢቀሩ ምስሎችዋንም ለመግዛት እንደማይፈልጉ የታወቀ ነው ። ስለዚህ ንግዳቸው እንዳይበላሽባቸው ድሜጥሮስና ከዚህ ንግድ ትርፍ የሚያገኙ ሌሎችም ሰዎች በከተማ ውስጥ ሁከት አስነሡ ።

የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት እያሉ ጩኸት ጀመሩ ። ብዙ ሕዝብም ተሰበሰበ ። ከጳውሎስ ጓደኞች ሁለቱን ይዘው ወደ ከተማይቱ የጨዋታ ስፍራ ሮጡ ። ጳውሎስም ወደ ቦታው ለመድረስ ቢሞክር እብድ የመሰለው ሕዝብ እንዳይገድለው ወዳጆቹ ከለከሉት ።

የሕዝቡም ጩኸት እየባሰ ሄዶ ሳለ ከተማይቱ በሙሉ በፍጹም ድብልቅልቅ ሆነች ። ሁለት ሰዓት ያህል ፣— የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት እያሉ ጩኸታቸውን ቀጠሉ ።

በመጨረሻ ግን የከተማ ጸሐፊ ሁኔታው አስፈሪ መሆኑን ተገንዝቦ ፡— ይህን የመሰለ ሽብር በባለ ሥል ጣን ፊት የሚያስከስሰን ይሆናል የማለት ሥጋት ስላደ ረበት በሕዝቡ መካከል ተነሥቶ ንግግር አደረገ ። በብዙ ምክርም ዝም ካሰኛቸው በኋላ በክርስቲያኖች ላይ ጉዳት ሳያደርሱባቸው ወደየቤታቸው ተበታተኑ ። የሐዋ. ፲፱ ፡ ፳፫—፵፩ ።

ሐ ፡ የመቄዶንያና የግሪክ አገር ጉብኝቱ ።

ሁከቱ ካለፈ በኋላ ጳውሎስ ምዕመናንን ጠርቶ በእግዚአብሔር ቃል ከመከራቸው በኋላ ተሰናብቶአ ቸው ወደ መቄዶንያ አገር ለመሄድ ተነሣ ። ከዚያም ወደ ግሪክ አገር መጣ ። ሦስት ወር ያህል የእግዚአብሔ ርን ቃል ሲያስተምር ከቆየ በኋላ በመርከብ በቀጥታ ወደ ሶርያ ለመሄድ አስቦ ነበር ። አይሁድ ግን በእርሱ ላይ ሴራ ማድረጋቸውን ስለ ሰማ ሐሳቡን ለውጦ በመጣበት በመቄዶንያ በኩል አልፎ ተመለሰ ።

ከመቄዶንያም በመርከብ ወደ እስያ ክፍለ አገር ተሻገረ ። ወደዚያም ከደረሰ በኋላ ከኤፌሶን ቤተ ክር ስቲያን ሽማግሌዎች ጋር ለመገናኘትና ለመነጋገር በጣም ስለ ፈለገ ሚሊጢን ከተባለችው ከተማ ላከባ ቸው ። እነርሱም በመጡ ጊዜ ልብን የሚነካ ምክር ያለበት ንግግር አደረገላቸው ። በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳቸው ተጠንቀቁ በማለት ፣ ይህን ንም የመሰለ መልካም ምክር በመጨመር የቤተ ክርስ ቲያን አገልግሎታቸውን በትጋት በፍቅርም እንዲያበረ ክቱ ለመናቸው ። የሐዋ. ፳ ፡ ፳፰ ።

ይህም ከሆነ በኋላ ወደ ሶርያ አገር በመርከብ ተመለሰ ። ከዚያም በእግር ወደ ኢየሩሳሌም በመምጣቱ የሦስተኛው የስብከት ጉዞ ፍጻሜ ሆነ ። የሐዋ. ፳—፳፩።

## ፰ ፤ ጳውሎስ የክርስቶስ እስረኛ ሆኖ እስከ ሮሜ ደረሰ ።

### ሀ ፣ በቤተ መቅደስ ተያዘ ።

ከፍ ብለን እንደ ተመለከትነው ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስን ቃል ለማስፋፋት ሲል ብዙዎች አገሮችን ጐብኝቶ ነበር ። አልፎ አልፎ መሰደድ ፣ መገረፍም ፣ መታሰርም ደርሶበታል ። ቢሆንም የወንጌል ስብከቱን ያቋረጠበት ጊዜ የለም ።

ሦስተኛው የወንጌል ስብከት ጉዞ ካለፈ በኋላ ግን የእግዚአብሔርን ቃል በነጻነት ለመስበክ ብዙ ጊዜ አልተሰጠውም ። ወደፊት ረዘም ያለ እስራት ይጠብቀዋል ።

አይሁድ አንድ ቀን በቤተ መቅደስ አግኝተውት ጩኸት አስነሡና ያዙት ። ወዲያውም ሊገድሉት ፈለጉ። በረብሻው መካከል ግን የሻለቃው ከወታደሮች ጋር ደርሶ ከሕዝቡ እጅ አድኖት በምን ምክንያት እንደ ተነሡበት ለማወቅ ወደ ወታደሮች ሰፈር ወሰደው ። የሐዋ. ፳፩ ፣ ፳፯—፴ ።

### ለ ፣ በኢየሩሳሌም አይሁድ ፊት ንግግር አደረገ ።

ጳውሎስ ከሻለቃው አስፈቅዶ በሰፈሩ ደረጃ ላይ ቆሞ ለተሰበሰቡት አይሁድ ንግግር አደረገ ። የራሱን የሕይወት ታሪክ ሲተርክላቸውም በመጀመሪያ ክርስቲያኖችን እንዴት እንዳሳደዳቸው ፣ በኋላም ኢየሱስ በደማስቆ መንገድ ላይ እንዴት እንደ ተገናኘው ፣ ከዚያም በቤተ መቅደስ ሲጸልይ ተመስጦ እንዴት እንደ መጣበትና ኢየሱስ ፦— ፍጠን ፣ ከኢየሩሳሌም ቶሎ ውጣ ፣ ስለ እኔ የምትመሰክረውን አይቀበሉህምና ብሎ እንዳዘዘው ሁሉ አንድ በአንድ ነገራቸው ። ንግግሩንም በመቀጠል ከኢየሱስ ፦—ሂድ ፣ እኔ ወደ አሕዛብ ከዚህ

ወደ ሩቅ እልክሃለሁ የሚለውን ቃል መስማቱን ሊነግ ራቸው ቻለ ።

እስከዚህ ድረስ በጥሞና አዳመጡት ። በውስጣ ቸው የገነፈለው ቊጣ ግን አላስችል ብሎአቸው በንግ ግሩ መካከል አቋረጡትና ፤— እንደዚህ ያለውን ከምድር አስወግደው ፤ በሕይወት መኖር አይገባውም ብለው ወደ ሻለቃው ጮኹበት ። ልብሳቸውንም እየወረወሩ ትቢያን ወደ ላይ ይበትኑ ነበር ።

የሻለቃውም ንዴታቸውን ፈርቶ በጳውሎስ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት በማለት ወደ ሰፈሩ እንዲያገቡት አዘዘ ። በዚያም አሳደረው ። የሐዋ. ፳፪ ።

## ሐ ፤ ጳውሎስ በሸንጎው ፊት ።

አይሁድ በምን ምክንያት እንደ ከሰሱት ለማወቅ ሲል የሻለቃው በማግሥቱ ፈትቶት በካህናት አለቆችና በአይሁድ ሸንጎ ፊት እንዲቆም አደረገ ። በእነርሱም ፊት ንግግር እንዲያደርግ ተፈቀደለት ።

በንግግሩም ላይ ፤— ወንድሞች ሆይ ፤ እኔ ፈሪሳዊና የፈሪሳዊም ልጅ ነኝ ፤ ስለ ሙታን መነሣት ይፈርዱብ ኛል ብሎ ጮኸ ። በሸንጎውም ላይ ግማሾቹ ፈሪሳው ያን ግማሾቹ ሰዱቃውያን ናቸውና ስለ ሙታን ትንሣኤ የማይስማሙ ስለ ሆኑ ጥል ጀመሩና ሸንጎው ተለያየ ። ጳውሎስም እንደ ገና ወደ ወታደሮች ሰፈር ተወሰደ ።

በሁለተኛው ሌሊት ሐዋርያው በታሰረበት ስፍራ ኢየሱስ ተገለጠለትና ፤— ጳውሎስ ሆይ ፤ በኢየሩሳሌም ስለ እኔ እንደ መሰከርህ እንዲሁ በሮሜም ትመሰክር ልኝ ዘንድ ይገባሃልና አይዞህ ብሎ አደፋፈረው ።

ይህ ቃል ጳውሎስን እንዳጽናናው ለማመን እን ችላለን ። ኢየሱስ የተናገረው ቃል አስደናቂም ነው ። ጳውሎስ ነጻነቱን ያጣ እስረኛ ሲሆን በእርሱ በኩል የወንጌል ቃል እንዴት እስከ ሮሜ ድረስ ይደርሳል? እንደሚደርስ ኢየሱስ በዚህ ቃል ሊነግረው ቻለ ። እር ሱም የተናገረው ሁሉ ይሆናል ፤ ይፈጸማል ። ጳውሎስ ራሱ የክርስቶስን ቃል ለመስበክ ወደ ሮሜ ለመድረስ ተስፋ ያደርግ ነበር ። የሐዋ. ፲፱ ፤ ፳፩ ። አሁን እንግዲህ ባላሰበው መንገድ የፈለገው ነገር ሊሟላለት ነው ። የሐዋ. ፳፫ ፤ ፩—፲፩ ።

## መ ፡ በብዙ ወታደር ታጅቦ ወደ ቂሣርያ ስለ መሄዱ ።

አይሁድ ጳውሎስን ከመጠን በላይ ስለ ጠሉት ከመካከላቸው አርባ ሰዎች ያህል ፦ እስክንገድለው ድረስ እንጀራ አንበላም ፡ ውኃም አንጠጣም በማለት በመሐላ ተስማሙ ። ለዚህም መንገድ ሲፈልጉ ፡ የሻለቃው እንደ ገና በሸንጎው ፊት እንዲቆም እንደ ምነውና ወደዚያ ለመድረስ በመንገድ ላይ ሳለ አድብተን እንገድለዋለን ብለው ተመካከሩ ።

ያደረጉት ሴራ ግን እንዲሳካላቸው እግዚአብሔር አልፈቀደላቸውም ። አገልጋዩን የሚያድንበት የራሱ መንገድ አለው ። የጳውሎስ የእኅቱ ልጅ የአይሁድን ክፉ ምክር ሰምቶባቸው ለጳውሎስ ነገረው ። ልጁም በአንድ መቶ አለቃ እጅ ተመርቶ ወደ ሻለቃው ሊደርስ ቻለ ። የሰማውንም ነገር ሁሉ በምሥጢር አሜወተው።

የሻለቃውም ወዲያው ከመቶ አለቆች ሁለቱን ጠርቶ ፡ ሁለት መቶ ወታደሮችን ፡ ሰባ ፈረሰኞችንም ፡ እንዲሁም ሁለት መቶ ባለ ጦር መሣሪያዎችን አዘጋጁ ፤ ከሌሊቱም በሦስተኛው ሰዓት ጳውሎስን በደኅና ወደ ቂሣርያ ወደ አገረ ገዢው ወደ ፊልክስ እንዲያደርሱት ይሁን ብሎ አዘዛቸው ።

ከዚህም ጋር ቀላውዴዎስ ሉስዩስ የተባለው ሻለቃ ስለ ጉዳዩ ለአገረ ገዢው ለፊልክስ ሸኚ ደብዳቤ ላከ ።

ወታደሮቹም በታዘዙበት መሠረት ከሌሊቱ በሦስተኛው ሰዓት ከኢየሩሳሌም ተነሡ ። ጳውሎስ በመካከል በክብት ተቀምጦአል ። ማንም ጠላት እንዳይደርስበትም ወታደር ከፊት ከኋላም ፡ በግራ በቀኝም ከብቦታል። አራት መቶ ሰባ ወታደሮች ሆነው አንቲጳጥሪስ ወደ ተባለው ስፍራ በሰላም አደረሱት ። በማግሥቱም ሰባው ፈረሰኞች ጳውሎስን እስከ ቂሣርያ ድረስ እንዲያደርሱት ተደርጎ ሌሎቹ ወደ ሰፈራቸው ተመለሱ ። ጠላትም ሳይነካው ጳውሎስ ደኅና ሆኖ ወደ ቂሣርያ ደረሰ ። የሐዋ. ፳፫ ፡ ፲፪—፴፭ ።

## ሠ ፡ ጳውሎስ በፊልክስና በፊስጦስ ፊት ።

ሐዋርያው ወደ ቂሣርያ እንደ ተሰደደ አይሁድ በሰሙ ጊዜ ሊከስሱት ጠበቃ ቀጥረው መጡ ።

ጳውሎስም ለተከሰሰበት ነገር መልስ እንዲሰጥ ተፈቅዶለት በገዢው ፊት ያለ ፍርሃት ስለ ክርስቶስና ስለ ደኅንነት መንገድ ተናገረ ። ፊልክስ በሹመት እስካለ ድረስ ግን በጉዳዩ ውሳኔ ለመስጠት አልወደደም ። ስለ ዚህ አዲሱ ገዢ እስኪተካ ድረስ ጳውሎስ እንደ ታሰረ ተቀመጠ ።

አዲሱ ገዢ ፊስጦስ ነው ። በእርሱም ፊት ሊከሰሱት አይሁድ ከኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ ። ብዙ ከባድ ክስም አነሡበት ።

ለዚህም ሁሉ ጳውሎስ መልስ ሲሰጥ ፦— የአይሁድን ሕግ ቢሆን መቅደስንም ቢሆን ቄሣርንም ቢሆን አንዳች ስንኳ አልበደልሁም አለ ።

ፊስጦስ ግን አይሁድን ደስ ለማሰኘት ስለ ፈለገ፦— በእኔ ፊት እንድትፋረድ ወደ ኢየሩሳሌም ልትሄድ ትወድዳለህን? ብሎ ጠየቀው ።

ጳውሎስም ፦— ወደ ኢየሩሳሌም የምሄድበት ምክንያት የለኝም ፣ የቆምሁት በቄሣር ወንበር ፊት ነው ፤ ወደ ቄሣር ይግባኝ ብዬአለሁ ብሎ መለሰለት ።

በዚያን ጊዜ ፊስጦስ ከአማካሪዎቹ ጋር ተመካክሮ፦— ወደ ቄሣር ይግባኝ ብለሃል ፤ ወደ ቄሣር ትሄዳለህ በማት ነገሩን ዘጋው ።

ጳውሎስ ወደ ሮሜ እንዲሄድ ተወሰነ ። የሐዋ. ፳፬—፳፭ ፣ ፲፪ ።

ረ ፣ በመርከብ ወደ ሮሜ ስለ መሄዱ ።

ሐዋርያው በተከሰሰበት ነገር ፍርድ እንዲሰጥ ወደ ቄሣር ይግባኝ ማለቱን ሰምተናል ። ቄሣር የሚኖረው ግን በመናገሻው ከተማ በሮሜ ውስጥ ነው ። ሮሜም ጳውሎስ ከታሰረበት ከቂሣርያ በጣም የራቀ አገር ነው። ወደዚያም ለመድረስ ረጅም የመርከብ ጉዞ ማድረግ ያስፈልጋል ።

ለጉዞው መርከብ ተገኘ ። ጳውሎስም ሌሎችም እስረኞች ተሳፈሩ ። ዩልዩስ የሚሉት መቶ አለቃ እንዲ ጠብቃቸው ትእዛዝ ተቀብሎ ነበር ።

ሙራ ወደሚሉት ወደብ ከደረሱ በኋላ እስከ ኢጣልያ የሚደርስ ሌላ መርከብ ተገኝቶ ወደ እርሱ ገቡ ። ጉዞአቸው ግን በጣም አስቸጋሪ ሆነባቸው ።

ነፋሱ ከወደፊት ሆኖ ከለከላቸውና መንገዳቸውን የቀ ጠሉት በብዙ ድካም ነው ። ነፋሱም እየበረታ ሲሄድ የባሕሩ ሞገድ አስፈሪ ሆነ ። የመንገደኞቹም የመዳን ተስፋ እየመነመነ ሄደ ። ሁላችንም በዚህ በትልቁ ውቅያ ኖስ መካከል ሰጥመን መጥፋታችን ነው የሚለት ሥጋት አደረባቸው ።

እንደዚህ ሲተክዙ ሲፈሩ ሳሉ መንገደኞችን ለማጽ ናናት ጳውሎስ ተነሥቶ ፡— አይዞአችሁ ፤ የእግዚአብሔር መልአክ በዚች ሌሊት ተገልጦልኝ ሁላችንም እንደም ንድን ነግሮኛል ፤ መርከቢቱ ግን ትጠፋለች ብሎ ተናገረ ።

እርሱም እንደ ተናገረው ሆነ ። መላጥያ ወደ ተባ ለች ደሴት ከደረሱ በኋላ መርከቡ ከማዕበሉ ግፊያ የተነሣ ተሰባበረ ። ሁሉም ወደ ባሕር ተጣሉ ። ዋናን የሚያውቁት እየዋኙ ወደ ምድር ሲደርሱ ሌሎችም በሳንቃዎች ወይም በመርከቡ ስባሪ እየተንሳፈፉ ራሳ ቸውን ለማዳን ቻሉ ።

መንገደኞቹ በመላጥያ ሦስት ወር ያህል ከቆዩ በኋላ በሌላ መርከብ እስከ ኢጣሊያ መንገዳቸውን ቀጠሉ ። ፑቲዮሊስ ወደ ተባለው ወደብ ገብተው ከዚያ በእግር እስከ ሮሜ ድረስ ተጓዙ ።

መልአኩ ለጳውሎስ እንደ ተናገረው ሁሉ እግዚ አብሔር ከአደጋ ሁሉ አድኖ በሰላም አደረሳቸው ። የሐዋ. ፳፯ ፤ ፩—፳፰ ፤ ፲፭ ።

## ሰ ፤ ወንጌል ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ሮሜ ድረስ ተሰበከ ።

በኢጣልያ አገር ጳውሎስ ክርስቲያኖችን አገኘ ። እነርሱንም በማየቱ በጣም ተጽናና ። እስረኛ ነው ። ቢሆንም እስራቱ በጣም ጥብቅ አልሆነበትም ። አንድ ቤት ተከራይቶ የፈለገውን ሰው ሁሉ እንዲቀበልና እንዲያነጋግር ተፈቀደለት ። እንዲህ ሆኖ ሁለት ዓመት ተቀመጠ ። ወደ እርሱም ለሚመጡት ሁሉ የእግ ዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተምራቸው ነበር ። የሐዋ. ፳፰ ፤ ፴—፴፩ ።

እስረኛ ሆኖ ወደ ሮሜ የተሰደደው በ፶፱ ዓ. ም. ነው ተብሎ ታስቦአል ። ስለ እስራቱ ፍጻሜ ግን በሐዋ

ርያት መጽሐፍ የተጻፈልን ነገር የለም ። ሁለት ዓመት ታስሮ መቀመጡን እንጂ ከዚያ በኋላ ጳውሎስ እንዴት እንደ ሆነ ይህ መጽሐፍ አያስረዳንም ።

የወንጌል ቃል አስደናቂ በሆነ ፍጥነት የተስፋፋ ከመሆኑ የተነሣ ሐዋርያው ጳውሎስ ገና በሕይወቱ ሳለ ከኢየሩሳሌም እስከ ታላቂቱ እስከ ሮሜ ዋና ከተማ ለመድረስ ቻለ ። በብዙ በሌላ አገርም ተሰብኮ ነበር።

ይህም ሁሉ በሰው ኃይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይል የሆነ ነገር ነው ። በአይሁድ በአረማውያንም መካከል የክርስቶስ የደኅንነት ቃል ተሰብኮ የእግዚአብ ሐር ስም የተከበረና የተመሰገነ ሆነ ።

## ጥያቄዎች ።

፩. በፊልጵስዩስ ከተማ በመጀመሪያ የጳውሎስን ትምህርት ሰምተው ያመኑት እነማን ናቸው?
፪. በሁለተኛው የወንጌል ስብከት ጉዞ ላይ ከጳውሎስ ጋር የነበሩት እነማን ናቸው?
፫. የአቴና ፈላስፋዎች ግማሾቹ የጳውሎስን ስብከት የናቁት በምን ምክንያት ነው?
፬. የወንጌል መልእክተኞች ወደ ኤፌሶን በመጡ ጊዜ ትልቅ ሁከት የተፈጠረው ከምን የተነሣ ነው?
፭. ጳውሎስ በቤተ መቅደስ ሲጸልይ ሳለ ተመስጦ መጥቶበት ኢየሱስ ምን አለው?
፮. በኢየሩሳሌም ከታሰረ በኋላ ኢየሱስ ተገልጦለት ምን በማለት አጽናናው?
፯. በኢየሩሳሌም አርባ አይሁድ ያህል በጳውሎስ ላይ ምን ብለው ተማማሉበት?
፰. ሐሳባቸውን የኢየሩሳሌሙ የጦር አዛዥ እንዴት ለማወቅ ቻለ?
፱. አይሁድ በጳውሎስ ላይ ሐሳባቸውን እንዳይፈ ጽሙበት የጦር አዛዥ ሊያድነው ምን ምን አደረገ?
፲. ጳውሎስ በተከሰሰበት ነገር ንጉሐ ፍርድ እንዲያ ገኝ ያቀረበው አቤቱታ እንዴት ነው?
፲፩. ወደ ኢጣሊያ አገር ጳውሎስና ሌሎችም እስረ ኞች ያደረጉት ጉዞ እንዴት ሆነ?
፲፪. የጳውሎስ መታሰር ለወንጌል መስፋፋት ጠቃሚ ሆነ ለማለት የምንችለው ስለ ምንድር ነው ?

## ምዕራፍ ሦስት ።

# በሮሜ ክርስቲያኖች ስለ እምነታቸው ተሠዉ ።

## ኔሮ ቄሣር ። ፶፬—፷፰ ዓ.ም.

### ስለ ጠባዩ ።

በ፶፬ ዓ.ም. በሮሜ መንግሥት አንድ አስፈሪ የሆነ ሰው የቄሣርን ሥልጣን ጨበጠ ። ስሙ ኔሮ ነው። ኃይል ካገኘ በኋላ ፈጽሞ ለክፉ ሐሳብና ምኞት የተ ገዛ ሆነ ።

የማይስማማው ሰው ቢኖር በሞት ከምድር ገጽ እን ዲወገድ ያደርጋል።የራሱን እናት፥ሚስቶቹንም፥ወንድሙ ንም ብዙዎች ታላላቅ የሮሜን ሰዎች አስገድሎአል ። በልጅነቱም አስተማሪው የነበረው ሰው ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ሕይወቱን እንዲያጣ አድርጎአል ። ዝሙተኛ፥ ሴሰኛም ነው ። የሚያስመሰግነው ሥራ ባይኖረውም ሰው እንዲያሞግሰውና እንዲያመሰግነው ይፈልጋል ። ከንቱ በሆነ ትምክህትና ጉራ ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ የሚጣጣር ሰው ነበር ። ተንኰለኛ፥የደም ሰው ነው ።

ኔሮ ቄሣር ከመሆኑ በፊት በሮሜ ክርስቲያኖች ነበሩ ። ባለ ሥልጣኖች ግን አያስቸግሩአቸውም ነበር ። በ፷፬ ዓ.ም. ይህ ሁኔታ ተለወጠ ። ለውጡንም ያመጣው ታሪክ እንዲህ ነው ።

### ሮሜ ተቃጠለች ።

በሐምሌ ወር በ፷፬ ዓ. ም. ከሮሜ ከተማ አንድ ትልቅ ክፍል በእሳት ተያይዞ ተደመሰሰ ። በትልቁ ቃጠሎ ውስጥ ብዙዎች ሰዎች ሕይወታቸውን አጡ ። ቤታቸውም ተቃጥሎባቸው የሚኖሩበትን ስፍራ ያጡት በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ናቸው ። ቃጠሎው በጣም ኃይ ለኛ ከመሆኑ የተነሣ እስከ ዘጠኝ ቀን እየነደደ የሰውን ንብረት ይበላ ነበር ።

ሕዝቡም በደረሰበት ጉዳት ሁሉ አለቀሰ ። ከማል ቀሱም በላይ ሳያጉረመርምም አልቀረም ። በከተማችን ላይ እሳት የለኰሰባት ሰው ይኖር ይሆን? እያሉ ይጠ ያየቁ ጀመር ። በዚህም መካከል ፡— እሳቱን ያነደደብን ሌላ ሳይሆን ኔሮ ነው የሚል ወሬ ይወራ ጀመር ። በሕዝ

ቡም ግምት ኔሮ ይህንን ለማድረግ የተነሣው ደሳሳ መኖሪያዎችን በማጥፋትና የተሻሉትን ሕንፃዎች በማሳነፅ የከተማይቱን መልክ ለማሳመር እንዲመቸው ነው። ከዚህም ሌላ ፡— የራሱን ቤተ መንግሥት ግቢውንም ለማስፋት ቦታ እንዲያገኝ ነው የሚል ሐሜት ተፈጠረ።

ወሬው በቶሎ ተሰራጨ ። ከተማችንን በእሳት ያያያዘው ኔሮ ነው እየተባለ ተከታዩ ነገር ብስጭት ሆነ ።

## ኔሮ የክርስቲያኖች ጥፋት ነው አለ ።

ምን ይሻላል? ኔሮ በሐሳብ ተጨነቀ ። ከተጠረጠርሁበት ነገር ራሴን ነጻ ማድረግ ያስፈልገኛል ብሎ ተነሣ ። ጥፋቱ የሌላ ሰው ነው ብሎ ሕዝቡን ማሳመን ጥሩ ዘዴ ይመስላል በማለት ምን ያደርጋል? በከተማ እሳቱን የለኰሱ ክርስቲያኖች ናቸው የሚለውን የሐሰትን ክስ ሰነዘረባቸው ። ይህም ሰበብ ሆኖ ክርስቲያኖችን ማስያዝ ጀመረ ። ብዙዎችም ተይዘው ለልዩ ልዩ አሠቃቂ አሟሟት አልፈው ተሰጡ ። የከተማ ሕዝብም በማሳደዱ ተካፋይ ሆኖ ክርስቲያኖች ብዙ መከራ አዩ ።

## የታሪክ ጸሐፊው ቃል ።

ከተማይቱ ከተቃጠለች በኋላ ትንሽ ቆይቶ ታሪኩን የጻፈ ታሲቱስ የተባለ የታሪክ ጸሐፊ አለ ። ስለ ሆነው ነገር ፡—

ኔሮ ከተሰማበት ሐሜት ራሱን ለማዳን ሲል ክርስቲያኖች የሚሉአቸውን ሰዎች በዚህ ነገር ጥፋተኞች አድርጎአቸዋል ብሎ ጽፎአል ። ከዚህም የተነሣ ብዙዎች ክርስቲያኖች መታሰራቸውን በመጥቀስ ታሲቱስ ስለ ደረሰባቸው ሥቃይና ሞት እንዲህ ብሎአል ፡—

በመጀመሪያ ክርስቲያኖች ነን ብለው ያመኑት ተያዙ ። እነርሱም በተናገሩት ቃል ተመርተው ሌሎችንም ለማግኘት ቻሉ ። የተያዙም በጣም የበዙ ናቸው ። ቢመረምሩአቸው ግን ከተማይቱን ያቃጠሉ እነርሱ ናቸው ለሚለው ክስ ማስረጃ አልተገኘም ።

ነገር ግን የተወራባቸው ነገር ከእውነት የተለየ ሆኖ ቢገኝም ክርስቲያኖች በአረማውያን ሥራ ተካፋይነት የሌላቸው በመሆናቸው እንደ ሰው ጠላት ይቈጠሩ ነበር ። ስለዚህ ኔሮ ባስጀመረው ስደት መካከል ያዩት መከራ ብዙ ነው ።

ታሲቱስ አሠቃቂ ስለ ሆነው አሟሟታቸው እን ዲህ ብሎ ጽፎአል ፡— እነርሱን መግደል ብቻ በቂ መስሎ አልታየም ። በልዩ ልዩ መንገድ ይጫወቱባቸው ነበር ። የአውሬዎችን ቆዳ በማልበስ በውሾች ተቦጫጭቀው እንዲያልቁ ያደርጉ ነበር ። በመስቀሎች ላይ ተቸነከሩ ። በእሳትም የተቃጠሉ አሉ ። ቀኑ አልፎ ጨለማ ከሆነ በኋላ ሰውነታቸው በእሳት ያበራ ነበር ። ኔሮ ለዚህ ትርእይት የራሱን ግቢ ከፍቶ በሕዝቡ መካከል ሲመላለስ ይታይ ነበር ።

ኔሮ የክርስቲያኖችን ሥቃይና ሞት የተመለከተው በደስታ ነው ። የደም ሰው ነውና የሰውን ደም ለማየት ይወድዳል ። ያልተማሩት አረማውያን ሳይቀሩ ብዙዎች ሰዎች እስኪያዝኑ ድረስ ክርስቲያኖችን አሠቃያቸው ።

ይህን ያህል ሰው ሥቃይ በሞላበት አሟሟት መሞቱ ዓላማው የአንድ ሰው ክፉ ምኞት ለማርካት ብቻ እንጂ ለኅብረተ ሰቡ አንዳች ጥቅም ለማስገኘት አለመሆኑን ብዙዎች ተመልካቾች ተገነዘቡ ።

## የጴጥሮስና የጳውሎስ ሞት ።

የቤተ ክርስቲያን አፈ ታሪክ እንደሚተርክልን ሐዋርያው ጴጥሮስም ጳውሎስም ሁለቱም ኔሮ ቄሣር በነበረበት ጊዜ በሮሜ በሰማዕትነት ሞቱ ። የሞቱት በ፷፯ ዓ.ም. ነው የሚል ታሪክ አለ ። አንዳንዶች ሊቃውንት ግን ሁለቱ ሐዋርያት ሕይወታቸውን ስለ ክርስቶስ የሠውት ኔሮ በ፷፬ ዓ.ም. ባስጀመረው ስደት ጊዜ ሳይሆን አይቀርም ይላሉ ።

ጌታ ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ከሐዋርያት ጋር ተገናኝቶ ጴጥሮስ በሰማዕትነት እንደሚሞት አመልክቶ ነበር ። እውነት ፣ እውነት እልሃለሁ ፣ አንተ ጐልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር ፤ ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ ፣ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል አለው ። በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን አለ ። ይህንም ብሎ ፡— ተከተለኝ አለው የሚል ታሪክ ተጽፎለታል ። ዮሐ. ፳፩ ፣ ፲፰—፲፱ ።

በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ ፣ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል የሚሉት ቃላት ጴጥሮስ በወንጌል ምክንያት ሕይወቱን እንደ ሚሠዋ የሚያመለክቱ ይመስላሉ ።

አሟሟቱን የሚጠቅስ ከዚህ ጋር የተያያዘ አፈ ታሪክ አለ ። እንዲህ የሚል ነው ፦

ጴጥሮስ በሮሜ ከተማ ታስሮ ነበር ። ከወኅኒ ቤት ግን አምልጦ ሸሸ ። በመንገድ ላይ ሳለ ኢየሱስ መስ ቀል ሲሸከም ታየው ። ጴጥሮስም ቆም አለና ጌታ ሆይ ፣ ወዴት ትሄዳለህ? ብሎ ጠየቀው ። ኢየሱስም ፦ ሁለተኛ ለመሰቀል ወደ ሮሜ መሄዴ ነው ብሎ መለሰለት ።

ጴጥሮስ ይህንን በሰማ ጊዜ የሕሊና ወቀሳ ተሰም ቶት ወደ ሮሜ ተመለሰ ። ከዚያም ክርስቲያኖችን ለሚያ ሳድዱት ሰዎች እጅ ሰጠና ተሰቅሎ እንዲሞት ተፈረ ደበት ይባላል ።

ይህ ታሪክ በመጽሐፍ ያልተጻፈ አፈ ታሪክ ብቻ ቢሆንም ምናልባት እጆችህን ትዘረጋለህ ከሚለው ከኢየ ሱስ ቃል ጋር የሚገናኝ ሊሆን ይችላልና ኢየሱስ ከፍ ብሎ የተጻፈውን ቃል ሊናገር የቻለው ተሰቅሎ መሞ ቱን አስቦ ይሆናል ብለን ልንገምት እንችላለን ።

## ጥያቄዎች ።

፩. ኔሮ ክርስቲያኖችን ከማሳደዱ በፊት ክፉና ከንቱ ገገር መሆኑን ምን ምን በመሥራቱ ገለጠ?

፪. ክርስቲያኖችን ለማሳደድ እንዲመቸው ኔሮ ምን የሚል የሐሰት ክስ ሰነዘረባቸው?

፫. ስለ ጴጥሮስና ስለ ጳውሎስ አሟሟት የቤተ ክርስ ቲያን አፈ ታሪክ ምን ይላል?

፬. እኛ ከእነዚያ ከሃይማኖት ጀግኖች ምን ምን ልን ማር እንችላለን?

# በክርስቲያኖችና በአረማውያን መካከል የነበረው ልዩነት እንዴት ነው?

## ሃይማኖታቸውን በሥራ ተረጐሙት ።

ከፍ ብለን እንደ ተመለከትነው የሮሜ ክርስቲያኖች ተሰድደው በብዛት የተገደሉት በቋማር ከተማ ላይ እሳት ያነደዱባት እነርሱ ናቸው የሚል የሐሰት ክስ ስለ ተሰነዘረባቸው ነው ።

የጥንት ዘመን ክርስቲያኖች ግን ባላመነው ሕዝብ መካከል እንደ ጠላት የተቈጠሩት በዚህ ምክንያት ብቻ አይደለም ። አረማውያን የጠሉአቸው በልዩ ልዩ ምክንያት ነው ። ይኸውም ክርስቲያኖች ሃይማኖታቸውን በሥራ ለመተርጐም የተጉና የተጣጣሩ በመሆናቸው ነው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈላቸው መልእክት ፤— በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ የሚል ምክር አለ ። ሮሜ ፲፪ ፤ ፪ ። ክርስቲያኖች ይህን ምክር አልረሱትም ። ስለዚህ በሥራቸው ፣ በአካሄዳቸውም ሁሉ ዓለም የተባሉትን ያላመኑትን ሰዎች እንዳይመስሉአቸው ይጠነቀቁ ነበር ። ነቢያት ፣ ሐዋርያትም ጌታ ኢየሱስ ራሱም ባስተማሩአቸው መሠረት በቃል በሥራም ካላመኑ ሰዎች የተለዩ ለመሆን ሞከሩ ።

የሮሜ መንግሥት ክርስቲያኖች እውነተኞች የክርስቶስ ተከታዮች እንዲሆኑ በብዙ ረገድ ከአሕዛብ ልማድና ባህል መለየት አስፈላጊ ሆኖ አገኙት ። ይህም ቀጥሎ በሚገኙት ነጥቦች እንደ ተገለጠ ነው ።

## ፩ ፤ ክርስቲያኖች ሌሎች አማልክትን አያመልኩም ።

አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ መኖሩን ስለሚያምኑ ለሮሜ መንግሥት አማልክት አይሰግዱም ነበር ። በዚህ ምክንያት ያልተማሩት አረማውያን ጠሉአቸው ። አሕዛብ እንዳመኑበት ባለፉት ዘመናት የሮሜ ወታደሮች ጠላትን ለመዋጋት በሚሄዱበት ቍጥር ድል አድራጊዎች ያደረጉአቸው የሮማውያን አማልክት

ናቸው ። እስከ ዛሬ መንግሥታችንን የጠበቁት ዩኖ ፣ ማርስ ፣ ቬኑስ ሌሎቹም የእኛ አማልክት ሁሉ አይደ ሉምን የሚል እምነት ነበራቸው ። ክርስቲያኖች ግን ይህን አያምኑም ። ወደ ሮማውያንም አማልክት ቤተ መቅደሶች አይሄዱም ።

በዚህ ብቻ አልተወሰኑም ። ክርስቲያኖች በስብከ ታቸው የአማልክትን እምነት ለማፍረስ የተነሡ ሆነው ተገኙ ። አረማውያን የጠሉት ስብከት ነው ። የአማልክት አምልኮ ቢፈርስና ቢቀር መንግሥታችን ምን ይሆናል? መውደቅ አይደርስበትም? እያሉ ያስቡ ነበር ።

ክርስቲያኖች የመንግሥትን አማልክት ስለ ናቁ እንደ መንግሥት ጠላቶች ተቈጠሩ ። እንዲያውም የሰው ጠላት ሁሉ እነዚህ ናቸው እየተባሉ ይነቀፉ ነበር።

## ፪ ፤ ሰው የሚድነው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ይሉ ነበር ።

በሮሜ መንግሥት ውስጥ ብዙ ልዩ ልዩ ሃይማ ኖት ነበር ። መንግሥትም ሰው የወደደውን ሃይማኖት እንዲጠብቅ ይፈቅድለት ነበር ። እያንዳንዱ ፦ ለምን እንደዚህ ትሆናለህ? ተብሎ ሳይጠየቅ የተሻለ አድርጎ የመረጠውን አምላክ ሊያመልከው ይችላል ።

ክርስቲያኖች ግን ተሰደዱ ። ብዙ መከራ አዩ ። ስለምን?

በጋለ መንፈስ በሰው ሁሉ መካከል እምነታቸውን ለማስተማርና ለማስራጨት ስለ ተነሡ ነው ። በስብከ ታቸው ፦ የአማልክት እምነት የተሳሳተ ነው ፣ እው ነተኛውን ሃይማኖት የተማርን እኛ ብቻ ነን ፣ ኢየሱስ ብቻ ነው ሰውን ለማዳን የሚችል ፣ ስለዚህ ከነበራችሁ በት አምልኮ ተመለሱና በኢየሱስ እመኑ ፣ እውነት ሕይወትም መንገድም እርሱ ነው እያሉ ያስተምሩ ነበር። የሐዋ. ፬ ፣ ፲፪ ።

አሕዛብም ስብከታቸውን ሰምተው ፦ እነዚህ ሰዎች ሃይማኖታችንን ለማቋሸሽ የተነሡት በምን ምክንያት ነው በማለት ተበሳጩ ።

## ፫ ፤ ለቄሣር ሐውልት አይሰግዱም።

በብዙዎች የጣዖት አምልኮ መቅደሶች ውስጥ የቄሣርን ሐውልት ማቆም የተለመደ ሆነ ። ሰዎችም ቄሣርን ሊያከብሩት ሲሉ በሐውልቱ ፊት ዕጣን ያጥኑ ነበር ። በዘመን ብዛት ይህ ልማድ ልክ እንደ ጣዖት አምልኮ ሆነ ።

የመጀመሪያዎች ቄሣሮች አማልክት ነን ባይሉም ሰዎች በተጠቀሰው መንገድ እንዲያከብሩአቸው ይፈቅዱሉ ። በ፹፩ ዓ. ም. የነገሠው ዶሚቲያኑስ ግን ከዚህ አልፎ በግልጽ ፡— ጌታና አምላክ እኔ ነኝ ብሎ ራሱን ሾመ ። ሰዎችም እንደ አምላክ አድርገው እንዲሰግዱለት ተፈለገባቸው ። የማይሰግዱለትም ቢኖሩ እንደ ከሐዲና እንደ መንግሥት ጠላት ይቈጠሩ ነበር ። በቄሣር የሚል መሐላም የተለመደ ሆነና ልክ እንደ አምላክ መቈጠሩን ያሳያል ።

ክርስቲያኖች ግን ፡— ሌሎች አማልክት በፊትህ አይኑሩህ የሚለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በማስታወስ ፡— ለቄሣር አንሰግድም አሉ ። ሰው ነው ፤ አምላክም አይደለም ። ነገር ግን ፡— ለቄሣር አልሰግድም ማለት እንደ ወንጀል የሚቈጠርባቸው ስለ ሆነ የክርስቲያኖች አቋም በላያቸው ላይ መከራ ማስከተሉ አልቀረም ።

## ፬ ፤ በበዓላትም ተካፋይነት አልነበራቸውም ።

የሕዝቡ በዓላት በሚከበሩበት ወቅት በሥነ ሥርዓቱ ላይ የሮማውያንን አማልክት በልዩ ልዩ ነገር ያከብሩአቸው ስለ ነበር ክርስቲያኖች አብረው ለማክበር አይፈልጉም ።

## ፭ ፤ ከመጥፎ ጨዋታ ይርቁ ነበር ።

የዘመኑ የስፖርት ውድድር በጣም አስቀያሚ መልክ ነበረው ። ለምሳሌ ሁለት ጀግኖች የጦር መሣሪያ ይዘው በአደባባይ በብዙ ተመልካች ፊት እንዲጋደሉ ያደርጋሉ ። አንደኛው ሌላውን ወግቶ እስኪገድለው ድረስ ጨዋታው ይቀጥላል ። አሸናፊ ሆኖ ለሚወ

ጣውም በብዙ ወካታ ይጨበጨብለታል ። ይህን የመ ሰለ ሌላም ርዥስ ጨዋታ አላቸው ።

ክርስቲያኖች ይህን የመሰለ የስፖርት ውድድር እያዩ ፡— ኃጢአት ነው ፣ እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ አይወድድም በማለት ከማየት ይርቁ ነበር ። አረማውያን ም በበኩላቸው ፡— ለምን እንደ እኛ ጨዋታቸውን ለማ የት አትሄዱም እያሉ ይንቁአቸው ነበር ።

## ፯ ፤ በስውር ለመሰብሰባቸው አረማውያን መጥፎ ትርጒም ሰጡ ።

ክርስቲያኖች ከመጀመሪያው ጊዜ አንሥቶ በሃይ ማኖታቸው ምክንያት ይሰደዱ ስለ ነበር ስውር በሆነ ቦታ ለጸሎት ለቅዱስ ቊርባንም ለጥምቀትም መሰብሰብ ግዴታ ሆነባቸው ። ይህም በቀን ብዛት የክርስቲያንን ሃይማኖትና ሥርዓት ባለወቁ አረማውያን መካከል ለልዩ ልዩ ዓይነት ሐሜትና ከእውነት ለተለየ ወሬ ምክንያት ሆነባቸው ።

እነዚህ ሰዎች በሌሊት በሰው ቤት የሚሰበሰቡት ምን ምን ለማድረግ ነው? የነውርን ሥራ ለመሥራት አይደለምን? የሚል ሐሜትና ጥርጥር ተፈጠረ ።

ሌባ ሰው ሁሉ የሚሰርቅ ይመስለዋል እንደ ተባለ የክርስቲያኖችን የእርስ በርስ ፍቅር አረማውያን እየተ መለከቱ ፡— በድብቅ የሚገናኙት ለሌላ ሳይሆን ለዝ ሙት ሥራ ነው እያሉ ያወሩ ነበር ። ወይም ደግሞ ለቅዱስ ቊርባን መሰብሰባቸውን ሰምተው ነገሩ ምን እንደ ሆነ ሳይገባቸው ቢቀር ፣ ስውር በሆነ ስፍራ ... ደ ብቀው ሲሰበሰቡ ሕፃናትን አርደው ይበላሉ ይሉ ነበር ።

መነሾውም ከዬት እንደ ሆነ የማይታወቅ ሌላ ሌላ ወሬ ይወራባቸው ነበር ። ለምሳሌ ፣ የክርስቲያኖች አምላክ የአህያ ጭንቅላት አለው ፣ እነርሱም የሚሰግዱት ለአህያ ጭንቅላት ነው እያሉ አሕዛብ ያፌዙባቸው ነበር ።

ይህ ሐሰት ሁሉ ሊነዛ የቻለው ካለማወቅ የተነሣ መሆኑ ግልጽ ነው ። ተራ ሰው ሆነ ባለሥልጣን ክርስ ቲያኖችን በሚገባ አያውቅም ። ስለዚህ ከክፉ ሥራ ቢር ቁም ፣ ክፉዎች ናቸው ፣ ልክስክሶች ፣ ወራዳ ሕዝብ ፣ መጥፋት የሚገባቸው ናቸው የሚል ብስጭት በአረማ ውያን መካከል ይሰማ ነበር ።

## ፺፤ በተፈጥሮ አደጋ ጊዜ፡— የክርስቲያኖች ጥፋት ነው ይባል ነበር ።

በሕዝብ መካከል ክርስቲያኖችን ገለልተኛ የሚያ ደርጋቸው ሌላ ነገርም አለ ። ዝናብ ቢጠፋ የአገር ሕዝብም ከእህል ማነስ የተነሣ ቢራብ የተጠቃ እንደ ሆነ ፣ ወይም ደግሞ የመሬት መናወጥ ከተማዎችንና መንደሮችን አፈራርሶ ቢገኝ ፤ ቸነፈር ወይም ሌላ ዓይነት ተላላፊ በሽታ ሰውን የጨረሰ እንደ ሆነ የዘመኑ አረ ማዊ ሕዝብ ለደረሰባቸው ጉዳት ምክንያቱን ሲፈልጉ፡— ጥፋቱ የክርስቲያኖች ነው እያሉ ብዙ ጊዜ ይተቹባ ቸው ነበር ።

አማልክት ተቈጥተው ይህንን አደጋ ሁሉ አመጡ ብን ፤ ይኸውም የማያመልኩአቸው ሰዎች በመካከላችን በመኖራቸው ነው ፤ ክርስቲያኖች ናቸው የማያመልኩአ ቸው እያሉ ይጮኹባቸው ነበር ።

ይህም አልፎ አልፎ ለመሰደዳቸው ምክንያት ሆነ ማለት ነው ።

እንደ እውነቱ የሆነ እንደ ሆነ ግን ክርስቲያኖች በአገር ላይ ጉዳትን የሚያመጡ ሰዎች አልነበሩም ። አገርን የጠቀሙ እነርሱ ናቸው ። እንደምን ቢሉ ፣ በኑሮ በአካሄድም ከአረማዊው ሕዝብ በጣም የተሻሉ በመሆናቸው ነው ። ለዚህም የሕይወታቸው ታሪክ ማስረጃ ሊሆን ይችላል ።

በጉዳዩ ላይ አንድ ጥንታዊ ደራሲ የጻፈው ቃል እውነተኛ ነው ።

### ዲዮግኔቱስ ስለ ክርስቲያኖች የጻፈው ቃል ። ከሦስተኛው መቶ ዘመን ።

ክርስቲያኖች በኑሮ ልማድ ሆነ በቋንቋ ፣ በመኖሪ ያም ዓይነት ከሌሎች ሰዎች የተለዩ አይደሉም ። አኗ ኗራቸው ፣ መኖሪያቸውም ሌሎች ሰዎች እንደ ለመዱት ነው ።

ቢሆንም አካሄዳቸው ኑሮአቸውም ልዩ ነው ። በትውልድ አገራቸው ቢኖሩም ፣ በሁሉም ነገር ቢተባ በሩም በአቀማመጣቸው ጉብኝዎችና እንግዶች ይመስ ላሉ ። ተጋብተው ልጆችን ይወልዳሉ ። ነገር ግን ወደ

ውጭ አይጥሉአቸውም ። በሥጋ ነው ያሉት ። እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን አይኖሩም ። ቤታቸው በምድር ላይ ነው ። አገራቸው ግን በሰማይ ነው ።

ለሕግ ይታዘዛሉ ። አካሄዳቸው ግን በሕግ ከተፈለ ገባቸው በላይ ነው ። ሰውን ሁሉ ይወዳሉ ። ሰው ሁሉም ያሳድዳቸዋል ። ሕዝብ አያውቃቸውም ። ቢሆንም ይፈር ድባቸዋል ። ድሆች ናቸው ፤ ብዙዎችንም ባለጠጎች ያደ ርጋሉ ። ችጋረኞች ናቸው ፤ ቢሆኑም ሁሉም ነገር በት ርፍ አላቸው ። ያፌዙባቸዋል ፤ እነርሱ ግን ይመርቃሉ ። ሰዎች ይንቁአቸዋል ፤ እነርሱ ግን ሰውን ያከብራሉ ። የዲዮግኔቱስ ቃል እስከዚህ ድረስ ነው ።

የክርስቲያን ሥራና ኑሮ ይህን ያህል የታረመና የተጠበቀ መሆኑ ሲታወቅ ለምን ተሰደደ? ለሞት የሚያደርስ ክፉ ሥራ ካልሠራ ሕይወቱን ለምን አጣ?

ለዚህ ጥያቄ ጌታ ኢየሱስ ፡— ስለ ስሜ በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ብሎ የተናገረው ቃል መልስ ሊሆን ይችላል ። ማቴ. ፳፬ ፣ ፱ ።

ልዩ ልዩ ክፉ ነገር ቢወራበትም ፣ በልዩ ልዩ ነገር ቢከሰስም ክርስቲያን ባላመኑት ሰዎች መካከል ለመጠ ላቱ የመጨረሻው ምክንያት በኢየሱስ ክርስቶስ በማ መኑ ነው ።

## ጥያቄዎች ።

፩. ክርስቲያኖች በሮማውያን መካከል እንደ መንግ ሥት ጠላቶች ይቈጠሩ የነበር ከምን የተነሣ ነው?
፪. በሮማውያን መንግሥት ክርስቲያን ያልሆነው ሕዝብ ምን በማድረግ ቄሣርን ያከብረው ነበር?
፫. የክርስቲያኖች ስብከትና ምስክርነት በዘመኑ ሕዝብ መካከል ለምን የተጠላ ሆነ?
፬. የሮሚ መንግሥት አረማውያን ስለ ክርስቲያኖች ያሰራጩት የሐሰት ወሬ ምን ምን የሚል ነበር ?
፭. በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ ፳፬ ቍጥር ፱ የተጻ ፈው ቃል ለክርስቲያኖች መሰደድ የጠቀሰው ምክንያት ምን የሚል ነው?

## ምዕራፍ አምስት ።

# ታላላቅ ስደቶችና ሰማዕታት ።

### ፩ ፤ በዶሚቲያኑስ ዘመነ መንግሥት ስለ ሆነው ስደት ።

#### ሀ ፣ ጌታ ማን ነው? ቄሣር ወይስ እግዚአብሔር?

ከ፹፩ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ፺፮ ዓ.ም. ድረስ በሮማ መንግሥት ቄሣር የነበረው ዶሚቲያኑስ ክርስቲያኖችን የሚጠላ ከመሆኑም በላይ ራሱን እንደ አምላክ ይቈጥር ነበር ። ጌታና እግዚአብሔር እኔ ነኝ ማለቱን ከዚህ በፊት ሰምተናል ። ሰዎችም እንዲያመልኩትና ስግደት እንዲያደርጉለት ያስገድዳቸው ነበር ። ለእርሱ ስግደት ማድረግ የሮማን መንግሥት ሕጉንም እንደ ማክበርና እንደ መቀበል የሚቈጠር ነገር ነው ።

ከዚህ በፊት እንዳየነው ለቄሣር ሊሰግድ የማይፈልግ ሰው ቢኖር እንደ ሕግ ተላላፊና እንደ ወንጀለኛ ይቈጠራል ።

ክርስቲያኖች ግን ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይሰግዱም ። ስለዚህ በዶሚቲያኑስ ዘመን መከራ ሳይደርስባቸው አልቀረም ።

ይህ ቄሣር በወንጀል የተከሰሱትን ሰዎች ብዙ ጊዜ ቅጣት የሚወስንባቸው ከትውልድ አገራቸው ተነሥተው ወደ ሩቅ አገር ተሰድደው በዚያ በስደተኝነት እንዲቀመጡ ፍርድ በመስጠት ነበር ።

#### ለ ፣ ዮሐንስ ከጻፈላቸው ሰዎች መካከል መከራ የተቀበሉ አሉ ።

ብዙዎች የታሪክ ሊቃውንት እንደሚያምኑበት ሐዋርያው ዮሐንስ ፍጥሞ በምትባል ደሴት ተቀምጠ ክርስቶስ በገለጠለት መሠረት ለትንሽዋ እስያ አብያተ ክርስቲያናት ሰባቱን መልእክቶች የጻፈው ዶሚቲያኑስ ክርስቲያኖችን ባሳደደበት ጊዜ ነው ። ዮሐንስ ራሱም በብቸኝነት በዚህች ደሴት የተቀመጠው በወንጌል ..ክንያት ስደተኛ ሆኖ ነው የሚል እምነት አለ ። ራእይ ፩ ፣ ፱ ፤ ፪—፫ ።

በዘመኑ ክርስቲያኖች ይሰደዱ እንደ ነበር ከዮሐ ንስ ራእይ መጽሐፍ ልንረዳ እንችላለን ። ለምሳሌ በጴ ርጋሞን ቤት ክርስቲያን በሰማዕትነት የሞተ አንቲጳስ የተባለ ሰው መኖሩ በራእይ ፪ ፣ ፲፫ ተጠቅሶአል ።

ዮሐንስ ለሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንም ፦ ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ ። እነሆ ፣ እንድት ፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው ፣ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላ ችሁ ። እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ ብሎ ጽፎአል ። ራእይ ፪ ፣ ፲ ።

እነዚህ ቃላት እንደሚያስረዱን ክርስቲያኖች በዘ መኑ ይሰደዱ ነበር ።

## ፪ ፤ እግናቲዩስ ።

### ሀ ፣ ዘመኑና አገልግሎቱ ።

ከ፺፰ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ፩፻፲፯ ዓ.ም. ድረስ በሮሚ ቄሣር የነበረው ትራያኑስ ነው ። በዘመነ መንግ ሥቱ ብዙ ክርስቲያኖች በእምነታቸው ምክንያት ተከ ስሰው ለባለ ሥልጣን አልፈው ተሰጡ ። የሞት ፍርድም ተበየነባቸው ። ከእነርሱም አንዱ እግናቲዩስ የተባለው ስመ ጥሩ ጳጳስ ነው ።

እግናቲዩስ የእግዚአብሔርን ቃል በመስበክ ቤተ ክርስቲያንን ያገለገላት አንጾኪያ በተባለችው ከተማ ነው ። ታማኝ አገልጋይ ከመሆኑ የተነሣ የቤተ ክርስ ቲያኒቱ ጳጳስ ሆነ ።

በ፩፻፲፯ ዓ.ም. ትራያኑስ ቄሣር ለአገር ጕብኝት ወደ አንጾኪያ መጣ ። በዚያን ጊዜ ለከተማው ሕዝብ፦ ለአማልክት መሥዋዕት ለማቅረብ የማይፈልግ ሁሉ ብርቱ ቅጣት ይደርስበታል ሲል ማስታወቂያ አወጣ ።

### ለ ፡ ተይዞ ተፈረደበት ።

እግናቲዩስ የማስታወቂያውን ቃል ሰምቶ ፦ ለአማልክት የምሠዋው ነገር የለኝም በማለት የቄሣርን ትእዛዝ ተቃወመ ። በነገሩም ተይዞ ተከሰሰ ። ጳጳሱም የሚመጣበትን ነገር ሳይፈራ በግልጽ ፦ ክርስቲያን ነኝ ብሎ አመነ ።

ትራያኑስም ወደ ሮሚ ተሰድዶ በአንበሶች ተገነ ጣጥሎ እንዲሞት ፈረደበት ። ወዲያውም እጆቹ በሰንሰ

ለት ታስረው በአሥር ወታደሮች ተጠብቆ በመርከብ ወደ ሮሜ እንዲጓዝ ተገደደ ።

መንገደኞች በሰምርኔስ በኩል ስላለፉ እግናቲዩስ በዚያ ከአንድ ሌላ ስመ ጥሩ ክርስቲያን ጋር እንዲገናኝ ተፈቀደለት ። እርሱም ፖሊካርጵ ነው ። በወዳጅነት በፍቅር ያደረጉት የሐሳብ መለዋወጥ ሁሉ እግናቲዩስን እንዳጽናናውና እንዳበረታታው ለማመን እንችላለን ። በዚያም በቆየበት ወቅት ለልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ደብዳቤ ለመጻፍ ጊዜ አገኘ ።

ወደ ሮሜ ቤተ ክርስቲያንም መልእክት አስተላለፈ። ይህ መልእክት እስከ ዛሬ ድረስ ተጠብቆአል ። እንዲህ የሚል ቃል ይገኝበታል ።

## ሐ ፣ ወደ ሮሜ የላከው መልእክት ።

በሰውነቴም በልቤም ኃይል እንዳገኝ ጸልዩልኝ ። በእርግጥ ክርስቲያን ሆኖ መገኘት እንጂ በስም ብቻ ክርስቲያን መባል አይበቃኝምና በአፍ ብቻ ሳይሆን በእውነት ፈቃደኛ መሆን ያስፈልገኛል ። እውነተኛ ክርስትና ብርቱ በመሆን የሚገለጥ ነው እንጂ በዝ ምታ አይደለም ።

እናንተ ካልከለከላችሁኝ ለአምላኬ ለመሞት ዝግጁ መሆኔን በሰው ሁሉ ፊት እመሰክራለሁ ። ስለዚህ ባላ ገባብ እንዳታስቡልኝ እለምናችኋለሁ ። ወደ እግዚአብ ሔር እንድደርስ የአራዊት ጉርሻ ልሁን ። የእግዚአብ ሔር የስንዴ ቅንጣት ነኝ ። የአራዊትም ጥርሶች ቢፈ ጩኝ ለኢየሱስ ክርስቶስ ንጹሕ እንጀራ እሆናለሁ ።

ካንቀላፋሁ በኋላ ለማንም ሰው ሸክም እንዳልሆን ሰውነቴ በሙሉ ይለቅ ። አራዊት መቃብሬ እንዲሆኑ ይምጡብኝ ። እንዲይዙኝ እናንተ አነሣሱአቸው ። ብመ ሞቴ በክርስቶስ ነጻነትን አገኛለሁ ፣ በእርሱም ነጻ ሆኜ እነሣለሁ ። በጊዜአዊ እስራት የታሰርሁ ሆኜ እገኛለሁ። ስለዚህ አንዳች ምድራዊና አላፊ ነገር መመኘት እንደ ማያስፈልገኝ ተረድቼአለሁ ።

ገና በመንገድ ላይ ሳለሁ በባሕር በየብስም ሌትና ቀን አሁንም ከአራዊት ጋር እየታገልሁ ነኝ ። የአሥር ነብሮች ቁራኛ ነኝ ፣ ማለት ከወታደሮች ጋር ነው ያለ ሁት ። እነርሱም መልካም ነገር ቢያደርጉላቸው የባሰ

ውን ከፋት የሚያሳዩ ናቸው ። ይሁንና በእነርሱ ማጉላላት ልምምድ አገኛለሁ ። በዚህ ግን እጸድቃለሁ ማለቴ አይደለም ።

እውነተኛ ደቀ መዝሙር መሆንን የጀመርሁ አሁን ነው ። የሚታይ ሆነ የማይታይም ማንም ሰው በምቀኝነት ዓይን አይመልከተኝ ። ልድረስ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ። እሳት ፣ መስቀል ፣ የአውሬ ብዛት ፣ መጨፍጨፍ ፣ የአጥንቶቼ መበታተን ፣ የብልቶቼ መሰባበር ፣ የሰውነቴ መጨፍለቅ ሁሉ ፣ የሰይጣን ሥቃይ ሁሉ ይምጣብኝ ። ብቻ ፣ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ልድረስ ።

የመልእክቱ ቃል እስከዚህ ድረስ ነው ።

መ ፣ በሮሜ በአውሬ ተበልቶ ስለ መሞቱ ።

በወታደሮች የተጠበቀው እስረኛ እግናቲዩስ ወደ ሮሜ ከደረሰ በኋላ ብዙ ጊዜ ሳይቆይ ወደ አደባባይ ቲያትር ተወሰደ ። በዚያም ራብ ያጠቃቸው አውሬዎች ይጠብቁታል ። አስፈሪውንም ትርእይት ለመመልከት ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦአል ።

የአራዊት ቤት ተከፍቶ ተለቀቁበት ። በአንድ አፍታም ሰውነቱን በጫጭቀው ጨረሱት ። በአደባባዩም መካከል የቀረው ጥቂት የተበታተነ አጥንት ብቻ ነው ። ክርስቲያኖች ግን አጥንቱን ሰብስበው መታሰቢያውን ለማክበር ሲሉ ወደ አንጾኪያ ወሰዱት ።ከዚያም አኖሩት።

እግናቲዩስ የተመኘውን ፣ በናፍቆትም ይጠባበቅ የነበረውን ሞት አገኘ ። እስከ ሞት ድረስ የታመነ ሆነ። የሕይወትንም አክሊል ተቀዳጀ ።

## ፪ ፣ ፖሊካርጵ ።

ሀ ፣ ዘመኑና አገልግሎቱ ።

ፖሊካርጵ የሐዋርያው ዮሐንስ ወዳጅ ነበር ፣ ከእርሱም ተምሮአል ። በቀጥታ ከዮሐንስ ስለ ኢየሱስና ስለ ትምህርቱ ብዙ ነገር የመስማትና የመማር ዕድል ነበረው ማለት ነው ።

የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማርና በመስበክ አገልግሎት ያበረከተው በትንሽዋ እስያ በሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ነው ። ታማኝና ትጉ ክርስቲያን ከመሆኑ የተ ነሣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ሽማግሌ ወይም ጳጳስ ሆኖ ነበር ።

ለ ፥ ስደት ተጀመረ ፥ ወጣቱም ገርማኒኩስ ሞተ ።

በ፩፻፶፭ ዓ.ም. በሰምርኔስ ከተማ በክርስቲያኖች ላይ ስደት ተጀመረ ። በዚያን ጊዜ በሮሜ መንግሥት ቁጣር የነበረው አቴኒዩስ ጲዮስ ነው ። ዘመነ መንግሥ ቱም ከ፩፻፴፯ ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ፩፻፷፩ ዓ.ም. ድረስ ነው ።

የሰምርኔስ አረማውያን በክርስቲያኖች ላይ በተነ ሡበት ጊዜ የመጀመሪያ ሆኖ የተያዘው ገርማኒኩስ የተባለ ወጣት ነው ። የሞት ፍርድ ተፈርዶበት አንበሳ እንዲገድለው ወደ ቲያትር አደባባይ ወሰዱት ። ገዢው ግን ወጣትነቱን ተመልክቶ አዘነለትና ወደሚሞትበት ስፍራ ከደረሰ በኋላ እንኳን ክርስቶስን እንዲክደው ያባብለው ነበር ። ገርማኒኩስ ግን ሊሰማው አልቻለምና እንዲጠጣው የተመደበለትን የሞትን ጽዋ ሳይፈራው አንበሳው ወደ ነበረበት ስፍራ ገሰገሰ ። ከመቅጽበትም ኃይለኛው አውሬ ገነጣጥሎ ጣለው ።

ሐ ፤ ፖሊካርጵም ይምጣ ብለው ጮኹ ።

ተመልካቹ ሕዝብ ያለ ፍርሃት መሞቱን ባየ ጊዜ በበለጠ በንዴትና በደም ጥማት ተያዘና ፥— አማልክትን የማይፈሩ ይጥፉ ፥ ፖሊካርጵም ይምጣ ብለው ጩኸታ ቸውን ለቀቁ ።

ክርስቲያኖች ይህን ሲሰሙ ፖሊካርጵ ተይዞ እን ዳይሞትባቸው ከከተማ ወጣ ብሎ እንዲሸሸ መከሩት ። በመጀመሪያ ኰብልሎ መሄድ አስፈላጊ መስሎ አልታ የውምና በከተማ ውስጥ ለመቆየት አሰበ ። በመጨረሻ ግን አጥብቀው ስለ ለመኑት እሺ አላቸውና ከከተማ ወጥቶ በአንድ አራሽ ሰው ቤት ውስጥ ተደበቀ ። ከዚ ያም ከጥቂት ክርስቲያኖች ወንድማማች ጋር ሆኖ ሌትና

ቀን በጸሎት ይተጋ ነበር ። እንደ ወትሮው ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰላም እንዲወርድላቸው ይጸልይ ነበር ።

ከመያዙ ሦስት ቀን ቀደም ብሎ በሌሊት ተኝቶ ሳለ የተንተራሰበት ትራስ በድንገት በእሳት ተያይዞ ተቃጥሎ ሲጠፋ በሕልም ታየው ። ወዲያውም የሕል ሙን ትርጉም አውቆ ፤— ስለ ክርስቶስ በእሳት ተቃ ጥዬ መሞት እንደሚያስፈልገኝ ተረድቼአለሁ ብሎ ካጠገቡ ለነበሩት ሰዎች ሊነግራቸው ቻለ ።

መ ፡ ተያዘ ።

በዚህ መካከል ጠላቶቹ በየስፍራው ይፈልጉት ነበር ። እንደ ገናም ወዳጆቹ ካለበት ተነሥቶ ወደ ሌላ ስፍራ እንዲሸሽ ለመኑት ። አሳዳጆቹም ተከታትለው መጡ ። በዚያም ምናልባት ያለበትን ቦታ ሊነግሩን ይችላሉ በማለት ሁለት ልጆችን ያዙ ። ከእነርሱም አንዱ ተገርፎ ፖሊካርጵ ወደ ነበረበት ስፍራ መራቸው ። እርሱም በሰላም ተቀበላቸውና ምግብ እንዲያሰናዱላቸው አዘዘ ። ከዚያም በኋላ አንድ ሰዓት በጸሎት እንዲቆይ ፈቃድ ጠየቃቸው ። እነርሱም ፈቀዱለት ።

ከጸለየ በኋላ በአህያ ላይ አስቀምጠውት ወደ ከተማ ወሰዱት ። በመንገድ ላይ ሳሉ አንድ ባለ ሥልጣን ፖሊካርጵን አይቶት በሰረገላው ላይ እንዲወጣ ጋበዘውና ፡— ቄሣር ጌታ ነው ብትልና መሥዋዕት ብታቀርብለት ምን አለበት? በዚህ ራስህን ለማዳን ትችል ነበር ብሎ ሊያባብለው ሞከረ ። ፖሊካርጵ ግን ፡— የተናገርኸውን ነገር ለማድረግ አልችልም ብሎ መለሰለት ።

በዚያን ጊዜ በመንገድ ላይ ከእርሱ ጋር የነበሩት በክፉ ሁኔታ ያስፈራሩት ጀመር ። ከሰረገላውም ላይ ወረወሩት ። እግሩም ክፉኛ ተጐዳ ። ቢሆንም እስከ አደባባይ ድረስ ሊራመድ ቻለ ። በቦታው ብዙ ሕዝብ ይጠባበቀው ነበር ። በፖሊካርጵ ላይ የሚደርስበትን ነገር ለማየት ትልቅ ጕጕት አድሮባቸዋል ። ውካታውም ጩኸቱም ብዙ ነው ።

ሠ ፣ የገዢው ጥያቄ የፖሊካርጵም መልስ ።

በሕዝቡ ፊት ገዢው ፖሊካርጵን ጠርቶት እንዲህ አለው ፡—

ዕድሜህን አስብ ፤ በቄሣር ማል ፤ ተመለስ ፤ አማል ክትን የሚክዱት ይጥፉ በል ።

ፖሊካርጵም በአደባባዩ ዙሪያ የተሰበሰበውን ሕዝብ ተመለከተ ። ወደ ሰማይም አሻቅቦ በእጁ ወደ ሕዝቡ ጠቆመና ትካዜ በሞላበት አንደበት ፡— ክፉ አድራጊዎች ይጥፉ አለ ።

ገዢውም እንደ ገና ፡— ማል ፤ እኔም እለቅሃለሁ ፤ ክርስቶስን እርገም አለው ።

ፖሊካርጵ ግን ፡— ሰማንያ ስድስት ዓመት እርሱን ሳገለግል ቆይቼአለሁ ፣ ክፉ ሥራ ሠርቶብኝ አያውቅም ፤ ያዳነኝን ንጉሤን እንዴት አድርጌ ልሰድበው እችላለሁ? በማለት መለሰለት ።

ገዢውም ፡— ማል በቄሣር አለው ደጋግሞ ።

ፖሊካርጵም ሲመልስለት ፡— በቄሣር ይምላል ብለህ ተስፋ ታደርጋለህ ወይ? እንደማታውቀኝ አድር ገህ ነው የምትጠይቀኝ ። በግልጽ ልንገርህ ፤ ክርስቲያን ነኝ አለው ።

ለሕዝቡ ተናገር አለ ገዢው ።

ከእግዚአብሔር ሹመት ላገኙት ባለ ሥልጣኖችና ገዢዎች የሚገባቸውን አክብሮት እንድናሳያቸው ተምረ ናልና በአንተ ፊት መናገር ተገቢ መስሎ ታይቶኛል ። እነዚህ ግን የመከላከያ ቃሌን መስማት የሚገባቸው አይደሉም አለ ፖሊካርጵ መልሶ ።

አራዊት አሉኝ ፤ ሐሳብህን ካልለወጥህ ለእነርሱ እንድትሆን አደርጋለሁ አለ ገዢው በማስፈራራት ።

ፖሊካርጵም አሁንም ፍንክች ሳይል ፡— ይምጡ ብኝ ፤ ከክፉ ሥራ ወደ ጽድቅ እንጂ ከጥሩ ሥራ ወደ ክፉ መመለስ አያስፈልግም በማለት መለሰለት ።

እሳት እንዲበላህ ለማድረግ እችላለሁ አለ ገዢው።

ፖሊካርጵም ፦ ለአንድ አፍታ ብቻ በሚቆይ፥ ከዚያም በኋላ በሚጠፋ እሳት ታስፈራራኛለህ። ነገር ግን ለክፉዎች የተዘጋጀባቸው ዘለዓለማዊ እሳት፥ ማለት የሚመጣ ፍርድ መኖሩን አታውቅም ሲል መለሰለት።

ንግግራቸው እስከዚህ ነው።

ገዢው በማስፈራራትም በማባበልም ፖሊካርጵ ሐሳቡን እንዲለውጥ ለማድረግ አልቻለም። ፍርድ ከመ ስጠት በቀር ሌላ መንገድ የለውም።

## ፫፥ በጦር ተወግቶ ተቃጠለ።

ፖሊካርጵ ፦ ክርስቲያን ነኝ ብሎ አምኖአል የሚል ቃል ለሕዝቡ ተነገረ።

ይህን በሰሙ ጊዜ ሁሉም በአንድ ድምፅ ፦ በእሳት ተቃጥሎ ይሙት ብለው ጮኹ።

ፍርዱም በዚህ ተወስኖ ፖሊካርጵ ለእሳት በተዘ ጋጀው እንጨትና ጭራሮ ላይ በደስታ ወጣበት። ሰዎቹ በምሰሶ ላይ ሊቸነክሩት ፈለጉ። እርሱ ግን አያስፈል ግም፥ የእሳቱን ነበልባል እንድችለው ኃይል የሚሰጠኝ አምላክ ያለ ችንካር እንድቆም ብርታት ይጨምርልኛል ብሎ ተናገረ።

ይህ ታሪክ የተጻፈበት መጽሐፍ እንደሚተርክልን ግን እሳቱን ካነደዱ በኋላ ሰውነቱን አልነካውም። ስለዚህ አንድ ሰው በጦር ወግቶ ገደለው። ከጉኑም የፈሰሰው ደም እሳቱን አጠፋው። ከሞተ በኋላም እንደ ገና እሳት አንድደው አስከሬኑን አቃጠሉት።

ክርስቲያኖችም አጥንቱን ሰብስበው በክብር ቦታ አኖሩት።

## ፬፥ ዩስቲኑስ። Justin Martyr

ዩስቲኑስ በሁለተኛው መቶ ዘመን ውስጥ የኖረ ታዋቂነት ያለው ክርስቲያን መሪ ነበር። በእውቀቱም የረቀቀ ከመሆኑ የተነሣ የመጀመሪያ ክርስቲያን

ፈላስፋ ተብሎ ተሰይሞአል ። ብዙ መንፈሳዊ መጽሐፍም ጽፎአል ።

በሰማርያ አገር ከአሕዛብ ወገን ተወለደ ። ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ትልቅ የትምህርት ፍላጎት ስላደረበት አዋቂ ለመሆን ተጣጣረ ። እውነትን ለማወቅ እፈልጋለሁ ፣ እውነተኛውን መንገድ ሊያሳየኝ የሚችል ማን ነው? በሚል ሐሳብ እየተመራ ከልዩ ልዩ የፍልስፍና መምህራን ይማር ጀመር ። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ያስተማሩት ነገር ሰው የፈለሰፈው ትምህርት ብቻ በመሆኑ የልቡን ፍላጎት ሊያረካው አልቻለም ።

## ለ ፡ የክርስቲያኑ አዛውንት ምክር ።

ዩስቲኑስ ብዙ መምህራንን ከሞከረ በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን ብቻውን በባሕር ዳር ሲንሸራሸር ሳለ እንደ አጋጣሚ ከአንድ ክርስቲያን አዛውንት ጋር ተገናኘ ። ጭውውትም ጀመሩ ።

ዩስቲኑስ በዚያን ጊዜ ከዚህ ሽማግሌ የሰማው ነገር ሕይወቱን ለወጠው ። ከዚህ በፊት ከልዩ ልዩ መምህራን የሰውን ጥበብ ለመማር ተጣጥሮ ነበር ። ክርስቲያኑ ሽማግሌ ግን የሰው ፍልስፍናና ትምህርት በቂ አለመሆኑን ሊነግረው ቻለ ። እውነትን ለማወቅ ብትፈልግ ከፈላስፋዎች በፊት ይኖሩ የነበሩ የአይሁድ ነቢያት የጻፉትን ነገር ተመልከት አለው ። ስለ እውነት መንገድ እነርሱ አስተምረዋል ። ስለ ክርስቶስም ቀደም ብለው ትንቢት ተናግረዋል ። የትንቢታቸውም ቃል ሁሉ ክርስቶስ በሠራው ሥራ ፍጻሜ አግኝቶአል ሲል ሽማግሌው አስረዳው ።

## ሐ ፡ ክርስቲያን ሆነ ።

ከተነጋገሩ በኋላ ዩስቲኑስና ክርስቲያኑ አዛውንት ተለያዩ ። ሁለተኛም አልተገናኙም ። ዩስቲኑስ ግን የሽማግሌውን ምክር ሊረሳው አልቻለም ። የነቢያትን ትምህርት ማጥናት ጀመረ ። ከወንጌልም ታሪክ ጋር ቢያነጻጽረው እነርሱ ስለ ኢየሱስ የተናገሩት ሁሉ በሕይወቱ ፣ ሞቱም በመነሣቱም በእርግጥ የተፈጸመ መሆኑን ተገነዘበና እውነት ሆኖ አገኘው ።

ለዩስቲኑስ ግሩምና አዲስ ነገር ታየው ። የነቢያት ቃል የወንጌልም ታሪክ ከእግዚአብሔር የተገለጠልን እውነት መሆኑን ተረድቶ በእምነት ተቀበለው ። ዩስቲኑስ ክርስቲያን ሆነ ። ከወጣትነቱ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ትምህርት ቀስሞ ነበርና ክርስቲያን ከሆነ በኋላ ባገኘው ሰፊ እውቀት ተጠቅሞ በቃል በጽሑፍም በአሕዛብ መካከል የክርስቲያንን ሃይማኖት የሚደግፍና የሚያስፋፋ ትጉና ታጋይ ሐዋርያ ሆነ ።

መ ፡ ወደ ሮሜ ደርሶ ታሰረ ።

የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ ዩስቲኑስ ብዙ አገሮችን ከጎበኘ በኋላ በመጨረሻ ወደ ሮሜ መጣ ። በዚያም ጠላት ተነሥቶበት ለባለ ሥልጣን አልፎ እንዲሰጥ አደረገ ። ከሌሎችም ክርስቲያኖች ጋር ወደ ዳኛ ቀረበ ። የዳኛው ስም ሩስቲኩስ ነው ። የዘመኑ ቄሣር ከ፩፻፷፩ ዓ.ም. እስከ ፩፻፹ ዓ. ም. ድረስ ሥልጣን የያዘ ማርቆስ አውሬሊዩስ ነው ። እርሱም ለሩስቲኩስ ወዳጁ ነበር ።

ሠ ፡ ዩስቲኑስ በዳኛ ፊት ።

ዩስቲኑስ ተከስሶ ወደ ዳኛ ፊት በቀረበ ጊዜ ሁለቱ ያደረጉት ክርክር እንዲህ የሚል ሆነ ፦

ዳኛ ፤ ለአማልክት መታዘዝ ፡ የቄሣርንም ትእዛዝ ማክበር አለብህ ።

ዩስቲኑስ ፤ ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ የሚታዘዝ ሰው ጥፋተኛ አይሆንም ።

ዳኛ ፤ አንተ የምትከተለው ትምህርት እንዴት ያለ ነው?

ዩስቲኑስ ፤ ማንኛውንም ዓይነት ትምህርት ለማጥናት ሞክሬአለሁ ። በመጨረሻ ግን የተቀበልሁት የክርስቲያንን ሃይማኖት ነው ። ተሳስተው የሚገኙት ሰዎች ግን አይወዱትም ።

ዳኛ ፤ ወዮ ምስኪን ፡ ይህን ትምህርት ትወደዋለህ ማለት ነው?

ዩስቲኑስ ፤ አዎን ፡ የክርስቲያኖችን እውነተኛ ሃይማኖት ተከታይ ነኝ ።

ዳኛ ፤ ይህ ሃይማኖት ምን ምን የሚል ነው?
ዩስቲኑስ ፤ የሚታየውን ነገር ሁሉ ፣ ለዓይን የማይታየውንም በፈጠረ በአንድ አምላክ እናምናለን ። በጌታችንም በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን ። በሰው ሁሉ ሊፈርድ የሚመጣ ፣ ነቢያትም የተናገሩለት የእግዚአብሔር ልጅ ነው ። መልካሙን ነገር ለመማር ለሚፈልግ ሁሉ እርሱ መምህር ነው ። ደኅንነትንም የሚያበሥር ነው ። እኔ ግን ሰው ነኝ ፤ በታናሽነቴም ስለ ዘለዓለማዊ መለኰቱ ብዙ ነገር ለመናገር አልችልም ። ይህንን የሚችሉት ነቢያት ናቸው ። የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብዬ ያመንሁበት ወደ ዓለም እንደሚመጣ እነርሱ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ትንቢት ይናገሩ ነበር ።
ዳኛ ፤ ክርስቲያኖች የሚሰበሰቡት በዬት ነው?
ዩስቲኑስ ፤ ሰው በሚኖርበት ስፍራ ሁሉ እግዚአብሔር ቅርብ መሆኑን ያምናሉ ። ስለዚህ በዬትም ሊሰበሰቡ ይችላሉ ።
ዳኛ ፤ መልካም ። በዬት እንደሚሰበሰቡ ግን ደቀ መዛሙርትህንም በዬት እንደምትሰበስባቸው ልትነግረኝ አትችልም?

ዩስቲኑስ ፤ እኔ የምኖረው ከጢሞቴዎስ መታጠቢያ ቤት አጠገብ ባለው በማርቲኑስ መኖሪያ ቤት በሁለተኛው ፎቅ ላይ ነው ። ስለ ሌላ መሰብሰቢያ ቦታ አውቀት የለኝም ። ወደ እኔ ሊመጣ የሚፈልግ ሰው ቢኖር ስለ እውነተኛው መንገድ አስተምረዋለሁ ።
ዳኛ ፤ እንግዲህ ክርስቲያን ነህ ።
ዩስቲኑስ ፤ እውነት ፣ ክርስቲያን ነኝ ።
ዳኛ ፤ ስማ ፣ አንተ የንግግር አዋቂ ትባላለህ ፤ እውነተኛውንም መንገድ አውቀዋለሁ ትላለህ ። እስቲ ፣ ከገረፉህ በኋላ አንገትህ ተቈርጦ ስትሞት ወደ መንግሥተ ሰማያት የምትገባ ይመስልሃል?
ዩስቲኑስ ፤ ይመስልሃል አትበለኝ ። እንደምገባ አውቃለሁ ። እርግጠኛ ነኝ ፤ በውስጤ ምንም ጥርጥር የለብኝም ።
ዳኛ ፤ ወደ ዋናው ነገር እንመለስና ልንገራችሁ ፤ ሁላችሁም ቀርባችሁ ለአማልክት መሥዋዕት ማቅረብ ይኖርባችኋል ።

ዩስቲኑስ ከእርሱም ጋር የነበሩት ሌሎቹም ክርስቲያኖች ይህን አናደርግም ብለው መለሱ ።

ረ፡ ዩስቲኑስ ሌሎቹም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ሞቱ።

ለአማልክት አንሠዋም በማለታቸው ነገሩ ተወሰነ። ፍርድም ተሰጠ ። ለአማልክት አንሰግድም ፣ ለቄሣር ትእዛዝም አንታዘዝም ብለዋልና ይገረፉ ፣ ከዚያም በኋላ አንገታቸው ተቈርጦ ይሙቱ የሚል ቃል ከዳኛ ተሰማ።

እንደ ተበየነባቸው ሆነ ። እስረኞች ወደሚሞቱበት ስፍራ ተወሰዱ ። እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ለጌታ ክብር አሠቃቂ በሆነው አሟሟት ከዚህ ዓለም ተለዩ ። ይህም የሆነው በ፩፻፷፯ ዓ.ም. ገደማ ነው ።

## ፫፤ ጴርጴቱአ ።

### ሀ፡ በካርታጐ አምስት ክርስቲያኖች ታሰሩ ።

ሰጵቲሚዩስ ሴቬሩስ ቄሣር በነበረበት ጊዜ እንደ ገና በክርስቲያኖች ላይ ስደት ተጀመረ ። ዘመነ መንግሥቱ ከ፩፻፺፫ ዓ.ም. እስከ ፪፻፲፩ ዓ.ም. ድረስ ሲሆን ክርስቲያኖች እንዲሰደዱ ትእዛዝ ያስተላለፈው በ፪፻፪ ዓ.ም. ነው ። በዚያን ጊዜ በተለይ በግብጽ አገርና በሰሜናዊ አፍሪካ ውስጥ የነበሩት ክርስቲያኖች ከባድ በሆነ ሁኔታ ተሠቃዩ ።

ካርታጐ በተባለች ከተማ አምስት አዲሶች ክርስቲያኖች ነበሩ ። ሦስቱ ወንዶች ሁለቱም ሴቶች ናቸው ። በቅርብ ጊዜ ያመኑ ከመሆናቸው የተነሣ ገና የክርስትናን ትምህርት በመማር ላይ ናቸውና አልተጠመቁም ነበር ። ስደት በመጣ ጊዜ አምስቱ ተያዙ ።

ጴርጴቱአ የተባለች ከሁለቱ ሴቶች አንዷ ትዋ ከትልቅ ሰው የተወለደች ስትሆን ፊሊኪታስ የተባለች ሁለተኛይቱ በሰው ቤት የምታገለግል በክርስቶስ ያመነች ባሪያ ናት ።

### ለ፡ ጴርጴቱአና አባትዋ ።

ጴርጴቱአ ባል አግብታ ከመታሰርዋ በፊት ልጅ ወልዳ ነበር ። ሰዎችም ሊያስሩአት የመጡባት ሕፃንዋን ታቅፋ ሳለች ነው ። ወደ ወኅኒ ቤት ከወሰዱአት በኋላ አረማዊ የሆነ አባትዋ ሊፈልጋት ወዲያው መጣ ።

ለእርስዋም ለሕፃንዋም በጣም ስላዘነ ክርስቶስን እንድ ትክድ ፥ አማልክትንም እንድታከብር በብዙ ልመና ሊያባብላት ሞከረ ።

እርስዋ ግን ፡— አባቴ ሆይ ፥ ያችን እንስራ ታያለ ህን? ብላ ጠየቀችው ።

እርሱም ፡— አያለሁ አለ ።

እርስዋም ፡— ታዲያ ፥ እንስራ ከሆነች ሌላ ስም ሊኖራት ይቻላልን? ብላ ብትጠይቀው ሌላ ስም የላትም አለ ።

ጼርጼቱአም መልሳ ፡— እንግዲያውስ እኔ ክርስቲ ያን ከሆንሁ ሌላ ስም አይሆንልኝም ፥ ራሴን የምጠራው በዚህ ስም ብቻ መሆን አለበት አለችው ።

በዚያን ጊዜ አባትዋ ከመጠን በላይ ተቈጣት ። እርስዋ ግን ስለ አባትዋ ስትል ሐሳብዋን ለመለወጥ አልቻለችም ። እርሱም ትቶአት ሄደ ።

ሐ ፣ ስለ ልጅዋ የተሰማት ኀዘን ።

ከእስራትዋ ይልቅ ጼርጼቱአን ያሳዘናት በወኅኒ ቤት ከሕፃንዋ መለየትዋ ነው ። የወኅኒ ቤት ጠባቆች ሕፃንዋን ወስደውባት ነበር ። የሚጠባ ልጅም ስለ ሆነ ልጁ ምን ይሆናል እያለች ታለቅስ ነበር ። በሁለት ዲያ ቆናት አቤቱታና ልመና ግን ሕፃንዋ እንዲመለስላት ተፈቀደላት ። በጣም ደስ ብሎአትም በወኅኒ ቤት ታጠ ባው ነበር ።

ፌሊኪታስም በወኅኒ ቤት ሳለች ሴት ልጅ ወለደች። አንዲት ክርስቲያን ሴት ሕፃንዋን የራስዋ አድርጋ ወሰ ደችላት ።

የጼርጼቱአ አባት ልጁን ከአሠቃቂ ሞት ለማዳን ብዙ ጊዜ እየመጣ ይለምናት ነበር ። ክርስቲያን አይደ ለሁም በይና ይለቅቁሻል እያለ ያባብላት ነበር ። እርስዋ ግን በእምነትዋ የጸናች ሆነች ። ይህንን በግልጽ ለማሳ የት የቻለችው በወኅኒ ቤት ሳለች በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በመጠመቅዋ ነው ።

የከተማው ገዢ በተፈጥሮው ደግ ሰው ነውና ገና በአፍላ ጊዜዋ ያለችው መልከ መልካም ሴት ከሞት

እንድትድን ለማድረግ ስለ ፈለገ እንደ አባትዋ ያባ ብላት ነበር ። እርስዋ ግን በግልጽ ፦ ክርስቲያን ነኝ ፤ ለአማልክትም አልሠዋም ከማለት በስተቀር ሌላ የምት ጨምረው ነገር የላትም ። ስንዝር ያህል ወደ ኋላ አላፈ ገፈገችም ።

መ ፥ አምስቱ በአውሬ ከቈሰሉ በኋላ በሰይፍ ሞቱ ።

እንግዲያውስ ገዢው ምን ያድርግ? የሮሜ ባለ ሥልጣን እንደ መሆኑ መጠን የመንግሥትን ሕግ ማክ በር አለበት ። እንደ ሕጉ የሆነ እንደ ሆነ ለመንግሥት አማልክት ለቄሣርም ተገቢውን አክብሮትና ስግደት ለማድረግ የማይፈልግ ሁሉ የግድ መቀጣት አለበት ። ስለዚህ በኀዘንም ቢሆን ገዢው ጴርጴቱአ ፥ ፊሊኪታ ስም ፥ ሦስቱም ወንዶች በአውሬ ተበልተው እንዲሞቱ ፈረደባቸው ።

ብዙ ተመልካች ወደ ተሰበሰበበት ወደ ካርታጐ የቲያትር አደባባይ ወሰዱአቸው ። በዚያም በብረት መዝጊያ በተዘጋ ቤት ውስጥ አውሬ ይጠብቃቸዋል ።

የአውሬ ቤት ተከፈተ ። ነብርም ፥ ድብም ፥ ከርከ ሮም ተለቀቀባቸው ። ነገር ግን በምን ምክንያት እንደ ሆነ አልታወቀም ፤ አውሬዎቹ እስረኞቹን ቢያቈስሉአ ቸውም አልገደሉአቸውም ። ስለዚህ ወታደሮች በሰይፍ እንዲገድሉአቸው ተወሰነ ።

ሳቱሩስ የተባለው ከሦስቱ ወንዶች አንዱ ነብር ክፉኛ አቍስሎት ነበርና ከቍስሉ ደም ይፈስ ነበር ። በእጁ ላይ ቀለበት አድርጎአልና ቀለበቱን አውልቆ በደሙ ነክሮት ለሚገድለው ወታደር ሰጠውና ፦ እም ነቴን አትርሳ ካለ በኋላ እንዲገድለው አንገቱን ገለጠለት።

ፊሊኪታስን እንዲወጋት የተመደበው ወታደር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሞክር ሳታት ። እርስዋ ግን በገዛ እጅዋ ሰይፉን ወደ አንገትዋ መልሳ በዬት እንደሚወ ጋት አሳየችው ።

ጴርጴቱአም ያለ ፍርሃት በደስታ ለገዳዩ ሰውዬ ደረትዋን ገልጣ አሳየችው ። እርስዋም ተወግታ ሞተች።

በዚህ ዓይነት አሟሟት አምስቱ ሰዎች የክርስቲ ያን ትግላቸውን በድል አድራጊነት ፈጸሙት ። የሕይ

ወትንም አክሊል ሊቀዳጁ ወደ ዘለዓለማዊው ዓለም ተሻገሩ ።

## ፩ ፤ በዴሲዩስ ዘመነ መንግሥት ስለ ሆነው ስደት ።

### ሀ ፣ አደጋ ሲመጣ ጥፋቱ የማን ነው?

ከፍ ብለን የጠቀስናቸው ሰማዕታት ለረጅም ጊዜ በየአገሩ በክርስቲያኖች ላይ ለደረሰባቸው ስደት ፣ መከራና ሞት ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ ። ተመሳሳይ በሆነ መንገድ በጠላት ጥቃማ ለባለ ሥልጣን አልፈው የተሰጡ ፣ በዳኛ ፊትም ክርስቶስን እንዲክዱ የተጠየቁ ፣ እንቢ በማለታቸውም በእሳት ፣ በሰይፍ ፣ በአውሬ ፣ በስቅላት ፣ በድብደባም ፣ በግርፋትም የሞቱ በሺህ የሚቈጠሩ ናቸው ።

አንዳንዶች ቄሣሮች ክርስቲያኖችን በጣም አያጠቁአቸውም ነበር ። እንደ ተመለከትነው ግን ክርስቲያኖች ታድነው እንዲቀጡ አዋጅ በማስነገር ለብዙ ሥቃይ ምክንያት የሆኑባቸው ቄሣሮች አሉ ።

በ፪፻፵፱ ዓ.ም. ዴሲዩስ የሮሜ ቄሣር ሆነ ። ዘመነ መንግሥቱም አጭር ሆነ ። በ፪፻፶፩ ዓ.ም. ከውጭ አገር ጠላት ጋር ባደረገው ዘመቻ ላይ ተወግቶ ሞተ። ነገር ግን ለአጭር ጊዜ ብቻ ሮሜን የገዛ ቢሆንም ክርስቲያኖችን በማሳደዱ በቤተ ክርስቲያን ላይ ከባድ ሥቃይ አደረሰባት ።

በዘመኑ ብዙዎች አስቸጋሪዎች ሁኔታዎች የሮሜን መንግሥት ሰላም ያናውጡ ነበር ። የውጭ አገር ጠላት ድንበሩን እየተሻገረ በጦር መሣሪያ በአገር ተወላጅ ላይ አደጋ ይጥል ነበር ። ተላላፊ በሽታ ሌላ ዓይነት አደጋም ሕዝቡን ያጠቃው ነበር ።

ይህ ሁሉ ጉዳት በአገራችን ላይ ሊደርስ የቻለው በምን ምክንያት ነው? እያሉ ሰዎች ይጠያየቁ ጀመር ። ምናልባት ሰው የሮሜን አማልክት በሚገባ ባለማክበሩ ይሆን? አማልክትን ችላ ያሉአቸው ፤ እንዲያውም የናቁአቸው ሰዎች መኖራቸው ይታወቃል ። በተለይም ክርስቲያኖች የተባሉት በዚህ ነገር የሮሜን አማልክት አስቈጥተዋቸው ይሆናል ። የዘመኑ የተፈጥሮ አደጋዎች

ጦርነቶችም አገሩን ያወኩት በእነዚህ ሰዎች ምክንያት ከሆነ ቢወገዱ ይሻላል የሚል እምነት በሕዝብ መካከል አልጠፋም ።

ለ ፡ የተርቱሊያኑስ ቃል ።

ነገሩ አዲስ አይደለም ። ክርስቲያኑ ደራሲ ተርቱሊያኑስ ክርስቲያኖችን በሚደግፍ መጽሐፍ እንዲህ ብሎ ጽፎአል ፡—

ሰዎች ክፉዎች ወንጀለኞች ናቸው ይሉናል ። የቲበር ወንዝ ውኃ እያደገ ቢመጣና እስከ ከተማይቱ ግንብ ቢደርስ ፡ ወይም ደግሞ የዓባይ ውኃ አንሶ ማሳ ዎቹን ካላጠጣ ፡ ሰማይ ዝናብ ከከለከለ ፡ የመሬት መንቀጥቀጥ ቢመጣ ፡ ድርቀት ወይም በሽታ አገሩን ቢያጠቃ ሕዝቡ ተነሥቶ ፡— ክርስቲያኖች ወደ አንበሶች እያለ ይጮኻል ።

እንደ ሕዝቡ አስተሳሰብ ይህ አደጋ ሁሉ የመጣው በክርስቲያኖች ምክንያት ነው ማለቱ ነው ።

በዴሲዩስ ዘመነ መንግሥት ለተጀመረው ስደት ተመሳሳይ ምክንያት ይኖራል ብለን ለማሰብ እንችላለን።

ሐ ፡ የመሥዋዕት ማስረጃ ተፈለገ ።

ሰው ሁሉ ለአማልክት መሥዋዕት ማቅረብ አለበት ብሎ ዴሲዩስ ማስታወቂያ አስነገረ ። ሁሉም ለዚህ ትእዛዝ መታዘዙ እንዲታወቅለት ሰው በቤተ መቅደስ ከሠዋ በኋላ ፡— በትእዛዙ መሠረት መሥዋዕትን አቅርቦአል የሚል በባለ ሥልጣን የተዘጋጀ የጽሑፍ ማስረጃ በእጁ እንዲኖር በሕግ ተወሰነ ። እንደዚህ ያለ ማስረጃ በእጁ ያልያዘ ሰው ቢኖር ፡— ለቄሣር አልታዘዘም ፡ የአማልክትና የመንግሥት ጠላት ነው ተብሎ ይከሰሳል።

ይህ ሕግ ለክርስቲያኖች በጣም አስቸጋሪ ሆነ ። ማምለጫ መንገድ ጠፋባቸው ። ሞትንም በመፍራት የተፈለገባቸውን መሥዋዕት አቅርበው ክርስቶስን የካዱት የበዙ ናቸው ። ሌሎች ግን ለአማልክት ሳይሠው ለቄሣር የታዘዙ ለማስመሰል ሲሉ በገንዘባቸው ማስረጃ በመግዛት ከመሞት ዳኑ ። ይህን የመሰለ የማምለጫ

መንገድ የሞከሩ ግን በብዙ አገር እንደ ከሐዲዎች ሳይቈጠሩ አልቀሩም ። በተንኰል ሕይወታቸውን ለማ ዳን የሚፈልጉ ሆነው ስለ ተገኙ ነገሩ እንደ ውድቀት ተቈጠረባቸው ።

ከእነርሱ በመለየት የቄሣርን ትእዛዝ ፥ የባለ ሥል ጣንንም ዛቻ ፥ የሞትንም ሥቃይ ሳይፈሩ እስከ መጨረሻ ትንፋሻቸው ድረስ በክርስቲያን እምነታቸው የጸኑ በር ከት ያሉ ናቸው ። ብዙዎቹም ሕይወታቸውን አጡ ።

በዴሲዩስ ስደት የኢየሩሳሌም ፥ የአንጾኪያ ፥ የሮ ሜም ጳጳሳት በሰማዕትነት ሞቱ ። ሕይወታቸውንም ለማ ዳን ሸሽተው በተደበቁበት ስፍራ በብዙ ጭንቀት መካ ከል የኖሩ የበዙ ናቸው ። አንዳንድ ጊዜም ተይዘው በመንግሥት የማዕድን ቦታዎች ከባድ ሥራ በመሥራት እንዲጉላሉ ይደረግ ነበር ።

## ፯ ፣ ዲዮክሌቲያኑስ ያመጣው ከባድ ስደት ።

## ክርስትና እንዲጠፋ የታወጁት አዋጆች ።

ከስደቶች ሁሉ የባሰ ሆኖ የተገኘው የመጨረሻው ነው ። ይህም ዲዮክሌቲያኑስ ቄሣር በነበረበት ዘመን ነው ። ዘመነ መንግሥቱ ከ፪፻፹፬ እስከ ፫፻፭ ዓ.ም. ነው ።

መንግሥታችን እንዲጠነክር ክርስቲያኖች በሙሉ መጥፋት አለባቸው በሚል እምነት በ፫፻፫ እንዲሁም በ፫፻፬ ዓ.ም. ቀጥሎ ያሉትን አዋጆች አስነገረ ።

ሀ ፣ የክርስቲያኖች መሰብሰቢያ ቦታዎች የሆኑት አብያተ ክርስቲያናት ይፍረሱ ።

ለ ፣ የተገኙት መጽሐፍ ቅዱሶች በሙሉ ይቃጠሉ ።

ሐ ፣ ክርስቲያኖች በዬትም ለጸሎት ሊሰበሰቡ ፈቃድ የላቸውም ።

መ ፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤት የተቀጠረ ክርስቲያን ሁሉ ክርስቶስን ካልካደ ወዲያው ከሥራ ይሰናበት።

ሠ ፣ ሰው በክርስቲያንነቱ ከጸና የዜግነት መብቱ ሁሉ ይጠፋበታል ።

ረ ፡ ነጻነት የተሰጣቸው ክርስቲያኖች ባሪያዎች ሃይማኖታቸውን ካልካዱ እንደ ገና ነጻነታቸውን ያጣሉ። አንድም ሳይቀር ክርስቲያኖች ሁሉ ወደ ቤተ መቅደስ ቀርበው ለአማልክት እንዲሰግዱና እንዲሠው ይሁን ። ሳያደርገው የሚቀር ሰው ቢኖር በሞት ይቀጣል ።

ሰ ፡ ከዚህም ሌላ የቤተ ክርስቲያን ካህናት በሙሉ እንዲታሰሩ የተለየ አዋጅ ተነገረ ። የተያዙት ካህናት ግን በጣም የበዙ ስለ ሆኑ ወኅኒ ቤቶች የማይበቁ ሆኑና ፡— ለአማልክት ቢሠሙ ይለቀቁ ተብሎ የእስራት ትእዛዝ ተለወጠ ።

ከእነዚህ አዋጆች የተነሣ ጊዜው ለክርስቲያኖች በጣም አስፈሪ ሆነ ። በአዋጁ መሠረት አብያተ ክርስቲያናት ፈራረሱ ። ጳጳሳትና ቄሶችም ታስረው ተገደሉ ። ምዕመናንም በብዛት ታደኑና ወደ ሮማውያን አምልኮ እንዲመለሱ ተጠየቁ ። ከደረሰባቸውም ሥቃይ የተነሣ ክርስቶስን ክደው ወደ አረመኔነት የተመለሱት ጥቂቶች አልነበሩም ። ሌሎች ግን እስከ ሞት ድረስ ለክርስቶስ ታማኞች ሆነው ተገኙ ።

## የሰማዕታት ደም የቤተ ክርስቲያን ዘር ነው ።

ይህን በመሰለ ሥቃይ መካከል ቤተ ክርስቲያን ለምን አልተደመሰሰችም? የእግዚአብሔር ተአምራት ነው ። አልጠፋችም ። መጥፋትም ይቅርና ክርስቲያኖች በተሰደዱበትና በተገደሉበት መጠን የክርስቶስ ወንጌል በበለጠ እየተስፋፋ ሄደና በየአገሩ ተከታዮችን አገኘ ። ስለዚህ የስደት ዘመን ቤተ ክርስቲያንን አስፋፋት እንጂ አልቀነሳትም ለማለት ይቻላል ።

በ፪፻፳ ዓ.ም. የሞተው ተርቱሊያኑስ የተባለው ከቤተ ክርስቲያን አበው አንዱ ፡— የሰማዕታት ደም የቤተ ክርስቲያን ዘር ነው ብሎ የጻፈው ቃል እውነተኛ ነው ። የክርስቲያን ደም በፈሰሰበት ቦታ አዲስ ክርስቲያን ተገኘ ። የሰማዕታትን በደስታና በድፍረት መሞት በመገረም ተመልክተው ራሳቸው ክርስቲያኖች የሆኑ ጥቂቶች አይደሉም ።

በተራ ሕዝብ መካከል ብቻ ሳይሆን በባለ ሥልጣኖችና በከፍተኛ ደረጃ በሚኖሩት ሰዎች መካከል እንኳን የክርስቶስ ወንጌል ተሰሚነትን አገኘ ። በቄሣርም ቤት ሳይቀር ሰዎች አምነዋል ። አስገራሚ የሆነ ነገር ነው ። ገና በሐዋርያት ዘመን ቄሣርን በሚያገለግሉት ሰዎች መካከል በክርስቶስ ያመኑ ነበሩ ። ፊልጵ. ፬ ፣ ፳፪ ይመልከቱ ።

ኃያሉ የሮሜ መንግሥት ትጥቁን ታጥቆ በቈራጥነት ቢነሣም የወንጌልን መስፋፋት ሊያግደውና ሊያጠፋው አልቻለም ። ከዘመን ወደ ዘመን ቃሉ አሰደናቂ በሆነ ቅልጥፍና እየተስፋፋ ሄደ ። ይህም ሆኖ በ፫፻ ዓ. ም. ገደማ በሜዲቴራኔ ባሕር ዙሪያ ወዳሉት አገሮች ሁሉ ተዳርሶ ነበር ። በትንሽዋ እስያም በርከት ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ተቋቁመው ነበር ። በኤውሮጳ ክፍለ ዓለምም እስከ እንግሊዝ አገር ድረስ የክርስቶስ ቃል ተሰምቶ ነበር ።

## ጥያቄዎች ።

፩· በዮሐንስ ራእይ አንቲጳስ ስለ ተባለው ሰው ምን ተጻፈ?

፪· እግናቲዩስ እግዚአብሔርን በቃሉ ያገለገለው በየትኛው አገር ነው?

፫· እግናቲዩስ በእምነቱ ምክንያት የተያዘው በምን ጊዜ ነው?

፬· ከጥንታውያን ሰማዕታት መካከል ለሐዋርያው ዮሐንስ ወዳጁ የነበር ማን ነው?

፭· ገርማኒኩስ የተባለው ወጣት ክርስቲያን በሰማዕትነት መሞቱ እንዴት ነበር?

፮· ዩስቲኑስ ክርስቲያን ሊሆን የቻለው ምን በማድረጉ ነው? የመከረውስ ማን ነው?

፯· በ፪፻፪ ዓ.ም. በካርታጎ አገር በክርስትና እምነታቸው ምክንያት የሞቱት ሴቶች ስም ስማቸው ማን ነው?

፰· ክርስቲያኖች ለአማልክት መሥዋዕት እንዲያቀርቡ በዴሲዩስ ዘመነ መንግሥት እንዴት ያለ ነገር ተፈለገባቸው?

፱. በዲዮክሌቲያኑስ ዘመነ መንግሥት የመጣው ስደት ከሌላ ስደት ሁሉ ይበልጥ ለክርስቲያኖች ከባድ የሆነባቸው በምን ምክንያት ነው?

፲. ተርቱሊያኑስ ፦ የሰማዕታት ደም የቤተ ክርስቲያን ዘር ነው ብሎ ሊጽፍ የቻለው ምኑን ተመልክቶ ነው?

፲፩. በ፫፻ ዓ.ም. ገደማ የክርስቲያን ሃይማኖት ምን ያህል ተስፋፍቶ ነበር?

## ምዕራፍ ስድስት ።

## ፩፤ ቤተ ክርስቲያንን ያስፋፉ ሁኔታዎች እንዴት ያሉ ናቸው?

ባለፉት ምዕራፎች እንደ ተመለከትነው የክርስትና ሃይማኖት በምድር ላይ መሰበክ ከተጀመረበት ጊዜ አንሥቶ አልፎ አልፎ ምዕመናን ይሰደዱ ነበር ። ቢሆንም ክርስትና አልጠፋም ። በመጥፋት ፈንታ ክርስቲያኖች ከዓመት ወደ ዓመት እየጨመሩ ሄዱ ። ቤተ ክርስቲያን መስፋፋትዋን ቀጠለች ።

ይህም በምን ምክንያት ነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው ። ለጥያቄው መልስ የሚሆን ልዩ ልዩ ነገር ለመጥቀስ ይቻላል ። ቀጥሎ ያሉትን ሁኔታዎች ማውሳት አስፈላጊ ነው ።

### ሀ፤ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ አለ ።

ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ቃል ነው ። ወንጌልን ለዓለም ሕዝቦች እንዲሰብኩ አሥራ አንዱን ደቀ መዛሙርት በላካቸው ጊዜ ፦ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ብሎ ቃል ገባላቸው ። ማቴ. ፳፰፤ ፳ ።

እነርሱም በታዘዙት መሠረት ስብከታቸውን ጀመሩ ። በመጀመሪያዎች ሐዋርያት የተጀመረውም ነገር ከትውልድ ወደ ትውልድ ቀጠለ ። የክርስቶስ ቃል በተስፋፋበት ሁሉ ተቃውሞና ስደት ተከታትሎ መምጣቱ አልቀረም ። ቢሆንም ቤተ ክርስቲያን አልጠፋችም ።

ይኸውም ክርስቶስ ከእርስዋ ጋር ስለ ነበር ነው ። የገሃነም ደጆች አይችሉአትም ብሎ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ተስፋ አላጠፈውም ። ማቴ. ፲፮ ፥ ፲፰ ። በክር ስቶስ ኃይል ታሸንፋለች ።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ ፰ ፥ ፴፭—፴፯ እንደ ሚለው መከራ ፥ ጭንቀት ፥ ስደትም ራብም ፥ ራቁትነ ትም ፥ ፍርሃትና ሰይፍ ክርስቲያንን ሊነካው ይችላል ። ሲጸናበትም እንደሚታረድ በግ ሊሆን ይችላል ። በወ ደደው በክርስቶስ ግን ያሸንፋል ። እንዲያውም ከአሸ ናፊ በልጦ ይገኛል ። በምስክርነትም ሌሎችን ያሳምናል።

እንግዲህ ጥንታውያን ክርስቲያኖች በብዙ መከራ መካከል ያልጠፉበት ፥ ወንጌልም እየተስፋፋ ሊሄድ የቻ ለበት ዓይነተኛው ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር ስለ ሆነ ነው ።

ለወንጌል መስፋፋት ሌሎችም ምክንያቶች አሉ። ቀጥሎ ያሉትን እንመልከት ።

## ፪ ፤ ወንጌል የሰውን ልብ የሚያረካ ስለሆነ ተሰሚነትን አገኘ ።

የሮሜ መንግሥት ቄሣሮችና ባለ ሥልጣኖች የክርስቲያኖችን ስብከትና ትምህርት ሊያግዱት ያል ቻሉት በምን ምክንያት ነው ? በጣም ጣፋጭና ልብን የሚያረካ መልእክት በመሆኑ ነው ። የወንጌል ቃል የልብን ናፍቆት ሊያስታግሥና ሊያሟላ ይችላል ።

የክርስቲያኖች ስብከትና ትምህርት በአጭሩ እንዲህ የሚል ነበር ፤ ሰማይና ምድርን የፈጠረ አንድ እው ነተኛ አምላክ አለ ። እርሱም ሰውን ይወድዳል ። ከመ ውደዱም የተነሣ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ዓለም ላከ ። አንድያ ልጁም ሰውን ከኃጢአቱ ለማዳን እንዲ ችል ስለ ሰው ሁሉ ተሰቅሎ ሞተ ። እርሱም ጻድቅ ስለ ሆነ ሞትን አሸንፎ በሦስተኛው ቀን ሕያው ሆኖ ከመቃብር ተነሣ ። አሁንም ሕያው ነው ። ከሙታን ከተነሣ በኋላ ወደ ሰማይ አረገ ። ከእግዚአብሔርም ዘንድ በቀኝ ተቀመጠ ። በዓለም ፍጻሜ ግን በሕያዋ ንና በሙታን ሊፈርድ ከዚያ ተመልሶ ይመጣል ። በእርሱም የሚያምኑት የኃጢአታቸውን ስርየት ያገ

ኛሉ ። እግዚአብሔርም ልጆቹ አድርጎ ይቀበላቸዋል ። በምድርም ላይ እስካሉ ድረስ በሚያስፈልጋቸው ሁሉ ይከባከባቸዋል ። እንዲሁም በሞት ከዚህ ዓለም በሚለዩበት ጊዜ በወዲያኛው ዓለም ሰላምና ብፅዕና በሞላበት በእግዚአብሔር መንግሥት እስከ ዘላለም ይኖራሉ ።

የኢየሱስን ቃል ሰምቶ በእምነት የተቀበለው ሁሉ ይህንን በረከት ያለ ዋጋ ያለ ገንዘብም ያገኛል እያሉ ይሰብኩ ነበር ።

ይህ ስብከት ብዙዎችን የሚያጽናና ፣ የሚያረካም ሆነ ። የፈጠረኝ አምላክ ይወድደኛል የሚለውን ትምህርት ከዚህ በፊት ሰምተው አያውቁም ነበር ። በጣም ግሩምና አዲስ ነገር ሆነላቸው ። ይህ አምላክም በልጁ ተገልጦ ከኃጢአቴ አድኖኛል የሚለው ቃል የበለጠውን ልባቸውን ማረከ ። ከዚህም በላይ ከሞት በኋላ ምን እሆናለሁ ? እያሉ ሰዎች ሲጨነቁ ክርስቲያኖች ስለ ዘላለም ሕይወት የሚያስተምሩት ቃል እረፍትንና ሰላምን መለሰላቸው ። በደስታም ተቀበሉት ።

ለቤተ ክርስቲያን አስደናቂ እድገት አንዱ ምክንያት ይህ ነው ።

## ፫ ፤ የክርስቲያን የመንፈስ አንድነት ብዙዎችን ወደ ወንጌል ስብከት የሚስብ ሆነ ።

በባህል ፣ በቋንቋ ፣ በአለባበስ ፣ በአኗኗር ይህንንም በመሰለ ምክንያት በሰው መካከል ልዩነት መደረጉ የተለመደ ነገር ነው ። ሰው በልዩ ልዩ ምክንያት ተለያይቶአል ።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ጻፈው ግን ክርስቲያኖች በአንድ ተስፋ የተጠሩ ፣ አንድ መንፈስም የተቀበሉ ፣ በአንድ ጌታ ያመኑ ፣ በአንዲትም ጥምቀት የተጠመቁ ፣ አንድ አካል እንዲሆኑ የተፈጠሩ በመሆናቸው እውነተኛ አንድነት አላቸው ።

የጥንት ዘመን ክርስቲያኖች በአገር በቋንቋም ፣ በባህል ፣ በአኗኗርም የተለያዩ ቢሆኑም ፤— በክርስቶስ አንድ ነን እያሉ በኅብረታቸው ይደሰቱ ነበር ። አረማውያንም መለያየት በበዛበት ዓለም ይህንን የመሰለ

አንድነት በማየታቸው ልባቸው ተነካና ፣ እኛም በዚህ አንድነት ተካፋዮች ብንሆን ጥሩ ነው በሚል መንፈስ ወደ ክርስቲያኖች ይጠጉ ነበር ።

ሁላችን በክርስቶስ አንድ ነን በሚለው እምነት ክርስቲያኖች ጨዋ ሰው ፣ባሪያ ፣ ባለጠጋ ሀብታም ፣ የተማረ ያልተማረ ፣ ትልቅ ትንሽ ፣ ወንድ ሴት እያሉ በሰው መካከል ልዩነትን አያደርጉም ነበር ። በእነርሱ አስተሳሰብ የኑሮ ደረጃ ልዩነትን አያመጣም ። ድሀና ሀብታም ጐን ለጐን በቤተ ክርስቲያን ሊቀመጡ ይችላሉ ። ቤተ ክርስቲያንም ለሁሉም ክፍት ስለ ሆነች የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት የቀረቡት የተቀበሉትም ድሆች በርከት ያሉ ናቸው ። ፩ ቆሮ. ፩ ፣ ፳፮—፳፱ ።

እንዲሁም በዘር ወይም በጐሣ ምክንያት ልዩነትን ባለማድረግዋ ብዙዎች ሰዎች ተደስተው ለቤተ ክርስቲያን ተጨመሩ ።

## ፬ ፣ በክርስቲያኖች እጅ ተአምራት ይደረጉ ነበር።

ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በተመላለሰበት ዘመን ከሰዎች አጋንንትን በማውጣት በሰይጣን ላይ ኃይል ያለው መሆኑን ብዙ ጊዜ ይገልጥ ነበር ። ድውያንም በእጁ ተፈወሱ ። ሰውም ይህን ሁሉ አይቶ እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር ።

አሥራ ሁለቱንም ደቀ መዛሙርት ለእግዚአብሔር ቃል ስብከት በላካቸው ጊዜ ፣ ድውዮችን ፈውሱ ፣ አጋንንትንም አውጡ ብሎ ሥልጣን ሰጣቸው ። ማር. ፫ ፣ ፲፭ ። በሐዋርያትም ጊዜ ብቻ ሳይሆን ቀጥሎ ባሉት ዘመናትም ወንጌል በተስፋፋበት አገር ሁሉ በእግዚአብሔር ኃይል እንደዚህ ያሉ ተአምራት ይፈጸሙ ነበር ።

ይህን ሁሉ በማየት ብዙዎች ሰዎች ፣ የክርስቲያኖች አምላክ እውነተኛ መሆን አለበት እስከ ማለት ደረሱና የእግዚአብሔርን ቃል አመኑ ።

## ፭ ፤ የሰማዕታት ሰላምና ደስታ የሰውን ልብ ነካው ።

በስደት ጊዜ ሰማዕታት በደስታና በተቀደሰ ድፍ፡ ረት ሲሞቱ ባዩ ጊዜ ፣ እነዚህ ሰዎች ያገኙትን ኃይል ደስታና ሰላምም እኛም ማግኘት ያስፈልገናል በሚል ስሜት ተቀስቅሰው ከአረመኔነት ወደ ክርስቲያንነት የተመለሱ ጥቂቶች አይደሉም ። የክርስቲያኖች ጠን ካራ እምነት አሸነፉቸው ማለት ነው ።

ተርቱሊያኑስ ፦ የሰማዕታት ደም የቤተክርስቲያን ዘር ነው ብሎ ሊጽፍ የቻለው ይህን ሁኔታ ተመልክቶ ነው ።

## ፮ ፤ ክርስቲያኖች ቢሰደዱም ስለ ክርስቶስ መመስከራቸውን አልተውም ።

ከዚህ በፊት እንደ ተመለከትነው ስደት ከመጠን በላይ ሲጸናባቸው በግልጽ ሳይሆን በስውር ለጸሎትና ለእግዚአብሔር ቃል ስብከት እንዲሰበሰቡ ክርስቲ ያኖች የተገደዱበት ጊዜ ነበር ።

ቢሆንም በሕዝብ መካከል እየተመላለሱ ስለ መድኃኒታቸው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መመስከራች ውን አላቋረጡም ። በዘመድ መካከል ፣ በጐረቤትም መካከል ፣ በያሉበት ሁሉ ከክርስቶስ ስላገኙት ደስታ ስለ ቃሉም እውነተኛነት ይናገሩ ነበር ።

በዚህ ዓይነት ምስክርነት የወንጌል ቃል ይስ ፋፋ እንደ ነበር የታመነ ነው ። ሐዋርያት ጥንት ፦ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም እንዳሉት ሁሉ ፣ የሮሚ መንግሥት ክርስቲ ያኖች በክርስቶስ ያገኙትን በረከት ከመግለጥ ዝም ለማ ለት አልቻሉም ። የሐዋ. ፬ ፥ ፳ ።

## ፯ ፤ የክርስቲያኖች የእርስ በርስ ፍቅር በመልካም ይመሰክርላቸው ነበር ።

ጌታ ኢየሱስ ፦ እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ይህን አዛችኋለሁ ብሎ የተናገረውን ቃል የጥንት ዘመን ክርስቲያኖች አልረሱትም ። የሐዋ. ፲፭ ፥ ፲፯ ። ሐዋርያት

ም ስለ ወንድማማች ፍቅር ያበረከቱት ምክር ብዙ ነው ። ክርስቲያኖችም ያገኙትን ምክር በተግባር ተር ጕመውታል ። ይዋደዱ ነበር ። ፩ ቆሮ. ፲፫ ። ፩ ዮሐ. ፬፥ ፯—፰ ።

የዘመኑ አሕዛብ ፍቅራቸውን በመገረም ይመለ ከቱት ነበር ። ተርቱሊያኑስ መገረማቸውን በመጥቀስ ፦— እነዚህ ክርስቲያኖች እንዴት እንደ ተፋቀሩ ተመልከቱ ይላሉ ብሎ ጽፎአል ።

ክርስቲያናዊ ፍቅር ሰውን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚስብ ኃይል ሆነ ።

## ፰ ፤ ክርስቲያኖች የቸርነትን ሥራዎች በመሥራ ታቸው ከሃይማኖት ውጭ የሆኑትን ያስደስቱ ነበር ።

ሰው በተፈጥሮው ለራሱ ጥቅም ለማግኘት እንጂ ሌሎችን ለመጥቀም እጅግ አያስብም ። የሌላውን ችግር እየተመለከተ፥— የእኔ ጉዳይ አይደለም ብሎ ማሰቡ የተ ለመደ ነገር ነው ።

ክርስቲያኖች ግን ከዚህ የተሻለውን ነገር አሳይ ተዋል ። ከክርስቶስና ከሐዋርያት እንደ ተማሩት ለሰው ሁሉ ፤ በተለይም ለተቸገሩት የረድኤት እጃቸውን ይዘ ረጉላቸው ነበር ። ድሆችን ፤ ባልቴቶችንም ድሀ አደጎ ችንም በገንዘባቸው ይረዱአቸው ነበር ። በአካባቢአ ቸውም ሕመምተኞች ቢኖሩ እየጠየቁ ያጽናኑአቸው፥ በሚቻላቸውም ሁሉ ይራሩላቸው ነበር ።

ከዚህ በፊት እንደ ሰማነው በስደት ጊዜአት ክር ስቲያኖች፥— ክፉ አድራጊዎች ፤ አጥፊዎች ፤ የአገር ጠላ ቶች እየተባሉ ይታሙ ነበር ። የቸርነትን ሥራዎች በመሥራታቸው ግን እንደዚህ ያለ ሐሜት ከእውነት የተለየ መሆኑን ያሳዩ ነበር ። ጥቂቶች ያልሆኑ አሕ ዛብ ይህን ነገር ስለ ተገነዘቡ መቃወማቸውን ትተው ወንጌልን አምነው ክርስቲያኖች ሆኑ ።

በቃል ብቻ ሳይሆን መልካም ሥራ በመሥራትም ክርስቲያኖች ሃይማኖታቸውን አስፋፉ ማለት ነው ።

ለምሳሌ አንድ የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ጸሐፊ እንደ ጻፉት ፤ በ፪፻፶ ዓ.ም. ገደማ የሮማ ቤተ ክርስ

ቲያን ብዙዎች አባሎችን አግኝታ ነበር ። ይህች ቤተ ክርስቲያን በቸርነት ሥራዎች የበረታች እንደ መሆንዋ መጠን ፩ሺ ፭፻ ለሚያህሉ መበለቶችና ችጋረኞች የገ ንዘብ እርዳታ ታደርግ ነበር ።

ጌታ ኢየሱስ፤—መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰ ማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ ብሎ የተናገረው ቃል በእ ነርሱ ሁኔታ በሥራ ተተረጐመ ። ማቴ. ፭ ፣ ፲፮ ።

በአገር ላይ የመሬት መንቀጥቀጥ ፣ ድርቅ ፣ ተላ ላፊ በሽታ ወይም ይህን የመሰለ የተፈጥሮ አደጋ በደ ረሰ ቍጥር ከአረመኔዎች ይበልጥ የተቸገሩትን የሚረ ዱአቸው ክርስቲያኖች ነበሩ ።

## ፱ ፤ በክርስቶስ ያመነ ድሀ ቢሞት የአካባቢው ምዕመናን የመቃብርን ቦታ ይፈልጉለት ነበር።

ገንዘብ ያለው ቤተሰብ በገንዘቡ ለሞተ ሰው የመ ቃብርን ቦታ ሊያዘጋጅለት ይችላል ። ድሆች ግን ይቸ ገሩበታል ። ስለዚህ ከምዕመናን መካከል ድሀ ቢሞት በሥርዐት እንዲቀበር ክርስቲያኖች ያስቡለት ነበር ።

በመጀመሪያ የመቃብርን ቦታ በማጣት ብዙዎች ክርስቲያኖች ሳይቸገሩ አልቀሩም ። ስለዚህ ከቤተ ክር ስቲያን አባሎች አንዱ ቢሞት ፣ በዬት እንቀብረዋ ለን የሚል ጥያቄ ይመጣል ።

አረመኔዎች በሚቀበሩበት ስፍራ መቅበር ጥሩ መንገድ መስሎ አልታየም ። ስለዚህ ክርስቲያኖች የራ ሳቸውን የመቃብር ቦታዎች ይፈልጉ ጀመር ። ከእነዚ ህም አንዱ ከሮሜ ከተማ በስተ ደቡብ ካታኩምባስ ከተባለችው ስፍራ አጠገብ የሚገኘው ነው ። የቦታው ስም ካታኩምባስ ስለ ተባለ የመቃብሩ ስፍራ ካታ ኮምብ ተብሎ ተሰይሞአል ።

ካታኮምብ በምድር ማኅፀን ውስጥ የተቆፈረ ፣ በጣም ጥልቅ የሆነ ፣ ሰው ሊተላለፍበት የሚችል ብዙ ዘወርዋራነት ያለው መንገድ ነው ። የመንገዶቹ ጠቅ ላላ ርዝመት እስከ ፱፻ ኪሎ ሜትር ይደርሳል ተብሎ ተገምቶአል ።

በእነዚህ ረጃጅም ቀሻዎች ውስጥ በግራና በቀኝ በኩል በግድግዳዎቹ ላይ እንደ መደብ ያሉ ቦታዎች ተቈፍረው ተደልድለው ነበር ። በእነዚህ መደቦች ላይ ክርስቲያኖች ሙታናቸውን ያኖሩአቸው ነበር ። አስከሬኑም በቦታው ካረፈ በኋላ በድንጋይ ይከደን ነበር ።

## ፲ ፤ ክርስቲያኖች ለባሪያዎች ቸርነትን ያደርጉ ነበር ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ፦ አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም ፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም ፥ ወንድም ሴትም የለም ፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ ብሎ ጽፎአል ። ገላ. ፫ ፥ ፳፰ ።

እንግዲህ በክርስቲያኖች እምነት ባሪያና ጨዋ ሰው አንድ ናቸው ።

በሮማውያን መንግሥት ውስጥ የባሪያ አገዛዝ የተለመደ መሆኑ የሚታወስ ነው ። የባሪያም መብት በሕግ የተጠበቀ ነበር ። የመንግሥትም ሕግ ስለሆነ ክርስቲያኖች በመሠረቱ የባሪያን መኖር ባይደግፉም ልማዱ እንዲሻር ማድረግ ለጊዜው ከአቅማቸው በላይ ሆነ ።

ነገር ግን ሕጉን ለመለወጥ ባይችሉም ባሪያዎችን በልዩ ልዩ መንገድ ለመርዳት መሞከራቸው አል ቀረም ። ሰብአዊ የሆነ መብታቸው በበለጠ እንዲጠበቅ ፥ ስለ እግዚአብሔር ብለው በቸርነት ዓይን ይመለከቱአቸው ነበር ።

አንዳንድ ጊዜም ፦ እግዚአብሔር የሚወድደው ሥራ ነው በማለት በሰው ቤት ከፉኛ የተሠቃዩ ባሪያዎች ነጻ ሆነው እንዲወጡ አብያተ ክርስቲያናት በገንዘባቸው አስፈላጊውን ወጪ ያደርጉ ነበር ።

ነጻነታቸውን ባገኙ ባሪያዎች መካከል በከፍተኛ ቦታ ቤተ ክርስቲያንን እስከ ማገልገል የደረሱ አሉ ። ለምሳሌ በሦስተኛው መቶ ዘመን ውስጥ በሮሜ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ የሆነው ካሊስቱስ ነጻነት የተሰጠው ባሪያ ነው ። ቤተ ክርስቲያን በጨዋ ሰውና በባሪያ መካከል ልዩነትን ላለማድረግዋ ይህ ታሪክ ማስረጃ ሊሆን ይችላል ።

ከፍ ብለው የሚታዩት ነጥቦች ቤተ ክርስቲያን በጥንት ዘመን አስደናቂ በሆነ ፍጥነት የተስፋፋችበትን ምክንያት ሊገልጡ ይችላሉ ። ክርስቲያኖች ትምህርታቸውን ራሳቸውንም በሚገባ ይጠብቁ ስለ ነበር በክርስቶስ ኃይል ወንጌል ተስፋፋ ።

## ጥያቄዎች ።

፩. በመከራ ጊዜ ክርስቲያኖችን የሚያበረታታ የክርስቶስ ቃል ምን የሚል ነው ?

፪. የክርስቲያኖች መልእክት ባላመነው ሕዝብ መካከል ተሰሚነትን ያገኘው በምን ምክንያት ነው ?

፫. የጥንት ዘመን ምእመናን የሃይማኖታቸውን ትምህርት በሥራ የተረጐሙት ምን ምን በመሥራታቸው ነው?

፬. ካታኮምብ የተባለው ስፍራ እንዴት ያለ ነበር?

## ምዕራፍ ሰባት ።

# በስደት ጊዜ ፈርተው ክርስቶስን የካዱትን ቤተ ክርስቲያን እንዴት አደረገቻቸው ?

## ሀ ፣ ተቸግረው ክርስቶስን የካዱት ብዙዎች ሆኑ ።

ባለፉት ምዕራፎች እንደ ተመለከትነው ክርስቲያኖች ስለ ሃይማኖታቸው በተሰደዱበት ጊዜ እስከ ምት ድረስ ታማኞች የሆኑ ፣ በደስታም ሕይወታቸውን የሠው በዛ ያሉ ናቸው ።

ከእነርሱ በመለየት ግን ከሥቃይና ከሞት እንዲተርፉ እምነታቸውን የካዱ ብዙዎች አሉ ። ይህም ሲሆን ስደት ካለፈ በኋላ በክሕደት በመውደቃቸው የተጸጸቱና ያዘኑ ይቅርታም ሊለምኑ የተነሡ በርከት ያሉ ናቸው ።

እንዲህ ከሆነ ይቅርታ በመለመን ሊመለሱ የሚፈልጉትን ቤተ ክርስቲያን ልትቀበላቸው ይገባታል ወይስ አይገባትም ?

በብዙ አገር በዚህ ጉዳይ ላይ የሐሳብ ልዩነት ና ክርክር ተፈጠረ ። በተለይ ክርስቲያኖች በዝተው በት በነበር በሰሜናዊ አፍሪካ ውስጥ ጉዳዩ ለሰፊ ክር ክር ምክንያት ሆነ ።

ለ ፡ <u>እንቀበላቸውም የሚሉ ነበሩ ።</u>

ክርስቶስን የካዱትን በፍጹም እንቀበላቸውም ፡ አንድ ጊዜ ከካዱ ውጭ መሆን አለባቸው ፡ ይቅርታ ቢለምኑም ወደ ቤተ ክርስቲያን አንድነታችን ልንመል ሳቸው አንችልም ፡ ብንቀበላቸው ቤተ ክርስቲያንን እንደ ማርከስ ይቈጠራል ፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ንጽሕት መ ሆን አለባት በማለት የተከራከሩ አሉ ። በእነርሱ አስ ተሳሰብ ከሐዲዎች ምናልባት ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ ለማግኘት ቢችሉም ወደ ፊት ክሕደትና ግድ የለሽነት እንዳይበዛ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስፍራ ሊኖራቸው አይቻልም ።

ሐ ፡ <u>ልንቀበላቸው ይገባናል የሚሉት አሸነፉ ።</u>

ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ግን ከዚህ አስ ተያየት በመለየት፡— ተሰድደው የካዱት ንስሐ በመግባት ቢመለሱ ቤተ ክርስቲያን ልትቀበላቸው ይገባታል ይሉ ነበር ። ይህም እንደ ጥንት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ደንብ ነበር ። አንድ የታወቀ ክርስቲያን ንስሐ ገብቶ ይቅርታ ቢለምን ጸሎት ያደርጉለትና ይቀበሉታል ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከጥንት ዘመን ጀምሮ የወ ደቁትን በዚህ ዓይነት ትቀበላቸው ነበር ።

ከዴሲዩስ ስደት በኋላ ግን ይህ ሥርዓት በሰሜ ናዊ አፍሪካ ፡ በተለይም ካርታጎ በተባለችው ከተማ በቂ መስሎ አልታየም ።

በነገሩ ስምምነት እንዲገኝ በ፪፻፶፩ ዓ. ም. በሮሜ ከተማ ፷ ጳጳሳት የተገኙበት ጉባዔ ተደረገ ። በስፊ ውም ከተወያዩበት በኋላ፡— በስደት ጊዜ ሞትን በመ ፍራት ክርስቶስን የካዱትን ሰዎች እንደ ገና ወደ ቤተ ክርስቲያን አንድነታችን ልንመልሳቸው እንችላለን ብለው ተስማሙ ። ንስሐ ቢገቡ ማለት ነው ። በዚህም ውሳኔ እንቀበላቸውም የሚሉት ተረቱ ።

የሆነ ሆኖ ፦—ይቃርታ የሚለምን ሰው ቢኖር ይቅርታ ሊያደርግለት የሚችል ጳጳሱ ብቻ ነው አሉ ። እንደ አዲስ ኪዳን ሥርዓት የሆነ እንደ ሆነ ግን እንዲህ ማለት አያስፈልጋቸውም ነበር ። ምክንያቱም በያሉበት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉ ይህንን ለማድረግ ይችላሉ ።

## ምዕራፍ ስምንት ።

# ለክርስቲያኖች ሙሉ ነጻነት ተሰጣቸው ።

### ሀ ፣ ስለ ክርስትና የመንግሥት ሕግ ተለወጠ ።

የመጨረሻውን ታላቅ ስደት ያስጀመረው ዲዮክሌቲያኑስ ቄሣር ክርስቲያኖችን ለመደምሰስ ቢሞክርም አለመቻሉን ሰምተናል ። በመንግሥት ሥራ ደክሞት በ፫፻፭ ዓ. ም. በፈቃዱ ለቅቆ ለሌላ አስረከበው።

ተከታዮቹ የሆኑት ቄሣሮችም እንደ ፊተኞቹ የክርስትናን ሃይማኖት ለማጥፋት ሞከሩ ። ግን አቃታቸው።

በ፫፻፲፫ ዓ. ም. በሥልጣን የሚወዳደሩትን ካሸነፋቸው በኋላ በሮሜ መንግሥት ቄሣር የሆነ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ነው ። እርሱም ከሌሎች ቄሣሮች በመለየት ክርስቲያኖችን የሚወድና የሚደግፍ ሆነ ።

ልዩ ታሪክ ስለ እርሱ ይነገራል ። ጠላትን ለማሸነፍ ወታደሮቹን አስከትሎ ወደ ዘመቻ በሄደበት ጊዜ በድንገት እንደ ፀሐይ የሚያበራ መስቀል በሰማይ ጠፈር ላይ ታየው ። ከመስቀሉም ከፍ ብለው፦—በዚህ ምልክት አሸንፍ የሚሉ ቃላት ይታዩ ነበር ። ጌታም ተገልጦለት የመስቀል ምልክት ያለበትን አርማ እንዲያዘጋጅ አዘዘው ። ይህንንም አደረገና አርማውን ወደ ጦር ግንባር ይዞት ቢሄድ አሸናፊ ሆኖ ወጣ ይባላል ።

ቆስጠንጢኖስ ሥልጣን በጨበጠ ጊዜ ለክርስቲያኖች ሙሉ ነጻነት አሳወጀ ። ክርስቲያን መሆን በሕግ የተፈቀደ ነገር ሆነ ማለት ነው ። በስደት ጊዜ የተወረሰው የክርስቲያኖች ንብረት እንዲመለስላቸው ተወሰነ ። እንደ ገናም አብያተ ክርስቲያናትን ለመሥራት

ተቻለ ። ክርስቲያኖችም እንደ ሰንበት አድርገው የሚያ ከብሩት የእሑድ ዕለት በመንግሥት አዋጅ የእረፍት ቀን ሆነ ።

## ለ ፣ የመንግሥት ድጋፍ ያስከተለው አደገኛ ነገር ።

ይህን በመሳሰሉ ሕግጋት የሮሜ መንግሥት ባለ ሥልጣኖች ክርስቲያኖችን ይደግፉአቸው ጀመር ። ክርስቲያንም መሆን የተናቀ ነገር ሳይሆን ክብርን የሚያስገኝ ነገር ሆነ ። ቄሶች ከመንግሥት የገንዘብን እርዳታ አገኙ ። ለአብያተ ክርስቲያናትም ልዩ ልዩ የገንዘብ ስጦታ ተሰጠ ።

ነገር ግን ይህ ድጋፍ ሁሉ በአንድ በኩል የሚያ ስደስት መስሎ ቢታይም በቤተ ክርስቲያን ላይ አደ ገኛ ነገር ሳያስከትልባት አልቀረም ። እንደምን ቢሉ ፣ ጥቂቶች ያልሆኑ ሰዎች መንግሥት ለቤተ ክርስቲያን ደጋፊ መሆኑን በተመለከቱ ጊዜ ክርስቲያን መሆን ይጠቅማል እያሉ ያስቡና እንዲሁ ለሥጋዊ ጥቅም ብቻ ሲሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጕረፍ ጀመሩ ። ከዚ ህም የተነሣ በእውነት በልባቸው ክርስቲያኖች ሳይ ሆኑ በስም ብቻ ወይም በግብዝነት የክርስትናን ሃይማ ኖት የተቀበሉት ብዙዎች ሆኑ ።

ቆስጠንጢኖስ በልዩ ልዩ መንገድ ክርስቲያኖ ችን የሚደግፍ ቢሆንም ራሱ ሙሉ ክርስቲያን አል ሆነም ። ለጥምቀት የሚያስፈልገውን ትምህርት ያገ ኘው በ፫፻፲፪ ዓ. ም. ገደማ ነው ። ነገር ግን በዚያን ጊዜ አልተጠመቀም ። ጥምቀትን የተቀበለው ታምሞ ወደ ሞት አቅራቢያ ከደረሰ በኋላ ነው ። ተጠምቆም ጥቂት ቀን ከቆየ በኋላ በ፫፻፴፯ ዓ. ም. ሞተ ።

## ምዕራፍ ዘጠኝ ።

## ዩሊያኑስ ከሐዲ ።

### ሀ ፤ አረመኔነትን በሕግ ሊመልስ ሞከረ ።

ከአንድ ሰው በቀር ከቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት በኋላ ይገዙ የነበር ቄሣሮች የክርስትናን ሃይማኖት ይደግፉ ነበር ። አረመኔነትንም ይቃወሙ ነበር። በሕግም ሳይቀር አረማዊነት እንዲጠፋ ለማድረግ ይሞክሩ ነበር ።

የቆስጠንጢኖስ የወንድሙ ልጅ ዩሊያኑስ ግን የዚህ ዓይነት ሰው አልነበረም ። የክርስትናን ሃይማኖት ትምህርት በልጅነቱ ጊዜ ተምሮ ነበር ። ቄሣርም ክርስቲያኖችን ይደግፋቸው ስለ ነበር ዩሊያኑስም በግዳዊ በኩል ትምህርቱን የተቀበለ ይመስል ነበር ። ነገር ግን ከልቡ አይደለም ።

በልጅነቱ ጊዜ ከወንድሙ በቀር ዘመዶቹ ሁሉ ተገድለው ነበርና በዚህ ሁሉ ምክንያት ክርስቲያናችን ጠላቸው ። የጥንታውያን አባቶች የልዩ ልዩ አማልክት እምነት የተሻለ መስሎ ታየው ።

ስለዚህ ዩሊያኑስ ራሱ ቄሣር በሆነ ጊዜ የክርስትናን ሃይማኖት ለማጥፋት የጥንቱንም የአሕዛብን ሃይማኖት እንደ ገና ለመቀስቀስና የመንግሥት ሃይማኖት ለማድረግ ኃይሉን ሁሉ ሰብስቦ ተነሣ ። ይህንን የሞከረው ግን እንደ ሌሎቹ ቄሣሮች ክርስቲያኖችን በማስያዝና በማስገደል ሳይሆን ፥ የቤተ ክርስቲያንን ሥራ ለመጉዳት የሚችሉትን ሕግጋት በመደንገግ ነው።

ለምሳሌ ክርስቲያኖች በከፍተኛ ደረጃ እንዳያስተምሩ በሕግ ከለከላቸው ። ክርስቲያኖችን ይንቃቸው ነበር ። ገሊላውያን እያለ ያፌዝባቸው ነበር ። ለቤተ ክርስቲያንም የትምህርት ሥራ እንቅፋት ለመፍጠር ሲል የሐሰት አስተማሪዎችን ይደግፋቸው ነበር ።

ከጥንት ጀምሮ ያላመኑ አይሁድ ክርስቲያኖችን ይጠሉ ነበር ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንን ለመጉዳት አይሁድን ደገፈ ። እነርሱም በኢየሩሳሌም ውስጥ ቤተ መቅደስን እንደ ገና እንዲሠሩ ፈቀደላቸው ።

## ለ ፡ ገሊላዊው አሸነፈው ።

ዩሊያኑስ ሁለት ዓመት ብቻ ነገሠ ። ይኸውም ከ፫፻፷፩ እስከ ፫፻፷፫ ዓ. ም. ነው ። በዚህም አጭር ጊዜ ውስጥ ያደረገው የሃይማኖት ጥረት ሁሉ ሳይሳካለት ቀረ ። አሮጌው የአምልኮ ሥርዓት እየሞተ ሄደ ። የክርስትና ሃይማኖትም በዚሁ መጠን እተስፋፋ መሄዱን ቀጠለ ።

በሞተበት ዕለት በክርስቲያኖች ላይ ያደረገው ዘመቻ ሁሉ ከንቱ መሆኑ ተሰምቶት፡— እንግዲህ አሸንፈሃል አንተ ገሊላዊ ብሎ ተናገረ ይባለል ። ገሊላዊ ማለቱ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው ።

እውነቱን ነው ፡ ቄሣር የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ለማፍረስ አልቻለም ።

የክርስትናን ሃይማኖት ከተማረ በኋላ የአረመኔነት ደጋፊ ሆኖ ስለ ተነሣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ዩሊያኑስ ከሐዲ የሚለውን አሳዛኝ ስም አትርፎአል ። እርሱ ከሞተ በኋላ የአረመኔነትን አምልኮ የደገፈ ቄሣር ሁለተኛ አልተነሣም ።

## ጥያቄዎች ።

፩. በተሰደዱ ጊዜ በፍርሃት ተይዘው ሃይማኖታቸውን የካዱት ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የፈጠሩት የሐሳብ ልዩነት እንዴት ያለ ነበር ?

፪. ንስሐ የገቡትን ከሐዲዎች እንዴት ብናደርጋቸው ይሻላል ? በሚለው ጥያቄ ላይ በመጨረሻ ምን ተብሎ ተወሰነ ?

፫. ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ቄሣር ሆኖ ክርስቲያኖችን በሕግ መደገፉ ቤተ ክርስቲያንን የሚጠቅም ሆነ ወይስ የሚጎዳ ?

፬. የዩሊያኑስ ስደት ከፊተኞች ቄሣሮች ልዩ ሆኖ የተገኘው በምንድር ነው?

፭. ዩሊያኑስ በሞተ ጊዜ ምን ብሎ ተናገረ ይባላል ?

## ምዕራፍ አሥር ።

# ክርስትና በኢትዮጵያ ስለ መግባቱ።

### መግቢያ ።

እስከ አሁን ያነበብነው ታሪክ የክርስትና ሃይማኖት በጥንታዊው በሮሜ መንግሥት ውስጥ መስፋፋቱን የሚተርክ ነው ። በሜዲቴራኔ ባሕር ዙሪያ ያሉት አገሮች በሙሉ በሮሜ ቄሣር ሥልጣን ሥር የሚተዳደሩ ነበሩ ።

ክርስትናም በቆስጠንጢኖስ ዘመን የመንግሥት ሃይማኖት ከመሆኑ በፊት ይህ ሃይማኖት በእነዚህ አገሮች ውስጥ በመጠኑ ተሰብኮና ታውቆ ነበር ። ከቆስጠንጢኖስ በኋላም ወንጌል እየተሰበከ መስፋፋቱን ቀጠለ ።

ነገር ግን ክርስትና ጥንት ሥር የሰደደው በሮሜ አገሮች ውስጥ ብቻ አይደለም ። ወደ ብዙዎች ሌሎችም አገሮች ተዳርሶአል ።

በምሥራቅ በኩል የወንጌል መልእክተኞች እስከ ፋርስ እስከ ሕንድ አገርም ደርሰዋል ። ወደ ደቡብም የክርስትና ሃይማኖት በአረብ አገር ተሰብኮ አብያተ ክርስቲያናት ተመሥርተዋል ። ከአረብ አገርም አልፎ የክርስቶስን ወንጌል የሰበኩ ሰዎች ወደ ጥንታዊትዋ ኢትዮጵያም መድረሳቸው ታውቆአል ።

ከዚህ ቀጥለን ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ስለ መድረሱ እናናባለን ።

### ሀ ፣ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ።

### ስለ አገሩ ።

ከዚህ በፊት እንደ ሰማነው በሐዋርያት ዘመን አንድ ኢትዮጵያዊ ሰው ለእግዚአብሔር ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ ። ይህ ሰው ከወንጌላዊው ፊልጶስ ጋር እንዲገናኝ እግዚአብሔር አደረገ ። ወንጌላዊውም

የክርስቶስን ወንጌል አስተምሮት አሳመነው ። በእጁም ተጠምቆ ኢትዮጵያዊው ደስ ብሎት ወደ አገሩ ተመለሰ ። የሐዋ. ፰ ፥ ፳፮—፴፱ ።

በሐዋርያት ሥራ እንደ ተጻፈ ይህ ሰው ከኢትዮጵያ ንግሥት ዘንድ ከፍተኛ ሹመት ነበረው ። በገንዘብዋ ሁሉ የሠለጠነ ነበር የሚል ቃል ተጽፎለታል ። ዘመናዊ በሆነ አነጋገር የንግሥቲቱ የህንደኬ የገንዘብ ሚኒስትር ነበር ለማለት እንችላለን ።

በዚህ ታሪክ ላይ ኢትዮጵያ የተባለችው አገር በዘመናችን ኢትዮጵያ ተብላ ከምትጠራው አገር ትንሽ የተለየች ሳትሆን አትቀርም ። የታሪክ መርማሪዎች እንደ ገመቱት የህንደኬ አገር በስተ ሰሜን በኩል የኢትዮጵያ አዋሳኝ የነበረች ፥ ኑባ የተባለችው አገር ትሆናለች ። የመናገሻ ከተማዋም መርዌ ትባል ነበር ።

በዚህ አስተሳሰብ በመጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከግብፅ በስተ ደቡብ ያለውን አገር ያመለክት ነበር ማለት ነው ።

## ኢትዮጵያዊው ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ ምን ሆነ?

ጃንደረባው ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ ስለ ክርስቶስ የተማረውን ትምህርት ሌሎችም እንዲሰሙትና እንዲያውቁት ምን ምን እንደ ሠራ አይገልጥልንም ። ከፍተኛ የመንግሥት ሹመት ያለው ሰው እንደ መሆኑ መጠን ግን ሌሎች ስለ አዲሱ እምነት እንዲሰሙ ለማድረግ ችሎአል ብለን ብንገምት ስሕተት አይመስልም ።

ኤቭሴቢዮስ የተባለው በጥንት ዘመን ይኖር የነበር የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ጸሐፊ ስለ ጃንደረባው እንዲህ ብሎ ጽፎአል ።

ከፊልጶስ የእግዚአብሔርን ቃል ምሥጢር ከሰሙት አሕዛብ መካከል የመጀመሪያ ሆኖ የተቀበለው እርሱ ነው ። ሐዋርያው በራእይ ተመርቶ አስተማረው ። እርሱም ከትልቁ ዓለም የመጀመሪያ የእምነት ፍሬ ሆኖ ወደ አገሩ ተመልሶ ፥ ስለ እግዚአብሔር እውቀት ፥ መድኃኒታችንም ለደኅንነታችን ሲል በመካከላችን ማደ

ሩን ተናግሮአል ይባላል ። ስለዚህ ፣ ኢትዮጵያ እጆች ዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚለው ትንቢት በእርሱ አማካይነት ፍጻሜ አግኝቶአል ለማለት ይቻ ላል ።

ከፍ ብለን እንዳመለከትነው ግን በጃንደረባው ምስክርነት ወይም ስብከት ምን ያህል ሰው እንዳመነ ታሪክ ስለማይገልጥልን ለማወቅ አልተቻለም ።

በጥንታዊትዋ ኢትዮጵያ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እስከ አራተኛው መቶ ዘመን ድረስ ይነግሡ የነበር ነገሥታት አረማውያን እንደ ነበሩ ለማረጋገጥ ተች ሎአል ።

ለ ፣ ስለ አክሱም መንግሥት ሃይማኖት ክርስትና ከመ ግባቱ በፊት ።

የአክሱም መንግሥት እንደ ዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሰፊ አልነበረም ። በአክሱም አካባቢ ያሉትን ክፍለ አገ ሮች ብቻ ያቀፈ ነበር ። መናገሻ ከተማውም እስከ ዛሬ ድረስ ታዋቂነት ያላት አክሱም ናት ። ነገሥታት ዋም በዘመናቸው ስመ ጥሩዎችና ገናናዎች ነበሩ ።

ከፍ ብለን እንደ ጻፍነው እስከ አራተኛው መቶ ዘመን ድረስ አረመኔዎች ሆነው ልዩ ልዩ አማልክ ትን ያመልኩ ነበር ። በእባብ ያመልኩ ነበር ፣ እንዲ ሁም የጨረቃ ፣ የፀሐይ ፣ የምድርም እያሉ ልዩ ልዩ አማልክትን በመጥቀስ ይሰግዱላቸው ነበር ። በጥንታ ውያን የድንጋይ ሐውልቶች ላይ የተገኙ ጽሑፎች ለዚህ ነገር ማስረጃ ሊሆኑ ይችላሉ ።

ከዚህ ሌላ ክርስትና በኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት የአይሁድ ሃይማኖት አልፎ አልፎ ታውቆ እንደ ነበር ለማመን የሚቻል ይመስላል ። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ቢባል የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ከአ ይሁድ ጋር ግንኙነት በማድረጉ ነው ብንል ከእውነት የራቀ አይሆንም ።

እንደ ኢትዮጵያ አፈ ታሪክ የሆነ እንደ ሆነ ንግ ሥተ አዜብ ከኢትዮጵያ ተነሥታ ንጉሥ ሰሎሞንን ለመጎብኘት ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘች ። ከእርሱም

ልጅ ወለደች ። ልጁም ምኒልክ ተባለ ። እርሱም ከደገ በኋላ አባቱን ሰሎሞንን ሊያየው ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ። ተመልሶም ሲመጣ ታቦትን ፣ እንዲሁም የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንን ይዞ መጣ ። እነርሱም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የአይሁድን ወይም የኦሪትን ትምህርት ያስተምሩ ጀመር ።

የኦሪት ትምህርት በኢትዮጵያ ሊገባ የቻለው በዚህ አኳኋን ነው ይባላል ።

የዘመናችን የታሪክ መርማሪዎች ከዚህ የተለየ ውን አስተያየት ያቀርባሉ ። ከጥንት ዘመን ጀምሮ በደቡብ ግብጽ አገር ፣ እንዲሁም በደቡብ አረብ ውስጥ አይሁድ ይኖሩ እንደ ነበረ ታውቆአል ። ይህም ሲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ አንዳንድ የአይሁድን ሃይማኖት ልማድ ሊለምድ የቻለው ከእነዚህ አይሁድ ጋር በተደረገው መተዋወቅና ግንኙነት ሳይሆን አይቀርም ብለው አስበዋል ።

ያም ሆነ ይህ እስከ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ወይም ከኦሪት የተገኙ አንዳንድ ልማዶች ሲሠራባቸው መቆየታቸው ታውቆአል ።

## ሐ ፣ የአክሱም መንግሥት ክርስቲያን ሆነ ።

ክርስትና በኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት በሰፊውም ባይሆን አልፎ አልፎ የኦሪት ሃይማኖት መታወቁ ቢታመንበትም የአክሱም ነገሥታት አረማውያን መሆናቸው ግልጽ ነው ። በአራተኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ ዙፋኑን ወርሶ ይገዛ የነበረው ኢዛና ወይም አብርሃ የተባለው ንጉሥ ነው ። ከዘመነ መንግሥቱ የመጀመሪያው ክፍል የተገኙት የሐውልት ቅርጾች እንደ ሚያስረዱን አረማዊ ነበር ። ራሱን ፣ "የመሕርም ልጅ" እያለ ይጠራ ነበር ። "መሕርም" የሚለው ቃል የጨረቃ አምላክ የሚጠራበት ስም ነበር ። "የመሕርም ልጅ" ማለቱም በዚያን ጊዜ በጨረቃ ማምለኩን ያሳያል ።

በ፫፻፴ ዓ. ም. ገደማ ግን ኢዛና ሃይማኖቱን እንደ ለወጠ ለማረጋገጥ ተችሎአል ። ከዘመነ መንግሥቱ የመጨረሻው ክፍል የተገኙት የሐውልት ቅርጾች እን

ድሚያሳዩን ፣ የመሕርም ልጅ መባልን ትቶ ፣ የሰማይ ንና የምድርን ጌታ የእግዚአብሔርን ስም ይጠቅሳል ። ይህም አረመኔነትን ትቶ እውነተኛውን አምላክ እስከ ማምለክ መድረሱን ያሳያል ።

ለዚህም ተጨማሪ ማስረጃ የሚሆነው የመስቀል ምልክት ነው ። በዘመነ መንግሥቱ መጀመሪያ ላይ በሐ ውልቶችና በገንዘቦች ላይ ያስቀረጸው ምልክት አረማ ዊነቱን የሚገልጥ የጨረቃ ምልክት ሲሆን በመጨ ረሻው የክርስቲያን ምልክት በሆነ በመስቀል ተተካ ።

ስለዚህ ክርስትና በኢትዮጵያ የገባው በንጉሥ ኢዛና ዘመነ መንግሥት መሆኑ ተደርሶበታል ። ይህም የሆነው በ፫፻፴ ዓ. ም. ገደማ ነው ተብሎ ተገምቶ አል ።

ከዚህም ጋር የኢትዮጵያ አፈ ታሪክ ሊስማማ ይች ላል ።

## መ ፣ የፍሬምናጦስና የአድስዮስ ታሪክ ።

በኢትዮጵያ የታሪክ መጻሕፍት ላይ እንደምናነ በው የክርስትና [illegible] ታሪክ በአጭሩ ቀጥሎ እንደ ተጻፈ ነው ።

<u>መሮጵዮስ</u> የሚባል የግሪክ አገር ነጋዴ ነበር ። በመርከብ ከሌሎች መርከበኞች ጋር ለንግድ ወደ ሕንድ አገር ለመድረስ ተነሣ ። እነርሱም በመንገድ ላይ በኤ ርትራ ባሕር ወደብ ገብተው ትንሽ እንደ ቆዩ ጠላት ተነሥቶባቸው ከሁለት ልጆች በስተቀር ሁሉንም ገደሉ ። የአገሩ ሕዝብ ለወጣቶቹ አዝነው በሕይወት እንዲኖሩ ፈቀዱላቸው ።

ልጆቹ ክርስቲያኖች ናቸው ። የአንዱ ስም ፍሬ ምናጦስ ፣ የሁለተኛውም አድስዮስ ነው ። ሁለቱም ወደ አክሱም ንጉሥ ተወሰዱ ። ይህ ከሆነ በኋላ ግን ብዙ ጊዜ ሳያልፍ ንጉሡ ሞተ ። ንግሥትም የመንግ ሥት ሥራ ከባድ ሆኖባት አልጋ ወራሽ እስኪያድግ ድረስ ፍሬምናጦስና አድስዮስ በአገር ቆይተው መን ግሥትን በማስተዳደር እንዲረዱአት ለመነቻቸው ። እነርሱም ለዚህ ነገር ፈቃደኞች ሆነው ሥራቸውን ጀመሩ ።

በዚህ መካከል በተለይ ፍሬምናጦስ የኢትዮጵያን ሕዝብ በክርስትና ሃይማኖት የማስተማር ጥሪ ተሰማው ። ስለ ክርስቶስም መመስከርን ጀመረ ። አልጋ ወራሹም ክርስቲያን ሆነ ።

ጊዜ ካለፈ በኋላ ፍሬምናጦስ የክርስትና ሃይማኖት በበለጠ እንዲስፋፋ በማለት ከኢትዮጵያ ተነሥቶ ወደ እስክንድሪያ ተጉዞ በዘመኑ የእስክንድሪያ ጳጳስ የነበረውን አትናቴዎስን ፈልጎ ለኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲሾምላት ለመነው ። አትናቴዎስም በጉዳዩ ፍሬምናጦስን ካነጋገረ በኋላ ከእርሱ የተሻለ የለም በማለት የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ጳጳስ እንዲሆን መርቆት ወደ ኢትዮጵያ መልሶ ላከው ።

ፍሬምናጦስም ለተጠራው ከፍተኛ አገልግሎት ፈቃደኛ ሆኖ ክርስትናን በኢትዮጵያ ለማስፋፋት ወደ አገሩ ተመልሶ መጣ ። ስብከቱንም ማስተማሩንም ቀጠለ ።

በኢትዮጵያ ታሪክ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ተብሎ ተሰይሞአል ። ትርጉሙም ብርሃንን የገለጠ የሰላም አባት የሚል ነው ።

አልጋ ወራሽ ካደገ በኋላ በንግሥት ፈቃድ ወደ አገሩ ለመመለስ ይችል ነበር ። ነገር ግን አልተመለሰም ። የወንጌል ሥራ ጥሪ ተሰምቶት በኢትዮጵያ ውስጥ መኖርን መረጠ ። አድስዮስ ግን ወደ አገሩ ተመልሶ ገባ ።

ከፍ ብሎ በአጭሩ የተጠቀሰው ታሪክ አፈ ታሪክ ቢሆንም ትክክለኛ ነገር እንደሚኖርበት ይታመናል። ፍሬምናጦስ በ፫፻፶ ዓ.ም. ገደማ በእርግጥ ጳጳስ እንደ ነበር በሌላ በታሪክ ማስረጃ ለማረጋገጥ ተችሎአል ።

### ሠ ፡ ክርስትና እየተስፋፋ ሄደ ።

ፍሬምናጦስ ካረፈ በኋላ ሚናስ የተባለው ሰው የኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲሆን ተመረቀ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አቡን ተብሎ የሚጠራው የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ ዘወትር ከግብጽ አገር ቤተ ክርስቲያን ይመጣ ነበር ። ይህም እስከ ዘመናችን ድረስ የቆየ ልማድ ሆነ።

እንደ አውሮጳ አቈጣጠር በ፲፱፻፶፩ ዓ. ም. ግን የኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በትውልዱ ኢትዮጵያዊ የሆነውን የራስዋን አቡን አገኘች ።

በተረፈ ፥ ከፍሬምናጦስ ዘመን በኋላ ስለ ሆነው ታሪክ ብዙ እውቀት የለንም ። በአገር ውስጥ የእግ ዚአብሔር ቃል እየተስፋፋ መሄዱን ለማመን እንች ላለን ። የኢትዮጵያ ታሪክ እንደሚተርከው ተስዓቱ ቅዱሳን ወይም ዘጠኙ ቅዱሳን ተብለው የተሰየሙ መነኰሳት ከሶርያና ከሌሎችም አገሮች መጥተው የወ ንጌልን ስብከት ቀጠሉ ። አብያተ ክርስቲያናትም ተሠሩ ። ከዚህም ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ወደ ዘመኑ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተተረጐመ ።

መጽሐፍ ቅዱስ በአገሩ ቋንቋ ተጽፎ መገኘቱ ለምዕመናን ከፍ ያለ ጥቅም እንደ ሰጠ ያለ ጥርጥር ለማመን እንችላለን ። ይህ ታላቅ ሥራ በምን ጊዜ እንደ ተጀመረ ፥ ከፍጻሜም የደረሰው በምን ጊዜ እንደ ሆነ በትክክል ለማወቅ አልተቻለም ። ሆኖም በ፭፻ እና በ ፮፻ ዓ.ም. መካከል የተፈጸመ ሥራ ነው ተብሎ ታስ ቦአል ። ይህም ሲሆን የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ ረጅም ዕድሜ ያለው መሆኑ ታውቆለታል ።

በዚህ መጽሐፍ አማካይነት ፥ እንዲሁም በክርስቲ ያኖች ስብከትና ምስክርነት ቀስ በቀስ የክርስትና ሃይማኖት በአገር ውስጥ እየተስፋፋ ሄደ ። በዘመን ብዛ ትም የክርስቲያን አገር ወደ መባል ተለወጠ ።

ጥያቄዎች ።

፩. በሐዋርያት ሥራ በምዕራፍ ፰ የተጠቀሰው ኢት ዮጵያዊ የመጣበት አገር የትኛው ይሆናል?

፪. ክርስትና በኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት የሕዝቡ አምልኮ እንዴት ነበር ?

፫. ክርስትና በኢትዮጵያ የገባው በማን ዘመነ መን ግሥት ነው?

፬. ንጉሡ ክርስቲያን የሆነው በስንት ዓመተ ምሕ ረት ገደማ ይሆናል ?

፭. ፍሬምናጦስ በኢትዮጵያ ታሪክ ማን ተባለ ?

፮· በኢትዮጵያ ታሪክ ተሰዓቱ ቅዱሳን እንዴት ያሉ ሰዎች ነበሩ ?

፯· የጥንቱ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ቋንቋ የትኛው ነው?

፰· ንባብ የሚችሉት ምዕመናን ሁሉ በሚያውቁት ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንዴት ያለ ጥቅም ይሰጣቸዋል ?

ምዕራፍ አሥራ አንድ ።

## የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና እምነት።

የክርስቶስ ሐዋርያት ንጹሕ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማሩ ሰውን ወደ እምነት በመምራት በየስፍራው አብያተ ክርስቲያናትን ይመሠርቱ ነበር ። እነዚህም አብያተ ክርስቲያናት ስሕተት በሌለበት በሐዋርያት ትምህርት ላይ የተመሠረቱ ስለ ሆኑ እምነታቸውም ሆነ ሥርዓታቸው በእኛም ዘመን ላሉት ቤተ ክርስቲያን አብነትና ምሳሌ ሊሆን ይችላል ።

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ሥርዓት እንዴት ቢሆን ይሻላል ብለን ብንጠይቅ ከሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ብንማር ከስሕተት ያስጠብቃል ።

የሐዋርያት ዘመን ካለፈ በኋላ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአንዳንድ ነገር ከሐዋርያት ንጹሕ ትምህርት እየራቁ ስለ ሄዱ የተሳሳቱበት ነገር አይጠፋም ። ስለ ዚህ በትምህርት ወይም በቤተ ክርስቲያን አመራር በኩል ከስሕተት እንድንጠበቅ የአዲስ ኪዳንን መምሪያ መከተል በጣም አስፈላጊአችን ነው ።

አስቀድመን ቤተ ክርስቲያንን ስለ ማገልገል አዲስ ኪዳን የሚናገረውን እንመልከት ።

ለምዕመናን ሁሉ የጸጋ ስጦታ ተሰጥቶአል ።

ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት አገልግሎትን ሊያበረክት የሚችል ማን ነው? የሐዋርያትን ትምህርት መሠረት በማድረግ — ክርስቲያን ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ለማ

ጠንክርና ለማስፋፋት የሚያበረክተው አገልግሎት አለው ብለን እንመልሳለን ። ሐዋርያው ጴጥሮስ ፣ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ ብሎ ጽፎአል ። ፩ ጴጥ. ፬ ፣ ፲ ።

ክርስቲያን ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የተቀበለ እንደ መሆኑ መጠን ከዚህ መንፈስ የጸጋን ስጦታ አግኝቶአል ። ይህም የቤተ ክርስቲያንን ሥራ ለማስፋፋት የሚያስችል ስጦታ ነው ። እንደ ስጦታው የሚሰብክ ፣ የሚያስተምር ፣ የሚመክር ፣ የሚዘምር ፣ የሚጸልይ ፣ በጉልበቱም በገንዘቡም ወይም በማንኛውም በሌላ መንገድ የሚረዳ ሰው አለ ። ስለዚህ ክርስቲያን ሁሉ እግዚአብሔር እንደ ሰጠው መጠን የእግዚአብሔር ቃል እንዲስፋፋ ማገልገል አለበት ። ክርስቲያን ሁሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነው ።

ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ግን ልዩ የአገልግሎት ጥሪ የደረሳቸው ሰዎች እንደሚኖሩ በአዲስ ኪዳን ለመመልከት እንችላለን ። ከዚህ ቀጥለን ዋና ዋናዎቹን እንጠቅሳለን ።

ሀ ፣ ሐዋርያት ።

ሐዋርያት በሚለው ስም ይጠሩ የነበር ክርስቶስ የጠራቸው ፣ ከእርሱም ጋር እየተመላለሱ ያደረገውን ሁሉ በዓይናቸው ያዩ ፣ የተናገረውን በጆሮአቸው የሰሙ ደቀ መዛሙርቱ ናቸው ። ከእነርሱም ሌላ ጳውሎስ ልዩ በሆነ መንገድ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ተገናኘ ። ቃሉም ልዩ በሆነ አገላለጥ የተገለጠለት በመሆኑ ሐዋርያ ተብሎ ሊጠራ ቻለ ። ሮሜ ፩ ፣ ፩ ። ሐዋርያ የሚለው ስም ይህን ለመሰለ ሰው ብቻ የተሰጠ ነው ። ስለዚህ እኛ ባለንበት ዘመን በእግዚአብሔር ቃል የሚያገለግሉ ሐዋርያት አይባሉም ።

ሐዋርያት የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰብኩና እንዲያስተምሩ የተጠሩ ነበሩ ። ማቴ. ፳፰ ፣ ፲፰—፳ ። የሐዋ. ፮ ፣ ፪—፬ ።

ለ ፡ ነቢያት ።

ነቢያት ከመንፈስ ቅዱስ የተገለጠላቸውን የእ ግዚአብሔርን ቃል ወይም መልእክት ይናገሩ ነበር። የሐዋ. ፲፩ ፡ ፳፰ ፤ ፳፩ ፡ ፲ — ፲፩ ። ነቢያት ቢባሉም ግን ሰዎች ናቸውና ሊሳሳቱ ይችላሉ ። ከዚህም የተነሣ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ጻፈው ሁሉ ምዕመናን ከነ ቢዩ የሚሰሙት ነገር ትክክለኛ እንደ ሆነ መለየት ያስፈልጋቸዋል ። ይህም ማለት ነቢይ የተባለው ሰው ክርስቶስና ሐዋርያት የብሉይ ኪዳን ነቢያትም ከተና ገሩት የተለየውን ነገር ሲናገር የተገኘ እንደ ሆነ መልእክቱን ከመንፈስ ቅዱስ እንዳልተቀበለው ይታ ወቅበታል ። ፩ ቆሮ. ፲፬ ፡ ፳፱ ።

ለክርስቲያን ዓይነተኛው መመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው ። ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር እንደ ተባለ ፤— መል እክት አለኝ የሚል ሰው ቢኖር ምዕመናን በእግዚአ ብሔር ቃል ተመርተው ሊመረምሩት ያስፈልጋቸዋል። ፩ ጴጥ. ፬ ፡ ፲፩ ።

ሐ ፡ አስተማሪዎች ።

አስተማሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተ ምሩ ናቸው ። በስብከት ብቻ ሳይሆን በትምህርት መልክ የቃሉን ምሥጢር አብራርተው የሚገልጡ ናቸው ። ፩ ቆሮ. ፲፪ ፡ ፳፰ ። ሮሜ ፲፪ ፡ ፯ ።

መ ፡ ወንጌልን ሰባኪዎች ።

በሕዝብ መካከል እየተዘዋወሩ ፡ ወንጌል ወዳል ደረሰበት አገር እየደረሱ ቃለ እግዚአብሔርን የሚሰ ብኩ ሰዎች ናቸው ። በዚህ ነገር ወንጌላውያን ከሐዋ ርያት ጋር ሊመሳሰሉ ይችላሉ ። ኤፌ. ፬ ፡ ፲፩ ። ፪ ጢሞ. ፬ ፡ ፭ ። የሐዋ. ፳፩ ፡ ፰ ።

ሠ ፡ ሽማግሌዎች ።

ሐዋርያት በየስፍራው ወንጌልን በመስበክ አብያተ ክርስቲያናትን ከመሠረቱ በኋላ ሽማግሌዎችን እንደ ሾሙላቸው በታሪኩ ተጽፎአል ። የሐዋ. ፲፬ ፡ ፳፫ ። የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በግሪክ ቋንቋ ጵሬስቢቴሮስ ወይም ኤጲስቆጶስ ይባላል ። ይህ የስም ልዩነት ብቻ ነው ። ሁለቱም ስሞች የሚያመለክቱት የቤተ ክርስቲያንን የሽማግሌ አገልግሎት ነው ። ኤጲስቆጶስ ማለት በኃላፊነት አንድ ሥራ የሚመለከት ወይም የሚቈጣጠር ማለት ነው ። ሁለቱን ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተጠቅሰው ልናገኛቸው እንችላለን ። የሐዋ. ፳ ፡ ፲፯ ። ፩ ጴጥ. ፭ ፡ ፩ ። ፊል. ፩ ፡ ፩ ። ፩ ጢሞ. ፫ ፡ ፩።

የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ኃላፊነት በቃል በሥራም ምዕመናንን እግዚአብሔር በሚወደው መንገድ በመምራት ነው ። ከስሕተት እንዲጠበቁ ፡ በመልካም ነገር ሁሉ እንዲጐለምሱ የማደፋፈርና የመምከር ኃላፊነት አለበት ። ፩ ጴጥ. ፭ ፡ ፩—፭ ። ፩ ጢሞ. ፫ ፡ ፩—፯። ማብራሪያ ። የሐዋርያት ዘመን ካለፈ በኋላ በቤተ ክርስቲያን መሪነት ጳጳሳትን መሾም የተለመደ ሆነ ። በዘመን ብዛት ጵጵስና ከፍተኛ ሹመት ሆነ ። ብዙ ጊዜም ለቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የማይገባ ሥጋዊ ሥልጣንና ኃይል ተሰጠው ለማለት ያስደፍራል ። በሐዋርያት ዘመን የጳጳሳት ሹመት በቤተ ክርስቲያን አልነበረም ። ከታሪክ ሂደት ጋር የመጣ ነገር ነው ።

ረ ፡ ዲያቆናት ።

ዲያቆን ማለት አገልጋይ ማለት ነው ። በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ምዕመናን በዲቁና የሚያገለግሉ ወንዶችና ሴቶች ነበሩ ። የተቸገሩትን በመርዳት ፡ ያዘኑትን በማጽናናት ፡ በሚቻላቸው ሁሉ ቤተ ክርስቲያን እንድትስፋፋና የሚፈለግባትን ሁሉ እንድትፈጽም አገልግሎታቸውን ያበረከቱ ነበር ። ፩ ጢሞ. ፫ ፡ ፰—፲፫ ። ሮሜ ፲፮ ፡ ፩ ። የሐዋ. ፮ ፡ ፩—፮ ።

ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያን አገል ጋዮች ሌላ በሐዋርያት መልእክቶች ተጠቅሰው የሚ ገኙት ብዙዎች አሉ ። ፩ ቆሮ. ፲፪ ። መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ እንደ ሰጠው መጠን ለቤተ ክርስቲያን እድገት ሲል እንዲያገለግል የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ።

የእግዚአብሔርን ቃል ለሰው ለማስተማር ፣ ቤተ ክርስቲያንንም በሥርዐት ለመምራት ግን በጣም አስፈ ላጊዎች የሆኑት ከፍ ብለን በዝርዝር የጠቀስናቸው አገልግሎቶች ናቸው ። እስከ ዛሬም የሐዋርያትን ቤተ ክርስቲያን አብነት በመከተል በየቤተ ክርስቲያኑ የእግዚ አብሔርን ቃል የሚያስተምሩ ፣ በዲቁናም የሚያገለግሉ ሰዎች እንዲኖሩ እናደርጋለን ።

## የጥንት ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ሥርዓት ።

### አንድነታቸው ።

የጥንት ዘመን ክርስቲያኖች እንደ አንድ ቤተ ሰብ በመሆን የዘርን ፣ የኅብረተሰብን ደረጃ ወይም የእውቀትን ልዩነት ሳይመለከቱ በፍቅር አንድነታቸ ውን ይገልጡ ነበር ። ይህም ጥሩ ኅብረት ባላመኑት ሰዎች መካከል ሳያስመሰግናቸው አልቀረም ። በፍ ቅር የተሳሰሩት በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ከእርሱ ደኅንነትን የተቀበሉ በመሆናቸው ነው ።

በሐዋርያት ዘመን የነበሩት ምዕመናን በፍቅር የሚተሳሰቡና የሚረዳዱ ስለ ሆኑ ሕዝቡ ሁሉ ተደሰ ተባቸው ። በሰው ሁሉ ፊትም ሞገስ ነበራቸው ። ከዕ ለት ወደ ዕለትም አዲሶች ምዕመናን ለቤተ ክርስቲ ያን ይጨመሩ ነበር ። የሐዋ. ፪ ፣ ፵፫—፵፯ ።

### ጥምቀትና የጸሎት ስብሰባ ።

ለቤተ ክርስቲያን የተጨመሩት የቅዱስ ጥምቀ ትን ጸጋ በመቀበል ነበር ። እሑድ እሑድም መዝሙር ለመዘመር ፣ ቃሉንም ለመስማት ፣ ጸሎትም ለማድረግ ይሰበሰቡ ነበር ።

## ቅዱስ ቍርባን ።

ቅዱስ ቍርባንንም በመካፈል አንድነታቸውን ያጸኑ ነበር ። ምናልባት ደግሞ ከክርስቲያኖች አንዱ በሕመም ምክንያት ወደ ጸሎት ቤት ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊመጣ ያልቻለ እንደ ሆነ ኅብስቱንና ወይኑን ወደ ቤቱ እየወሰዱ ያቈርቡት ነበር ። ክርስቲያኑም ምናልባት እስረኛ ቢሆን የሚቻል ከሆነ በእስር ቤት ቅዱስ ቍርባንን እንዲቀበል ያደርጉ ነበር ።

የቅዱስ ቍርባን ተካፋይ ለመሆን አስቀድሞ የተ ጠመቀ መሆን ያስፈልጋል ። ያልተጠመቁ የክርስትና ሃይማኖት ተማሪዎች ግን የእግዚአብሔርን ቃል ለመ ስማት የጸሎትም ተካፋይ ለመሆን ከሌሎች ምዕመናን ጋር ይሰበሰቡ ነበር ።

## የጸሎት ቦታቸው ።

በመጀመሪያ ያመኑት ሰዎች አይሁድ እንደ መሆ ናቸው መጠን እግዚአብሔርን ለመለመን በኢየሩሳ ሌም ወደ ቤተ መቅደስ ይሰበሰቡ ነበር ። ከዚህም ሌላ ግን በሰው ቤት እግዚአብሔርን ለመለመንና ለማመ ስገን በየጊዜው መሰብሰባቸው አልቀረም ። ከሐዋር ያት ዘመን በኋላም ማኅበረ ምዕመናን የመሰብሰቢያ ቦታ የሚሆን ቤተ ክርስቲያን ከመሥራታቸው በፊት በክርስቲያኖች የመኖሪያ ቤቶች እየተሰበሰቡ ይጸልዩ ነበር ።

## የቤተ ክርስቲያን ተግሣጽ ።

ክርስቲያን ኃጢአት በመሥራቱ ምናልባት የክ ርስቲያንን ስም ሲያስነቅፍ የተገኘ እንደሆነ ለጊዜው ከቅዱስ ቍርባን አንድነት ይወገዳል ። ቢሆንም ቃሉን ለመስማት ወደ ጸሎት ለመምጣት ፈቃድ አለው ። ስሕ ተቱም ታይቶት ንስሐ ለመግባት ከፈለገ ክርስቲያን ወንድሞቹና እኅቶቹ ጸሎት ያደርጉለታል ።

ቄስ በሌለበት ሽማግሌና ዲያቆን ይረዳ ነበር ።

በዘመን ብዛት ጳጳሳትና ካህናት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተመደቡ ። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን በጥምቀትና ቅዱስ ቍርባንን በማቅረብ ምዕመናንን ያገለግሉ የነበር ሽማግሌዎችና ዲያቆናት ናቸው ። በተለይም አብያተ ክርስቲያናት በጣም የበዙ ከሆኑ በኋላ ብዙውን ጊዜ ዲያቆናት ወይም ሽማግሌዎች ቅዱስ ቍርባንን በመስጠት ይረዱ ነበር ። በኋላ ግን ፣ ይህ መሆን የለበትም በማለት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቅዱስ ቍርባንን አገልግሎት ለጳጳሳት ወይም ለቄስ ሰጡ ።

LAPSLEY / BROOKS FOUNDATION, IN
1701 N. GREENVILLE AVE. ST. 810
RICHARDSON, TEXAS 75081, USA

ጥያቄዎች ።

፩. በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል የሚችል ማን ነው?

፪. ክርስቲያንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚያስችለው ምንድር ነው?

፫. ሐዋርያት እየተባሉ ይጠሩ የነበር ሰዎች እንዴት ያሉ ነበሩ?

፬. በቤተ ክርስቲያን የሽማግሌ ኃላፊነት እንዴት ነው?

፭. በቤተ ክርስቲያን የዲያቆን ኃላፊነት እንዴት ነው?

፮. በአዲስ ኪዳን ኤጲስቆጶስ የሚለው ቃል ማንን ያመለክታል ?

፯. የጥንት ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን የጸሎት ሥርዓት እንዴት ነበር ?

፰. በሐዋ ፳ ፣ ፳፰ ጳጳሳት የተባሉት ሰዎች በቤተ ክርስቲያን እንዴት ያለ አገልግሎት ነበራቸው ?

፱. ጳጳስ የሚለው ቃል በዘመን ብዛት ትርጕሙን ለውጦታል ማለት የምንችለው ከምን የተነሣ ነው ?

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት ።

## የስሕተት ትምህርቶች ።

### ሀ፤ የስሕተት ትምህርቶች በሐዋርያት ዘመን ።

### ግኑሲስ የሚሉት የተሳሳተ እውቀት ።

በሐዋርያት ዘመን ፣ እውቀት አለን ፣ አዋቂዎች እኛ ነን እያሉ በከንቱ የሚመኩ ሰዎች ነበሩ ። እውቀት ለሚለው ቃል አነርሱ በቋንቋቸው ግኑሲስ ይላሉ። ስለዚህ የግኑሲስ ወይም በእንግሊዝኛ አነጋገር የግኖስቲሲዝም ተከታዮች ናቸው እንላለን ።

ነገር ግን ፣ እውቀት አለን እያሉ ሲመኩ የሐሰትን ትምህርት ያስተምሩ ነበር ።

እነዚህ ከእውነት የራቁ ትምህርቶች ቀጥሎ እንደ ተዘረዘሩ ናቸው ።

፩. ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ አልመጣም ፣ ማለት እውነተኛ ሰው አይደለም ይሉ ነበር ። ሐዋርያው ዮሐንስ ግን ይህ ትምህርታቸው ከእግዚአብሔር ያልመጣ ፣ ክርስቶስንም የሚቃወም መሆኑን በግልጽ አስተምሮናል ። ፩ ዮሐ. ፬ ፣ ፫ ። ፪. ዮሐ. ፯ ።

፪. ሙታን በሥጋ አይነሡም ይሉ ነበር ። ትንሣኤ ከዚህ በፊት የሆነ ፣ የተፈጸመ ነገር ነው እያሉ ያስተምሩ ነበር ። የሙታን ትንሣኤ አለ ቢባል መንፈሳዊ ትንሣኤ ብቻ ነው እንጂ በሥጋ መነሣት የሚሆን አይደለም ማለታቸው ነው ። ፪ ጢሞ. ፪ ፣ ፲፰ ። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ትምህርት በመቃወም ሙታን በሥጋ እንደሚነሡ በግልጽ ጽፎአል ። ፩ ቆሮ. ፲፭ ፣ ፲፪—፶ ።

፫. መላእክት ሰውን ከአምላክ ጋር የሚያገናኙ አማላጆች ናቸው ። ስለዚህ ለመላእክት መስገድ ያስፈልጋል ይሉ ነበር ። ይህም ስሕተት ነው ። ቈላ. ፪ ፣ ፲፰ ይመልከቱ ።

፬. ከአይሁድ ሃይማኖት አንዳንድ ነጥቦችን እየጨመሩ ፣ ለክርስቲያን ያልተፈቀደ ምግብ አለ ፤

እንደ ብሉይ ኪዳን ሥርዓትም ቅዳሜን ማክበር አለበት ፤ እንዲሁም በሙሴ የተሰጡትን ሌሎችንም በዓላት ክርስቲያን ሊጠብቃቸው ያስፈልጋል እያሉ ያስተምሩ ነበር ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለዚህ መልስ ሲሰጥ ፥ ክርስቲያን ከዚህ ሁሉ ነፃ ነው ብሎአል ። ስለዚህ የግኑሲስ ሰዎች የሚሉት ሐሰት ነው ። ቈላ. ፪ ፥ ፲፮—፲፯ ። በተለይም ስለ ምግብ ዓይነት ብናስብ ሐዋርያው እንዳስተማረን እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ሁሉ መልካም ነውና በምስጋና ቢቀበሉት ክርስቲያኖች ሊበሉት ይችላሉ ። ርኵስ የተባለ ምግብ የለም ። ፩ ጢሞ. ፬ ፥ ፫—፭ ።

፭. ክርስቲያን ከሕግ ነጻ ስለ ሆነ በፈለገው መንገድ ሁሉ ሥጋውን ለማስደሰት ይችላል ፥ የሚከለክለው ምንም ነገር የለም በማለት በርኵስ ፍትወት እየተቃጠሉ ለዝሙትና ይህን ለመሳሰለ ውርደት ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ ሰዎች በመካከላቸው ነበሩ ። ውኃና ምግብ ለሰውነት አስፈላጊ እንደ ሆነ ሁሉ ሥጋን ለማርካት የወንድና የሴት ግንኙነት አስፈላጊ ነው ፥ ተገቢም ነው ይሉ ነበር ። ያም ሲመኩበት ነው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ግን የዝሙት ኃጢአታቸውን እንሥቶባቸው ፥ መመካታችሁ መልካም አይደለም . . . አትሳቱ ፥ አመንዝሮች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም ብሎ ይገሥጻቸዋል ። ፩ ቆሮ. ፭ ፥ ፩—፯ ፤ ፯ ፥ ፱—፲ ። ፪ ጢሞ. ፫ ፥ ፭—፯ ።

፮. በርኵሰት ሥራ ሥጋዊ ምኞታቸውን ለማርካት ከሚፈልጉት በመለየት ሌሎች ሥጋ መጥፎ ነው ፥ ከመንፈሳዊነት የተለየ ነው ፤ ስለዚህ የሥጋን ፈቃድ መፈጸም የለብንም በማለት በልዩ ልዩ መንገድ ሰውነታቸውን ይገቱና ያጕሳቍሉ ነበር ። በዚህም አስተሳሰብ እየተመሩ የጋብቻን አንድነት እንኳን እስከ መከልከል ደርሰዋል ። ሰው ንጽሕናውን እንዲጠብቅ ባያገባ ይሻላል ፥ ምናልባት ደግሞ አግብቶ እንደሆነ ከሚስቱ ጋር ባይገናኝ ይሻላል እያሉ ያስተምሩ ነበር ። የወንድና የሴት

የሥጋ ግንኙነት ርኩስ ነገር ነው ማለታቸው ነው ። ፩ ጢሞ. ፬ ፥ ፫ ።

እንደዚህ ያለ ፥ እግዚአብሔር የሠራውን የቅዱስ ጋብቻን አንድነት የሚያስንቅ ትምህርት በጣም የተሳሳተ መሆኑ ግልጽ ነው ። ሐዋርያው ጳውሎስ የጋብቻ አንድነት የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን በግልጽ አስተምሮአል ። ፩ ቆሮ. ፯ ፥ ፩—፭ ።
እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ሲፈጥራቸው የጋብቻን አንድነት እንደ ቀደሰውና እንደ ባረከው እነዚያ ሰዎች ረስተው ነበር ። ዘፍጥ. ፩ ፥ ፳፯—፳፰ ።

፯. የምንኖርበት ዓለም ክፉ ነው ፤ እግዚአብሔር ግን ፍጹም ቸር የሆነ አምላክ ነው ፤ ስለዚህ ክፋት የሞላበትን ዓለም የፈጠረው ፍጹም የሆነው አምላክ ሊሆን አይችልም ፤ ዓለም የተፈጠረው ከፋ በሆነ ኃይል ነው ፥ ክፋትም የበዛበት በዚህ ምክንያት ነው ይሉ ነበር ። አሪት ዘፍጥረትን ምዕራፍ አንድ ብናነብ ግን እንደዚህ ያለ ትምህርት ከእውነት የራቀ መሆኑ ይታየናል ። ሰማይና ምድርን የፈጠረ የሁሉም ነገር መጀመሪያ የሆነ ፥ ፍጹም ቸርነትና ጥበብ ያለው እግዚአብሔር ነው ሁሉንም እጅግ መልካም ሆኖ አገኘው ። ዘጥፍ. ፩ ፥ ፴፩ ። ዓለምን ያበላሸው በኃጢአት የወደቀው ሰው ነው እንጂ ፈጣሪ አይደለም ።

እንግዲህ ከፍ ብሎ የሚታየውን የሐሰትን ትምህርት ሁሉ እያስተማሩ ሲኖሩ ፥ እውቀት አለን እያሉ ይመኩ ነበር ። ሐዋርያው ጳውሎስ በ፩ ጢሞ. ፮ ፥ ፲፩ የጻፈባቸው ቃል እውነተኛ ነው ። ይህ እውቀት የእውነት ሳይሆን የውሸት እውቀት ነው ብሎአል ። ከንቱ መለፍለፍና ክርክር ያለበት ነው ። ስለዚህ ክርስቲያን ይህንን ከመሰለ ሁሉ መራቅ አለበት ።

ለክርስቲያን እውነተኛ ጥበብና የእውቀት ምንጭ መዝገብም ክርስቶስ ነው ። ቈላ. ፪ ፥ ፫ ። የግኑሲስ ተከታዮች እንደሚሉት አይደለም ።

ለ ፣ የስሕተት ትምህርቶች ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ።

## የአሪዮስ ስሕተት ።

ሀ ፣ ክርስቶስ ፍጡር ነው አለ ።

ክርስቲያኖች ከመጀመሪያው ዘመን አንሥቶ ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም የተወለደ እውነተኛ ሰው መሆኑን ከማመናቸውም በላይ እውነተኛ አምላክም መሆኑን በማመን ይሰግዱለትና ያመልኩት ነበር ።

በዮሐንስ ወንጌል መግቢያ ላይ ኢየሱስ ቃል ተባለ ። ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ተብሎ ተጻፈለት ። የሰውን ሥጋ ነሥቶ ከድንግል የተወለደው ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው ። አምላክ ነው ። ዮሐ. ፩ ፣ ፩ ። ቈላ. ፩ ፣ ፲፱ ፣

ነገር ግን አምላክነቱን ለመካድ የተነሡ ሰዎች አሉ ። በጥንት ዘመን ታሪክ ከእነርሱ ዋናው አሪዮስ የተባለው የእስክንድሪያ ከተማ ቄስ ወይም ሽማግሌ ነው ።

ክርስቶስ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረቶች የመጀመሪያው ነው ፤ ፍጡር ነው ፣ ያልነበረምበትም ጊዜ አለ ፣ ከዘላለም ጀምሮ የሚኖር አይደለም ፤ ከእግዚአብሔር ጋር የተካከለ አይደለም ፣ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ ነው ለማለት አይቻልም እያለ ያስተምር ነበር።

በእርሱ ትምህርት ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ክርክር ተፈጠረ ። አሪዮስን የደገፉ ሰዎች ሲኖሩ የሚቃወሙትም በዛ ያሉ ናቸው ። በቤተ ክርስቲያንም ክርክሩ የመለያየት ምክንያት ሆነ ።

ለ ፣ <u>የኒቅያ ጉባዔ</u> ።

በዚህ መካከል ቆስጠንጢኖስ ቄሣር ሰላም እንዲፈጠር በማለት የቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ኒቅያ በተባለችው የትንሽዋ እስያ ከተማ ተሰብስበው ስለ ጉዳዩ ውይይት እንዲያደርጉ ወሰነ ። በውሳኔውም መሠረት በ፫፻፳፭ ዓ. ም. ጳጳሳት ለዚህ ጉባዔ ተሰበሰቡ ። በቍጥር ፫፻፲፰ ናቸው ።

ግማሾቹ በዲዮክሌቲያኑስ ስደት ጊዜ ተሰድደው ብዙ መከራ ያዩ ፣ ልዩ ልዩ ሥጋዊ ጉዳትም የደረሰ ባቸው ናቸው ። ዓይናቸው ተበስቶ ዕውራን የሆኑ አሉ ። እግርና እጅ ተቆርጦበት አካለ ስንኩል የሆነ ብዙ አለ ። በሰውነታቸው ላይ የሚታየው ጠባሳ በስ ደት ጊዜ አሰቃቂ ግርፋትና ድብደባ የደረሰባቸው ለመሆኑ ምስክር ነው ።

ስለ አሪዮስ ሐሳዊ ትምህርት ውይይት ለማድረግ የተሰበሰቡ እነዚህ ናቸው ።

ሐ ፣ አትናቴዎስ ።

በጉባኤው ላይ ከጳጳሳት ይልቅ ለእውነተኛው ሃይ ማኖት ሊዋጋ የተነሣው አትናቴዎስ የተባለ ዲያቆን ነው ። በኋላ በእስክንድሪያ ጳጳስ እንዲሆን የተመረ ጠው እርሱ ነው ።

አትናቴዎስ በክርክሩ ላይ ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእ ግዚአብሔር ጋር የተካከለ ነው ከአብ አያንስም ፣ ከእ ግዚአብሔር አብ ጋር እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ከዘላለም ጀምሮ የሚኖር ነው ። አምላክ ባይሆን ኖሮ ከኃጢአታችን ሊያድነን አይችልም ነበር እያለ ይከ ራከር ነበር ።

ጉባኤውም በዚህ ነገር አትናቴዎስን በመደገፍ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ፣ የተፈጠረም ሳይ ሆን ከዘላለም ከአብ የተወለደ በህልውና ከአብ ጋር አንድ ፣ ከአምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ ነው ብለው ተስማሙ ። በዚህም ውሳኔ የአርዮስ ትምህርት ሐሰት ነው ብሎ ተወገዘ ።

ቤተ ክርስቲያን እስከ ዛሬ የጥንት ዘመን አበው ስለ ክርስቶስ የነበራቸውን እምነት በመከተል ፣ እው ነተኛ አምላክ ነው ፣ ከአብ ጋር አንድ ነው እያለች ትመሰክራለች ።

## ስለ መንፈስ ቅዱስ የተደረገ ጉባኤ ።

የአሪዮስ ተከታዮች ስለ መንፈስ ቅዱስም ያስተ ማሩት ትምህርት የተሳሳተ ነው ። በወልድ የተፈጠረ

ነው ይላሉ ። ስለዚህ ወልድ ከአብ በታች እንደ ሆነ መንፈስ ቅዱስም ከወልድ በታች ነው ይላሉ ። በምሳሌ ውስጥ ሦስቱ አካላት ሦስት የተለያዩ ደረጃዎች አሉ አቸው እንጂ እኩል አይሆኑም እንደ ማለት ነው ።

ቤተ ክርስቲያን ይህንን ትምህርት ትክክለኛ አድርጋ ልትቀበለው አልቻለችም ። በጉዳዩም ጉባዔ ዎች ተደርገው ተወያዩበት ። በ፫፻፹፩ ዓ. ም. ፻፶፮ ጳጳሳት የተገኙበት ጉባዔ ቍስጥንጥንያ በተባለችው ከተማ ተደረገ ። ጉባዔውም የአሪዮስ ተከታዮች ያስ ተማሩትን ትምህርት አውግዞ መንፈስ ቅዱስ በዘላለ ማዊነትና በመለኮት ከአብና ከወልድ ጋር የተካከለ ነው በማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተውን የቤተ ክርስቲያንን እምነት ገለጠ ። ከአብና ከወልድ ጋር በሚሰገድለት ፣ በነቢያት በተናገረ ፣ የሕይወት ጌታና ሰጪ በሆነ ፣ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን የሚለውን ቃል ትክክለኛ አድርገው ተቀበሉት ።

በዚህ ቃል እንደ ተገለጠ መንፈስ ቅዱስ እንደ አብና እንደ ወልድ እውነተኛ አምላክ ነው ።

## ስለ ክርስቶስ ባሕርያት የተደረገ ክርክር ።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንማረው ኢየሱስ ክር ስቶስ እውነተኛ ሰው እውነተኛ አምላክ ነው ። ክርስ ቶስ ግን አንድ እንጂ ሁለት አይደለም ። አንድነቱን አምነን እንመሰክራለን ።

ይህ ነገር እንዴት ሊሆን ይችላል ፣ እንዴትስ እውነተኛ ሰው ፣ እውነተኛ አምላክ ለማለት እንችላ ለን ? ብለው የሚጠይቁ ሰዎች ይኖራሉ ። ከዚህም አል ፈው ነገሩ ስላልገባቸው ትምህርቱን ሳይቀበሉት የቀሩ ክርክርም በማድረግ መለያየትን የፈጠሩ አሉ ።

ከዚህ የተነሣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተሰ ብስበው ለጠያቂዎች አስፈላጊውን መልስ አዘጋጁ ። በ ፬፻፶፩ ዓ.ም. አምስት መቶ ጳጳሳት የተገኙበት ጉባዔ ከልቄዶን በተባለችው ከተማ ተደርጎ ፣ ክርስቶስ አንድ ነው ፣ አንድ ሆኖ ሳለ ግን ሁለት የማይለያዩ ባሕርያት አሉበት ፣ አንደኛው አምላካዊ ሲሆን ሁለተኛው ሰብአዊ

ነው በማለት ስለ ክርስቶስ ያላቸውን እምነት ገለጡ ። ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክና እውነተኛ ሰው ነው ማለት ነው ።

ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት አብዛኞቹ የከልኬዶንን የእምነት መግለጫ ትክክለኛ አድርገው ተቀብለውታል ።

እስከ ዛሬ ግን ያልተቀበሉም አሉ ። ያዕቆባውያን የተባሉት የሶርያ አገር ክርስቲያኖች ፣ የግብጽ አገር ቤተ ክርስቲያንም ፣ የኢትዮጵያም ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ሲያስተምሩ ፣ አንድ አካል ሁለት ባሕርያት ማለትን ትተው አንድ አካል አንድ ባሕርይ ይላሉ ።

## የጴላጊዮስ ስሕተት ።

ጴላጊዮስ በአይርላንድ አገር የተወለደ መነኩሴ ነበር ።

በ፬፻፱ ዓ.ም. ትምህርቱን ለማስተማር ወደ ኢጣሊያ መጣ ። ከዚያም ወደ ሰሜን አፍሪካ ተሻገረ ። ሲያስተምርም እንዲህ ይል ነበር ።

፩. ሰው ነጻ የሆነ ፈቃድ አለው ። ክፉ ሆነ ደግ የፈለገውን ሁሉ ለመሥራት ይችላል ።

፪. ሰው ኃጢአት ሳይኖርበት ይወለዳል ፣ ማለት የተወረሰ ኃጢአት የለበትም ።

፫. ሰው ቢፈልግ ኃጢአትን ሳይሠራ ሊኖር ይችላል ። ኃጢአትንም ሠርተው የማያውቁ ሰዎች አሉ ።

፬. ለሰው ዋናው ነገር የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ ነው ። በወንጌልም ብቻ ሳይሆን ሰው ሕግን በመጠበቅም ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊደርስ ይችላል ።

እንደዚህ ያለ ትምህርት የክርስትናን ሃይማኖት ዋናዎች እርእስተ ነገሮች የሚቃረን መሆኑ ግልጽ ነው ። ሰው በራሱ ኃይል ከኃጢአት ለመራቅ ፣ በራሱም

ጥሪት ነፍሱን ለማዳን ከቻለ ክርስቶስ ኃጢአተኞችን ለማዳን ወደ ዓለም መምጣት አያስፈልገውም ነበር ።

የጥንት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን ነገር ደኅና አድርገው ስለ ተገነዘቡት የጲላጊዮስ ትምህርት ሐሰት ነው ብለው አወገዙት ። በተለይም ስሕተቱን ሊገልጥበት የተነሣው ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት አውግስጢኖስ ነው ። እርሱም በቃል በጽሑፍም ጉላ አድርጎ እንዳስረዳው ሰው ከአባት ከእናት የወረሰው ከፋ የሆነ የኃጢአት ዝንባሌ ያደረበት ፍጡር ነው ። በተፈ ጥሮው መልካም ሥራ የለውምና በራሱ ሥራ ሊድን አይችልም ።

በራሱ ተስፋ የሌለው ኃጢአተኛ ሊድን የሚች ለው በእግዚአብሔር ቸርነትና ጸጋ ብቻ ነው ። ይኸ ውም ክርስቶስን በልብ እምነት ቢቀበለው ነው ። ሰው ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊደርስ የሚችለው ስለ ኃጢ አተኞች በሞተው በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ የኃጢ አትን ስርየት በማግኘቱ ነው እንጂ በራሱ ሥራ አይ ደለም እያለ አውግስጢኖስ ያስተምር ነበር ።

የቤተ ክርስቲያን እምነት ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስም የተማርነው ይህ ነው ።

## ጥያቄዎች ።

፩. አሪዮስ ስለ ክርስቶስ ያስተማረውን ትምህርት ቤተ ክርስቲያን ልትቀበለው ያልቻለችው ከምን የተነሣ ነው?

፪. የኒቅያ ጉባዔ በስንት ዓመተ ምሕረት ተደረገ ?

፫. በኒቅያ ጉባዔ ላይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ብለው ተስማሙ ?

፬. በዚህ ጉባዔ ላይ የአሪዮስን ስሕተት ጥሩ አድርጎ የገለጠበት ዲያቆን ማን ነው?

፭. የአሪዮስ ተከታዮች ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን ይሉ ነበር ። ?

፮. የጥንት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን በማለት ያስተምሩ ነበር ?

፯ የከልኬዶን ጉባዔ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማ ድረግ ስለ ክርስቶስ ባሕርያት ምን ብሎ ወሰነ ?

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት ።

## የጥንት ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት መግለጫዎች ።

ባለፈው ምዕራፍ ቤተ ክርስቲያንን ስላስቸገሩ አት ስለ ስሕተት ትምህርቶች በአጭሩ አነበብን ። ማኅበረ ምዕመናን ከእነዚህ ስሕተቶች እንዲጠበቁ ፣ ትክክለኛ ውንም የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በቀላል መንገድ ለማወቅ እንዲችሉ ፣ የጥንት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አጫጭር የሃይማኖት መግለጫዎችን አዘጋጅተዋል ።

እነዚህ መግለጫዎች አጭር በሆነ መንገድ የመ ጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛ ትምህርት ስለሚጠቅሱ ለእኛም ይጠቅሙናል ።

ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ያለውን የጥንት ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት የሚገልጡ የሃይማኖት መግለ ጫዎች ሦስት ናቸው ።

### ሀ ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ።

ይህ ጽሑፍ የሐዋርያት ተብሎ የተጠራው የሐዋ ርያትን እምነትና ትምህርት የሚጠቅስ በመሆኑ ነው። አዘጋጆቹ ግን ከሐዋርያት ዘመን በኋላ የኖሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው ። ቃሉ እንዲህ የሚል ነው፦—

እኔ ሁሉን በሚችል ፣ ሰማይና ምድርን በፈጠረ ፣ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ ። ደግሞም በአንድ ልጁ ፣ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ ፣ ከድንግል ማር ያም በተወለደ ፣ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራ በተቀበለ ፣ በተሰቀለ ፣ በሞተ ፣ በተቀበረ ፣ ወደ ሲኦል በወረደ ፣ በሦስተኛው ቀን ከሙታን በተነሣ ፣ ወደ ሰማይ በወጣ ፣ ሁሉን በሚችል በእ ግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ ፣ በሕያዋንና በሙ ታን ሊፈርድ ከዚያ በሚመለስ ፤ በጌታችን በኢየ ሱስ ክርስቶስ አምናለሁ ። ደግሞም በመንፈስ

Pontius

ቅዱስ ፡ በአንዲት ቅድስት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ፡ በቅዱሳን አንድነት ፡ በኃጢአት ስርየት ፡ በሥጋ ትንሣኤ ፡ በዘላለም ሕይወት አምናለሁ ።

ለ ፡ የኒቅያ የሃይማኖት መግለጫ ።

እኔ ሁሉን በሚችል ሰማይንና ምድርን ፡ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ ። እርሱ ብቻ የአብ ልጅ በሚሆን ዓለም ሳይፈጠር ከአብ በተወለደ ፡ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን ፡ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ በሚሆን ፡ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ ፤ በሀልዎና ከአብ ጋር በተካከለ ፡ ሁሉ በእርሱ በሆነ ፡ ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ ደኅንነታችን ከሰማይ በወረደ ፡ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም ሥጋ ነሥቶ ሰው በሆነ ፡ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ በተሰቀለ ፡ መከራ በተቀበለ ፡ በተቀበረም ፡ በቅዱሳት መጻሕፍትም እንደ ተጻፈው በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣ ፡ ወደ ሰማይ በወጣ ፡ በአባቱም ቀኝ በተቀመጠ ፡ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ዳግመኛ በክብር በሚመጣው ለመንግሥቱ ፍጻሜ በሌለው በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ ።

ከአብና ከወልድ ጋር በሚሰገድለት ፡ ከአብና ከወልድ በሚሠርጽ ፡ በነቢያት በተናገረ ፡ የሕይወት ጌታና ሰጪ በሆነ ፡ በመንፈስ ቅዱስ እምናለሁ ። በአንዲትም ቅድስት የሁሉም በሆነች የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አምናለሁ ። ኃጢአት ለማስተስረያ በተደረገች በአንዲት ጥምቀትም አምናለሁ ። የሙታንንም ትንሣኤና ገና የሚመጣውን ዓለም ሕይወት እጠባበቃለሁ ።

ሐ ፡ የአትናቴዎስ የሃይማኖት መግለጫ ።

በአርዮስ ተከታዮች ላይ የተጻፈ ።

፩. ለመዳን የሚፈልግ ሰው ሁሉ ከሁሉም ነገር አስቀድሞ የሁሉ የሆነች የቤተ ክርስቲያንን

ሃይማኖት እውነተኛ አድርጎ ሊቀበለው ያስ ፈልገዋል ።

፪. ንጹሕና ሙሉ አድርጎ ያልጠበቀው ሰው ሁሉ ያለ ጥርጥር የዘላለም ጥፋት ይደርስበታል ።

፫. የክርስቲያኖች የጋራ ሃይማኖት እንዲህ ነው ፤ በሦስትነቱ አንድነቱን ፥ በአንድነቱም ሦስት ነቱን አምነን አንድ አምላክ እናከብራለን ።

፬. ይህንንም የምናደርገው አካላቱን ሳናደባልቅ ሕልውናውንም ሳንከፍለው ነው ።

፭. ምክንያቱም የአብ አካል ለብቻው ፥ የወልድም ለብቻው ፥ የመንፈስ ቅዱስም ለብቻው ነው ።

፮. ቢሆንም ፥ የአብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ መለ ኮት አንድ ሲሆን ክብሩ ሥልጣኑም ለዘላለም እኩል ሆኖ ይኖራል ።

፯. አብ በሕልውናው እንደ ወልድ ነው ፤ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ነው ።

፰. አብ አልተፈጠረም ፤ ወልድም አልተፈጠረም ፤ መንፈስ ቅዱስም አልተፈጠረም ።

፱. አብ ወሰን የለውም ፤ ወልድም ወሰን የለውም ፤ መንፈስ ቅዱስም ወሰን የለውም ።

፲. አብ የዘላለም ፥ ወልድም የዘላለም ፥ መንፈስ ቅዱስም የዘላለም ነው ።

፲፩. ቢሆንም ፥ ዘለዓለማዊ ሆኖ የሚኖረው አንድ እንጂ ሦስት ዘለዓለማውያን አይኖሩም ።

፲፪. እንዲሁም ደግሞ ያልተፈጠረና ወሰን የሌለው አንድ እንጂ ሦስት ያልተፈጠሩና ሦስት ወሰን የሌላቸው አሉ አይባልም ።

፲፫. እንዲሁም አብ ሁሉን የሚችል ፥ ወልድም ሁሉን የሚችል ፥ መንፈስ ቅዱስም ሁሉን የሚችል ነው ።

፲፬. ቢሆንም ፥ ሁሉን የሚችል የሆነው አንድ እንጂ ሦስት አይደሉም ።

፲፭. እንግዲህ አብ አምላክ ፥ ወልድም አምላክ ፥ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው ።

፲፮ ሆኖም አምላክ አንድ እንጂ ሦስት አማልክት አይደሉም ።

፲፯. እንደዚሁም አብ ጌታ ፣ ወልድም ጌታ ፣ መንፈስ ቅዱስም ጌታ ነው ።

፲፰. ቢሆንም ፣ ጌታ የሆነው አንድ እንጂ ሦስት አይደሉም ። ምክንያቱም እውነተኛው የክርስ ትና ሃይማኖት እያንዳንዱ አካል አምላክና ጌታ መሆኑን እንድናምን እንደሚያስገድደን ሁሉ

፲፱. እንደዚሁ የሁሉም የሆነ የክርስትና ሃይማኖት ሦስት አማልክት ወይም ሦስት ጌቶች ብለን እንዳንጠቅስ ይከለክለናል ።

፳. አብ በማንም አልተሠራም ፣ አልተፈጠረም ፣ አል ተወለደምም ።

፳፩. ወልድ ከአብ ብቻ ነው ፤ አልተሠራም ፣ አልተፈ ጠረምም ። ነገር ግን ተወለደ ።

፳፪. መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ነው ። አልተ ሠራም ፣ አልተፈጠረም ፣ አልተወለደምም ። ነገር ግን የሚሠርጽ ነው ።

፳፫. እንግዲህ አብ አንድ ሲሆን ሦስት አባቶች አይ ደሉም ፣ ወልድም አንድ ሲሆን ሦስት ውሉድ አይደሉም ፣ መንፈስ ቅዱስም አንድ ሲሆን ሦስት ቅዱሳን መናፍስት አይደሉም ።

፳፬. በሥላሴ ውስጥ አንዱ አካል ከሌላው ቀዳሚ ነት ወይም ኋለኛነት የለውም ። አንዱም ከሌላው የሚበልጥ ወይም የሚያንስ አይደለም ።

፳፭. ሦስቱ አካላት በዘለዓለማዊነትና በታላቅነት እኩል ናቸው ። ይኸውም ከፍ ብሎ እንደ ተጠ ቀሰ በሁሉም ነገር ሦስትነቱ በአንድነቱ ፣ አንድ ነቱም በሦስትነቱ እንዲከበር ነው ።

፳፮. ለመዳን የሚፈልግ ሰው ስለ ሥላሴ ማሰብ የሚ ገባው ይህ ነው ።

፳፯. ከዚህም ሌላ የዘላለምን ደኅንነት ለማግኘት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋዌ እውነ ተኛ አድርጎ ማመን ያስፈልገዋል ።

፳፰· ምክንያቱም እውነተኛው ሃይማኖት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ አምላክም ሰውም መሆኑን በማመን ነው ።

፳፱· እርሱም ዓለም ሳይፈጠር ከአብ ሕልውና የተወለደ አምላክ ።

፴· በዓለምም ላይ ከእናቱ በሥጋ የተወለደ ሰው ሆኖ ሳለ ለባዊት ነፍስ ያለችው የሰውን ሥጋ የለበሰ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው።

፴፩· በአምላክነቱ ከአብ ጋር የተካከለ ፣ በሰውነቱም ከአብ ያነሰ ነው ።

፴፪· ነገር ግን አምላክም ሰውም ቢሆንም ክርስቶስ አንድ እንጂ ሁለት አይደለም ።

፴፫· አንድ ነው ። ይኸውም ሰውነቱ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ በመሆኑ ነው እንጂ መለኮት ወደ ሥጋ በመለወጡ አይደለም ።

፴፬· እንግዲህ በጠቅላላው አንድ ነው ። ይኸውም በባሕሪያት መደባለቅ ሳይሆን በአካሉ አንድነት ነው ።

፴፭· ምክንያቱም ለባዊት ነፍስና ሥጋ የተዋሐዱበት ሰው አንድ እንደሚሆን ሁሉ አምላክና ሰው የሆነ ክርስቶስ አንድ ነው ።

፴፮· እርሱም ለደኅንነታችን ሲል መከራ የተቀበለ ፣ ወደ ሲኦልም የወረደ ፣ በሦስተኛውም ቀ" ከሙታን የተነሣ ።

፴፯· ወደ ሰማይ የወጣ ፣ ሁሉንም በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ የተቀመጠ ፣ በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ከዚያ የሚመለስ ነው ።

፴፰· ተመልሶ ሲመጣም ስለ ሠሩት ሥራ መልስ እንዲሰጡ ሰዎች ሁሉ በሥጋ ይነሣሉ ።

፴፱· መልካምም የሠሩት ወደ ዘላለም ሕይወት ፣ ክፋም የሠሩት ወደ ዘላለም እሳት ይገባሉ ።

፵· የሁሉም የሆነ የክርስቲያኖች ሃይማኖት ይህ ነው ። በጽኑ እምነት ይህንን ሃይማኖት ያልያዘ ሰው ሊድን አይችልም ።

# ምዕራፍ አሥራ አራት ።

## ባሕታውያንና መነኰሳት ።

## ስለ ባሕታውያን ።

<u>ከሰው ተለዩ ።</u>

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ከመለየቱ በፊት ፣ አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ ብሎ መናገሩ የሚታወስ ነው ። ዮሐ. ፳ ፣ ፳፩ ። ደቀ መዛሙርቱም የመጀመሪያ ዘመን ክርስቲያኖችም ይህንን ቃል በማሰብ ያላመነ ሰው ወደ ነበረበት ሁሉ እየደረሱ ስለ ክርስቶስ ይመሰክሩና ብዙዎችን ያሳምኑ ነበር ።

በዘመን ብዛት ግን አንዳንድ ክርስቲያኖች ክርስቶስ የተናገረውን በመርሳት ትልቅ ስሕተት እስከ መሥራት ደርሰዋል ። እነርሱም ባሕታውያን የምንላቸው ሰዎች ናቸው ።

ዓለም ክፉ ነው ፣ ከሰውም ጋር መኖር በፈተና ከመውደቅ ያደርሳል ፣ ስለዚህ በዓለም ፍትወት እንዳልረክስ በብቸኝነት መኖር ይሻለኛል ፣ ከሰው ተለይቼ ሥጋዬን በማጐሳቈል ቅዱስ እሆናለሁ በማለት ባሕታውያን ሆኑ ።

ባሕታዊ ማለት ከሰው ተለይቶ በብቸኝነት የሚኖር ማለት ነው ።

እነዚህ ሰዎች በቅድስና ለመኖር ሲሉ ወደ በረሀ እየሸሹ ሰው በሌለበት ጊዜአቸውን ያሳልፉ ነበር ። በቤት ሳይሆን በዋሻ ውስጥ የተቀመጡ አሉ ። በሌሊትም የሚተኙት በአፈር ላይ ነው ። የሥጋቸውን ምኞት ለማጥፋት ሲሉ በልዩ ልዩ መንገድ ሰውነታቸውን ያደክማሉ ። ምግብ በማሳነስ በራብ ተጨንቀው የሚኖሩ አሉ ። ሰውነታቸውን አይታጠቡም ፣ ጸጕራቸውንም ያሳድጋሉ ፣ የተበሳጨቀውን ልብስም ለብሰው ይኖራሉ ። ወይም በእርጩሚ ሥጋቸውን ሲገርፉ ይውላሉ ።

ይህን ሁሉ የሚያደርጉት የሥጋ ምኞት እንዲጠፋ ፣ ነፍሳቸውም ለመንግሥት ሰማያት የተዘጋጀች

እንድትሆን ነው ። ለዚህም ምሳሌ እንዲሆን የሁለት ባሕታውያንን ታሪክ በአጭሩ እናወሳለን ።

## አንቶኒዮስ ።

በ፫፻ ዓ.ም. ገደማ በግብጽ አገር አንቶኒዮስ የተባለ ወጣት ነበር ። ወላጆቹ ሀብታሞች የሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው ። አንቶኒዮስ ገና በወጣትነቱ ሳለ እነርሱ ሞቱ ። አንድ ቀን በቤተ ክእርስቲያን ቄሱ ፣ ፍጹም ልትሆን ብትወድ ፣ ሂድና ያለህን ሽጠህ ለድሆች ስጥ ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ በሚለው ፣ ኢየሱስ በተናገረው ቃል ላይ ስብከት ሲያደርግ ሰማ ።

ስብከቱም ልቡን በጣም ስለ ነካው ከወላጆቹ የወረሰውን ሀብት ሁሉ ለድሆች ሰጥቶ ከሰው ተለይቶ በምድረ በዳ ዋሻ ውስጥ ተቀመጠ ። በዚያም በጾም ፣ በጸሎትም ፣ በአፈር ላይ በመተኛትም ፣ አሳንሶ በመብላትም ፣ ይህንንም በመሳሰለ ሁሉ ሰውነቱን በማድከም ብዙ ዓመታትን አሳለፈ ። እስከ እርጅና ድረስ ከምድረ በዳ ኑሮ አልተለየም ።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመነኰሳት አባት የሚለው ስም ተሰጥቶታል ።

## የምሰሶው ስምዖን ።

የአንቶኒዮስን አርዓያ በመከተል ባሕታዊ የሆነ ፣ ዝናውም ወደ ብዙ አገር የደረሰ ሌላም አለ ። ስሙ ስምዖን ነው ። ቅዱስ ለመሆን ሲል በአንጾክያ ከተማ አቅራቢያ ቁመቱ ፳ ሜትር የሆነ የድንጋይ ምሰሶ አቆመና በላዩ ላይ ተቀመጠ ። በዚያም ያለ ማቋረጥ ቀና ጐንበስ እያለ ቀንና ሌሊት እስከ ፴ ዓመት ድረስ ቆየ ። የሌሊትን ቊር የፀሐይን ሐሩር ሳይፈራ ከዓመት ወደ ዓመት በምሰሶው ላይ ይቀመጥ ነበር ። ዝናብ ቢዘንብም ከዚያ አይወርድም ። በ፬፻፷ ዓ. ም. ከዚህ ዓለም እስኪለይ ድረስ ኑሮውን በዚህ ዓይነት ቀጠለ ።

ክርስቲያን ይህን በመሰለ ነገር እግዚአብሔርን ለማስደሰት መሞከሩ ትልቅ ስሕተት መሆኑ ግልጽ ነው ። ክርስቶስ ከተከታዮቹ የሚፈልገው ነገር ከዚህ የተለየ ነው ። ሰው ወዳለበት እንድንደርስ ፣ ደርሰንም

ቃለ እግዚአብሔርን እንድናስተምር እንጂ ከሰው እን ድንሸሽ አላስተማረንም ።

በጥንት ዘመንም ቢሆን የባሕታውያን ኑሮ የተ ሳሳተ መሆኑን ብዙዎች ሰዎች ሳይገነዘቡ አልቀሩም ። ስሕተታቸውን ለማረም ሲሉ በብቸኝነት ከመቀመጥ በአንድነት በገዳም መኖር ይሻላል በማለት የገዳምን ኑሮ ያስጀመሩ አሉ ።

## ስለ መነኰሳት ።

### ገዳማት ተቋቋሙ ።

የገዳም ኑሮ በጥንት ቤተ ክርስቲያን ዘመን የተ ጀመረው በአራተኛው መቶ ዘመን መካከል ነው ።

በግብጽ አገር ጳቆሚዩስ የተባለ መነኵሴ በ፫፻፳ ዓ.ም. ገዳም አቋቋመ ። ከዚያም በኋላ በልዩ ልዩ ስፍ ራዎች በእርሱ አማካይነት ገዳማት ተቋቋሙ ። ብዙ ዎች መነኰሳትም ወደ እነዚህ ቦታዎች ተሰበሰቡ ።

ጳቆሚዩስ ለገዳማት የሚሆን ሕግ አዘጋጅቶአል ። ክርስትናም በኢትዮጵያ ከገባና ገዳማት ከተመሠረቱ በኋላ የጳቆሚዩስ የገዳም ሕግ ለኢትዮጵያም መነኰሳት እንደ መምሪያ ሆነ ።

በቂሣርያ አገር ባስልዮስ የተባለ ዝነኛ የገዳም አለቃ ነበር ። በ፫፻፴ ዓ.ም. ተወልዶ እስከ ፫፻፸፱ ዓ.ም በሕይወት ቆየ ። በትውልድ አገሩ በሶርያ ትልቅ ገዳም አቋቋመ ። በምሥራቅ አገሮች ባስልዮስ የመነኰሳት መሪ ሆነ ። ገዳሙን ካቋቋመ በኋላ ግን ቄስ እንዲ ሆን ተመረጠ ፤ በኋላም በቂሣርያ ከተማ ጳጳስ ሆነ ።

በምዕራብ አገሮች የመነኰሳት መሪ የሆነ በ፬፻፹ ዓ.ም. ገደማ የተወለደው የኑርሲያው በነዲክቱስ የተ ባለው የኢጣሊያ አገር መነኵሴ ነው ። በሮሜ አቅራ ቢያ ሰፊ ገዳም መሥርቶአል ።

ሰው መነኵሴ እንዲሆን ሦስት ነገር እንዲያደ ርግ ተስፋ መስጠት ይኖርበታል ። አንደኛ ፤ ዘወትር በታዛዥነት እንዲኖር ፤ ሁለተኛ ፤ በድህነት እንዲኖር ፤ ሦስተኛ ፤ ሚስት ሳያገባ እንዲኖር ተስፋ ይሰጣል ። ሴት የሆነች እንደሆነ ባል እንዳታገባ ተስፋ ትሰጣለች ።

መነኰሳት የሠሩት ጠቃሚ ሥራ አለ ።

እግዚአብሔርን ለማገልገል ይህን በመሰለ ሕግ ተወስኖ መኖር አስፈላጊ መስሎ ባይታይም እግዚአብ ሔርን በመፍራት የኖሩ መነኰሳት ብዙዎቹ ጠቃሚ ሥራ እንደ ሠሩ የታመነ ነው ። ለምሳሌ እንደ ባሕ ታውያን ሳይሆኑ ብዙዎቹ በሥራ ትጉዎች ነበሩ ። ያል ታረሰውን መሬት በማረስ ፣ ጥቅምም ያላቸውን ልዩ ልዩ ተክሎች በመትከል ፣ ለተቸገሩ ሰዎችም የቸ ርነትን ሥራ በመሥራት ፣ ያልተማሩትንም በማስተ ማር ፣ ቃለ እግዚአብሔርን በመስበክ ፣ ጠቃሚ የሆ ኑትን መጻሕፍት ገልብጠው ለመጪዎች ትውልዶች በማቆየት ይህንንም የመሰለ ሁሉ በመሥራት ለዘ መኑ ሕዝብ ያበረከቱት አገልግሎት ጠቃሚ ሆኖ ተገኘ።

ሆኖም የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት የመነኰሳትን ሳይሆን የሐዋርያት ዘመን ክርስቲያኖችን አብነትና አርዓያ መከተሉ የተሻለ ነው ።

## ጥያቄዎች ።

፩. የጥንት ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት መግለጫዎች ስንት ናቸው?
፪. እነዚህ መግለጫዎች ለምን ተዘጋጁ ?
፫. ለእኛ እንዴት ያለ ጥቅም ይሰጣሉ ?
፬. የጥንት ዘመን ባሕታውያን የተሳሳቱት በምንድር ነው ?
፭. ባለፉት ዘመናት ይኖሩ የነበር መነኰሳት ከባሕ ታውያን የተሻሉ ሆነው የተገኙት በምንድር ነው?

## ምዕራፍ አሥራ አምስት

## የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች ።

በስብከት ፣ በትምህርትም ፣ ምዕመናንን በመምራት ፣ ስለ ክርስትና ሃይማኖት በጻፉት መጻሕፍትም ለጥ ንት ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከቱ ፣ እንደ ሃይማኖት አባቶች የሚቈጠሩ መምህራን አሉ።

ከእነዚህም ቀጥሎ ያሉትን ታሪኮች እንመልከት ።

## ሀ ፣ ኢሬኔዎስ ።

### ስለ ተወለደበት አገር ።

ኢሬኔዎስ በ፻፴ ዓ.ም. ገደማ በትንሽዋ እስያ ውስጥ ተወለደ ። አገሩ የሰምርኔስ ከተማ ነው የሚሉ አሉ ። በወጣትነቱ ጊዜ ለፖሊካርጵ ወዳጁ ነበር ። ፖሊካርጵም በበኩሉ ሐዋርያው ዮሐንስን ያወቀው ፣ ብዙ ጊዜም ከእርሱ ጋር የሚገናኝ ሰው ስለ ሆነ ስለ ኢየሱስ የሰማውን ነገር ለኢሬኔዎስ ሊነግረው ቻለ ።

### የወንጌል ሥራው በጋሊያ አገር ።

የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ጋሊያ ወደ ሚሉት አገር ሄደ ። ይህ አገር በዘመናችን ፈረንሳይ ይባላል ። ለወንጌል ቃል ትልቅ ፍቅር ስለ ነበረው በጥሩ አኳኋን የአገሩን ተወላጆች አስተማረ ። ቋንቋቸ ውንም ተማረ ። ብዙዎች ሰዎችም አምነው ክርስቲ ያኖች ሆኑ ።

ነገር ግን በአገር ውስጥ የክርስቲያኖች ጠላቶች አሉና በ፻፸፯ ዓ.ም.ሊዮን በሚሉት ከተማ ውስጥ ስደት ተጀመረ ። ብዙዎች ክርስቲያኖች መከራ ተቀብለው ስለ እምነታቸው ሞቱ ። በዕድሜ ገፋ ያለ የቤተ ክርስቲያኒቱ ጳጳስም ተይዞ አሰቃቂ በሆነ አኳኋት ሞተ ። እርሱም ከሞተ በኋላ ኢሬኔዎስ የሊዮን ጳጳስ እንዲሆን ተጠራ ።

### የሐሰትን ትምህርት ተቃወመ ።

ከስደት ይልቅ ለቤተ ክርስቲያን አደገኛ ሆኖ የተገኘው ነገር የዘመኑ የስሕተት ትምህርት ነው ። በመ ጽሐፍ ቅዱስ እየተጠቀሙ በተሳሳተ መንገድ ስለ እግዚአብሐር ስለ ክርስቶስም የሚያስተምሩ ሰዎች ነበሩ ። ትምህርታቸው በሐዋርያት ዘመንም የነበረ ግኑሲስ የሚሉት ዓይነት ነው ። ሌላም ከእውነት የራቀ ትምህርት የዘመኑን ክርስቲያኖች ያስቸግራቸው ነበር።

ኢሬኔዎስ ብዙ መጽሐፍ በማዘጋጀት እነዚህ ትምህርቶች ሐሳውያን መሆናቸውን ከመግለጡም

በላይ ትክክለኛውን የክርስቲያንን እምነት ለዘመኑ ሰዎች ያብራራላቸው ነበር ። በዚህም ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛና ነዋሪ የሆነ አገልግሎት አበርክቶአል ።

ስለ ሕይወቱ ፍጻሜ ትክክለኛውን ታሪክ ለማወቅ አልተቻለም ። በ፪፻፪ ዓ.ም. በሰማዕትነት ሞተ የሚል አፈ ታሪክ አለ ።

## ለ ፤ ተርቱሊያኑስ ።

### በትውልድ አገሩ ጠበቃ ሆነ ።

ተርቱሊያኑስ በ፻፶፭ ዓ. ም. ገደማ ካርታጎ በተባለች የሰሜናዊ አፍሪካ ከተማ ተወለደ ። የሞተበት ጊዜ በትክክል ባይታወቅም በ፪፻፴ ዓ. ም. ይሆናል ተብሎ ታስቦአል ።

ከአረመኔ ቤተ ሰብ የተወለደ ነውና ራሱም ሙሉ ሰው እስኪሆን ድረስ አረማዊ ሆኖ ይኖር ነበር ። በወጣትነቱም ጊዜ የብልግናን ሥራ ይሠራ ነበር ።

ጥሩ የትምህርት ተሰጥዎ አለውና በትምህርት ቤት አጥጋቢ ውጤት ያመጣ ነበር ። በዘመኑ ሕዝብ አስተሳሰብ የጥብቅና ሥራ በጣም የተከበረ ነበር ፤ ብዙ ገንዘብም የሚያስገኝ ስለሆነ ተርቱሊያኑስ የተመኘው ጠበቃ ለመሆን ነበር ። እንዳሰበውም ትምህርቱን አጠናቅቆ ጠበቃ ሆነ ።

### ክርስቲያን ሆነ ።

በተወለደበት አገር ፤ በተለይም በካርታጎ አካባቢ ከአረመኔነት ወደ ክርስትና የተመለሱ ሰዎች በርከት ያሉ ናቸው ። ተርቱሊያኑስም ስለ እነርሱ ሰምቶአል ። በአረማዊነቱም ይንቃቸው ነበር ።

በቀን ብዛት ግን ስለ እምነታቸው የበለጠውን ለመረዳት በቃ ። ብዙዎች ክርስቲያኖች ሞትን ሳይፈሩ በዳኛ ፊት በደስታ ስለ ክርስቶስ ሲመሰክሩ ሳይሰማ አልቀረም ። ንቀቱም ወደ ማድነቅ ተለወጠ ። የክርስቲያኖች ነገር ልቡን ማረከው ። በመጨረሻም የእውነት መንገድ እነርሱ ያሉበት ነው ፤ እኔም እንደ እነ

ርሱ ልሁን ብሎ የክርስትናን ትምህርት ተምሮ ክር ስቲያን ሆነ ። በካርታጐም ቤት ክርስቲያን በሽማግሌ ነት ተመረጠ ።

ዝነኛ ሰባኪና ደራሲ ሆነ ።

የተፈጥሮ የንግግር ችሎታ አለውና ጥሩ የእግዚ አብሔር ቃል ሰባኪ ሆነ ። ከዚህም በላይ ከፍተኛ የጽሕፈትም ችሎታ ስለአለው በተማረው ሰፊ ትም ህርት እየተጠቀመ የክርስቲያንን ሃይማኖት የሚያብ ራሩ መጻሕፍትን በብዛት ጽፎአል ። ጠቅላላ ቊጥራቸው ከሠላሳ በላይ ነው ።

በዘመኑ የክርስቲያኖችን ሃይማኖት የሚያንኳስ ሱና የሚነቅፉ ፈላስፎችና ደራሲያን ነበሩ ። ለእነር ርሱ ተቃውሞ መልስ እንዲሆን ተርቱሊያኑስ በክርክር መልክ የሃይማኖቱን እውነተኛነት ለማሳየት መጻሕፍትን ጽፎአል ።

ሰው በተፈጥሮው ተስፋ የሌለው ኃጢአተኛ እንደ መሆኑ መጠን በክርስቶስ መዳን እንደሚያስፈ ልገው ጠለቅ ባለ አኳኋን በመጻሕፍቱ አስረድቶአል። የእግዚአብሔርንም አንድነትና ሦስትነት በማመን ለመጀመሪያ ጊዜ ሥላሴ በሚለው ቃል የተጠቀመ ተርቱሊያኑስ ነው ።

ክርስቲያኖች ፣ አብ ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ በማለት ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን እምነት ይገልጣሉ ። ለሦስቱ አካላት ተርቱሊያኑስ በቋንቋው "ትሪኒታስ" የሚለውን ስም ሰጠ ። ትርጕሙም "ሥላሴ" ነው ።

እርሱ ከጻፋቸው መጻሕፍት ለቤተ ክርስቲያን የተገኘው ጥቅም ከፍ ያለ ነው ።

ስለ ጥምቀትና ስለ ጋብቻ የነበረው አስተያየት ።

ከፍ ብሎ የተጻፈው ነገር ሁሉ ቢታወቅለትም ግን በአንዳንድ ነገር መሳሳቱን ለመካድ አይቻልም ።

ለምሳሌ ሕፃናትን ማጥመቅ ስሕተት ነው ይል ነበር ። በዘመኑ ክርስቲያኖች ሕፃናትን ያስጠምቊአቸው

ነበር ። ተርቱሊያኑስ ግን ፣ ጥምቀት ለአዋቂ እንጂ ለሕፃን አይደለም እያለ ይከራከር ነበር ። ኢየሱስ ፣ ሕፃናትን ተውአቸው ፣ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው ፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና ብሎ የተናገረው ቃል እውነተኛ ትርጉም አልገባውም ነበር ።

እንደዚሁም ምንም ራሱ ሚስት ያገባ ቢሆንም በጋብቻ ላይ ዝቅተኛ ግምት ነበረው ። ለቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሚስት ከማግባት አለማግባቱ ነው የሚሻለው የሚል እምነት ነበረው ። ይህ አስተያየት ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፈ አይደለም ።

የሞንታኒዝም ተከታይ ሆነ ።

ተርቱሊያኑስ በኖረበት ዘመን ብዙዎች ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እየደከሙ መሄድን ጀመሩ ። የቸልተኝነት መንፈስ የተጫናቸው አሉ ። አካሄዳቸውንም ቢመለከቱት በእነርሱና ባላመኑ ሰዎች መካከል ብዙ ልዩነት አይታይም ። በሥራቸው ዓለማውያንን ይመስሉ ነበር ማለት ነው ።

ተርቱሊያኑስ ይህንን ሁኔታ እየተመለከተ ያዝን ነበር ። በመጨረሻም ከትልቅዋ ቤተ ክርስቲያን ተለይቶ ሞንታኒዝም የሚሉት የክርስቲያኖች ማኅበር ተከታይ ሆነ ።

ይህንን ማኅበር ያቋቋመው ሞንታኑስ የተባለ ሰው ነው ። እንቅስቃሴውም በእርሱ ስም ተሰይሞ አል ።

ሞንታኑስ አምኖ ከተጠቀመ በኋላ ፣ ከእግዚአብሔር ራእይ ተገለጠልኝ ብሎ ስብከት ጀመረ ። ብዙ ተከታዮችንም አገኘ ። እነርሱም በሕዝቡ መካከል የሚሰብኩት ስብከት ፣ ክርስቶስ በቶሎ ይመለሳል ፣ ስለዚህ ለመምጣቱ እንዘጋጅ ፣ ከዓለም ፍትወትና ርኵሰት የራቅን እንሁን ፣ ቸልተኝነት ይቅር ፣ በጸሎትና በመልካም ሥራም የበረታን እንሁን የሚል ነበር ።

ከዚህም ሌላ በልሳን ይናገሩ ነበር ። አንዳንድ ጊዜም ከመንፈስ ቅዱስ ያገኙት መስሎአቸው ፣ ትንቢት አለኝ እያሉ ይሰብኩ ነበር ።

## የሞንታኑስ ተከታዮች ስሕተት ።

በዚህ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ብዙዎች ክር ስቲያኖች እንደ ነበሩ የታመነ ነገር ነው ። በዓለም ርኵሰት እንዳይለከፉ ራሳቸውን ይጠብቁ ነበር ። ነገር ግን የተሳሳቱበት ነገር ይኖራል ። ስሕተታቸውም በተ ለይ ሁለት ዓይነት ነው ።

ሀ ፣ ለመንፈሳዊ ስብሰባ በሚሰበሰቡበት ጊዜ በጸሎት አደራረጋቸው ፡ በስብከት አቀራረባቸው ፣ በጠቅላላ በስ ብሰባው አመራር ከመጠን በላይ የምዕመናንን ስሜት ለመቀስቀስ ይጣጣሩ ነበር ። የስብሰባውም ተካፋዮች በስሜት ማዕበል ላይ ተንሳፍፈው ሲገኙ ፣ መንፈስ ቅዱስ ወረደልን ይላሉ ። የስሜት መቀስቀስና የመን ፈስ ሙላት ግን አንድ አይደለም ።

ለ ፣ እግዚአብሔር እስከ አሁን በራእይ ፣ እንዲሁም ትን ቢትን በመስጠት ራሱን ለምዕመናን ይገልጣል የሚል እምነት ነበራቸው ። ስለዚህ ፣ የተገለጠልኝ ትንቢት አለኝ እያሉ ሲናገሩ የሚሉት ነገር በእነርሱ መካከል ልክ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይቈጠር ነበር ። ይህም ሳይበቃቸው ቀርቶ ከእግዚአብሔር ተቀብለናል የሚ ሉትን ቃል ከሐዋርያት ትምህርት የበለጠ አድርገው ይቈጥሩት ነበር ።

ነገር ግን ክርስቲያን በምዕመናን መካከል ተነ ሥቶ የሚናገረው ቃል በምንም ዓይነት በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈው ቃል የበለጠ ወይም የተሻለ ሊሆን አለመ ቻሉ ግልጽ ነው ። ብልጫ ያለው የመጽሐፍ ቃል ነው ።

በሕይወቱ መጨረሻ ላይ ተርቱሊያኑስ የዚህ እንቅ ስቃሴ ተከታይ ሆነ ።

ቤተ ክርስቲያን ግን የሞንታኑስን ተከታዮች አልተቀበለቻቸውም ። ብዙ መከራም ካዩ በኋላ በስድ ስተኛው መቶ ዘመን ውስጥ ጠፉ ።

## ሐ ፣ አምብሮሲዮስ ።

የሚላኖ አገረ ገዢ ሆነ ።

አምብሮሲዩስ በ፫፻፵ ዓ. ም. በኢጣሊያ አገር ተወለደ ። አባቱ በሮሜ መንግሥት የተሾመ የጋሊያ

አገር ገዢ እንደ መሆኑ ከፍተኛ ሹመት ነበረው ። አምብሮሲዩስ ትምህርትን ካጠናቀቀ በኋላ በመንግ ግሥት ተቀጥሮ ሥራ ጀመረ ። በሥራውም የተመሰገነ ሆኖ ስለ ተገኘ ሚላኖ በተባለችው የኢጣሊያ አገር ከተማ የክፍለ አገሩ ገዢ ወይም አስተዳዳሪ እንዲ ሆን ተመረጠ ።

አምብሮሲዩስ ወደ ሚላኖ ከመምጣቱ በፊት የአሪዮስን የሐሰት ትምህርት ተከታይ የሆነ አንድ ጳጳስ በቤተ ክርስቲያን መሪነት ሲሠራ ቆይቶ ነበር ። ይህ ጳጳስ ሞተና አዲስ መምረጥ አስፈላጊ ሆነ ። የቤተ ክርስቲያኒቱ አባሎች ግን በጉዳዩ ተለያይተው ነበር ። ግማሾቹ እንደ ሟችው ጳጳስ የአሪዮስ ተከታዮች ሲሆኑ ሌሎቹ ፣ የአሪዮስ ትምህርት ስሕተት ነው ፣ ይህ ንንም ትምህርት የሚያስተምር በቤተ ክርስቲያናችን ጳጳስ እንዲሆን አንፈልግም በማለት ስለ ተቃወሙ በሚላኖ ቤተ ክርስቲያን የከረረ ጸብ ተፈጠረ ።

ማኅበረ ምዕመናኑ በቤተ ክርስቲያናቸው ተሰ ብስበው በተገኙበት ጊዜ የጳጳሱ የምርጫ ጉዳይ ሁከት እንዳይፈጥር በማለት አምብሮሲዩስ ራሱ የስብሰባው ተካፋይ ለመሆን ወደዚያ ሄደ ። ገዢ ነውና እርሱ ከተ ገኘበት የሚጣሉትን ሰዎች ሊያስታግሣቸው ይችላል እንደ ማለት ነው ።

## አምብሮሲዩስ ጳጳስ ይሁን ።

በስብሰባው መካከል ግን ያልታሰበ ነገር ሆነ ። ጳጳሳችን ማን ይሁን በሚለው ውይይት መካከል በድ ንገት አንድ ትንሽ ልጅ ፣ አምብሮሲዩስ ጳጳስ ይሁን ብሎ ጮኸ ። ከስብሰባው ተካፋዮች መካከል ብዙዎች ባይገልጡትም በልባቸው ያሰቡት ይህ ልጅ የተናገረ ውን ነገር ነው ። ስለዚህ ልጁ ይህንን እንደ ተናገረ ብዙዎቹ ወዲያው መስማማታቸውን በመግለጥ አምብ ሮሲዩስ የሚላኖ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ እንዲሆን ይለምኑት ጀመር ።

እርሱ ግን ፣ በፍጹም አልችልም ፣ ለዚህ ከፍተኛ አገልግሎት እኔ በቂ ሰው አይደለሁም በማለት ብዙ ጊዜ አለመስማማቱን ፣ አለመቻሉንም ነገራቸው ። ሕዝ

ሁም ካህናቱም ግን ልመናቸውን አልተውም ። ሆኖም ለእርሱ የሚሆን ነገር መስሎ አልታየውምና ከተፈለገ በት ነገር ሊያመልጥ ሲል ከከተማ ሸሸ ።

ለጥቂት ጊዜ ጉዳዩን ረጋ ባለ መንፈስ ካሰላሰለ በኋላ ፣ በሕዝቡ በኩል የደረሰኝ ጥሪ ምናልባት የእ ግዚአብሔር ጥሪ ይሆን ይሆናል ብሎ አሰበና ወደ ከተማ ተመልሶ ፈቃደኛ መሆኑን ገለጠላቸው ። ነገር ግን በጣም የቆየ ክርስቲያን አይደለም ። የክርስትናን ሃይማኖት በመማር ላይ ይገኝልና ገና አልተጠመቀም ነበር ። ስለዚህ የተፈለገበትን ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ለመፈጸም እንዲችል ተጠመቀ ፣ ጳጳስም እንዲሆን አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ አስፈላጊው ዝግ ጅት ተደርጎ ለአገልግሎቱ ተመረቀ ።

## ተወዳጅ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኖ ተገኘ ።

እርሱ የተማረው ትምህርት ለቤተ ክርስቲያን ሥራ ሳይሆን ለመንግሥት ሥራ የሚያበቃ ነበር ። ቢሆ ንም በጣም ትጉና መንፈሳዊ የቤተ ክርስቲያን አገል ጋይ ሆኖ ተገኘ ።

በመንግሥት ሥራ ላይ በነበረበት ጊዜ ብዙ ሀብት ነበረው ። የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ከጀመረ በኋላ ግን ፣ ለወንጌል ሠራተኛ ይህን ያህል ሀብት ሊኖረው አይገባም በማለት ብዙ ገንዘብ ለድሆች አካፍሎ ሰጠ። በሚገባም የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝብ ለማስተ ማርና ለመስበክ እንዲችል በትልቅ ትጋት መጽሐፍ ቅዱስን ያጠና ጀመር ። እግዚአብሔርም የንግግር ችሎታ ስለ ሰጠው የሰሚዎችን ልብ የሚስብና የሚያ ረካ ግሩም የሆነ ሰባኪ ለመሆን በቃ ። ስብከቱን ሰም ተው ካመኑት ሰዎች መካከል አንዱ ዝናው በቤተ ክር ስቲያን የታወቀ አውግስጢኖስ የተባለ የቤተ ክርስ ቲያን አባት ነው ።

አምብሮሲዩስ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱ በጣም የተመሰገነና የተወደደ ሰው ሆነ ። ኀዘንተኞችን የሚያጽናና ፣ ለድሆች የሚያስብ ፣ የተቸገሩትን የሚ ረዳ ፣ ምክር ለሚያስፈልጋቸው መምክሩን ያላቋረጠ መንፈሳዊ መሪ ነው ።

አንድ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ስለ እርሱ እንዲህ ብሎአል ፤ ለማኅበረ ምዕመናኑ እረኛ ፤ ለተጨቁኑት ደጋፊ ፤ የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ ፤ የሕዝብ አስተማሪ ፤ እውነትን የተመረኰዘ የነገሥታት አማካሪና ዘላፊ ነበር ። ርስቱን ፤ ወርቁን ፤ ብሩንም ለድሆች በማካፈል አገልግሎቱን ጀመረ ። ለራሱም ምንም ያህል ጥቅም አይፈልግም ነበር ። በየሰንበቱ ስብከት የሚያደርግ ፤ ቢያስፈልግም በሳምንት መካከል ፤ አንዳንድ ጊዜም በቀን ሁለት ጊዜ ቃሉን የሚሰብክ ነበር ። ልዩ በሆነ ጥንቃቄ ለክርስትና ተማሪዎች የሚያስብ ፤ ሊያነጋግረውም የሚፈልግ ሰው ቢኖር ትልቁንም ትንሹንም እኩል አድርጎ ይቀበላል ። ያለ ፍርሃትም የአሪዮስን ኑፋቄ ይቃወም ነበር ።

## በቴዎድርስ ላይ የቤተ ክርስቲያንን ተግሣጽ አደረገ ።

ፍርሃት ያልተሰማው የእግዚአብሔር ቃል ሰባኪ መሆኑን የሚመሰክርለት ብዙ ታሪክ አለ ። ለምሳሌ በ፫፻፺ ዓ.ም. በተሰሎንቄ ከተማ ሕዝቡ በአንድ የጦር አዛዥ ላይ ተነሥቶ ገደለው ። በዚያን ጊዜ የዘመኑ ቄሣር ቴዎዶሲዩስ፤—እንደዚህ ያለ ሥራ የመንግሥትን ክብር የሚነካ ነው በማለት በከተማው ሕዝብ ላይ ለመበቀል ሲል በጨዋታ አደባባይ ውስጥ እንዲሰበሰቡ አደረገና በዚያ ሳሉ ወታደሮች እንዲገድሉአቸው አዘዛቸው ። በብዙ ሺህ የሚቈጠሩትን ወንዶች ሴቶችም ሕፃናትንም እንደ ከብት አርደው ፈጁአቸው ።

አምብሮሲዩስ ይህንን ሁሉ ጥልቅ በሆነ ኀዘን ተመለከተው ። እንደዚህ ያለ ሥራ ተገቢ መስሎ አልታየውም ። ስለዚህ ቄሣር በሕዝብ ፊት ኃጢአቱን አምኖ ንስሐ ካልገባ ወደ ቤተ ክርስቲያን ፤ ወደ ቅዱስ ቍርባንም ሊመጣ አይችልም ብሎ ወሰነበት ።

ቄሣርም ተግሣጹን ተቀብሎ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጣና ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ኃጢአቱን አምኖ ይቅርታ ለመነ ።

ትጉ ወንጌላዊ የመዝሙርም ደራሲ ።

በጠቅላላው አምብሮሲዮስ ለቤተ ክርስቲያን ያበረከተው አገልግሎት ከፍተኛ ነው ። በራሱ ስብከት በሚላኖ ብዙዎች አሕዛብን ወደ እምነት መንገድ መልሶአል ። ቃሉ ወዳልተሰበከበትም አገር የወንጌል መልእክተኞችን መላኩ ተጽፎለታል ። በተለይም ብዙ መዝሙራትን በመጻፍ ፥ በዘመኑም አዲስ የሆነ መንፈሳዊ የመዝሙር ዜማ በማስተማር ማኅበረ ምዕመናንን ደስ በሚያሰኝ አኳኋን አገልግሎአል ።

በ፫፻፺፯ ዓ.ም. በሞት ከዚህ ዓለም በተለየ ጊዜ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆኑ ክርስቲያን ያልሆኑትም ጭምር አለቀሱለት ።

## ጥያቄዎች ።

፩. ኢሬኔዎስ በወጣትነቱ ጊዜ የኢሱስን ታሪክ ከማን ሰማው ?

፪. የእግዚአብሔርን ቃል የሰበከበት አገር የትኛው ነው ?

፫. ተርቱሊያኑስ በዬት አገር ተወለደ ?

፬. ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ምን ይሠራ ነበረ?

፭. እርሱ የጻፋቸው መጻሕፍት ለቤተ ክርስቲያን እንዴት ያለ ጥቅም ሰጡ ?

፮. ተርቱሊያኑስ በሕይወቱ መጨረሻ ላይ ከትልቅዋ ቤተ ክርስቲያን ለምን ተለየ ?

፯. አምብሮሲዩስ በሚላኖ የአገረ ገዢነት ሹመቱን ትቶ ጳጳስ እንዲሆን ያነሣሣው ነገር ምንድር ነው?

፰. አምቢሮሲዩስ ቤተ ክርስቲያንን የጠቀማት ምን ምን በመሥራቱ ነው?

፱. አምብሮሲዩስ ለዘመናችን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መልካም ምሳሌና አርዓያ ሊሆን የሚችለው ስለ ምንድር ነው?

## መ ፣ አውግስጢኖስ ።

### ልጅነቱ ።

ታላላቅ ከሚባሉት ከጥንት ቤተ ክርስቲያን መምህራን አንዱ አውግስጢኖስ ነው ።

ታጋስተ በተባለችው የሰሜን አፍሪካ ከተማ በ፫፻፶፬ ዓ.ም. ተወለደ ። አባቱ ክርስቲያን አልነበረም ። በሕይወቱ መጨረሻ ላይ ግን የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብሎ አምኖአል ። ሞኒካ የተባለችው የአውግስጢኖስ እናት እግዚአብሔርን የምትፈራ ፣ ጥሩ መንፈሳዊት ፣ ልጅዋን በክርስቲያናዊ መንገድ ለመምራት የተጣጣረች ክርስቲያን ነበረች ። ከእርስዋ አውግስጢኖስ በጥሩ አኳኋን የክርስትና ትምህርት ተማረ ።

አውግስጢኖስ ግን በልጅነቱ ጊዜ አልተጠመቀም ። ይኸውም እንዲጠመቅ በቂ እውቀት ቢኖረውም ጥምቀትን ካለመፈለጉ የተነሣ ነው ። የተማረው ትምህርት ልቡን በጣም አልነካውምና በልጅነቱ ክርስቲያን የመሆን ፍላጎት አልነበረውም ። በትምህርት ቤት በነበረበት ጊዜ ዓለማውያን ከሆኑ ጓደኞች ጋር በመተባበር ራሱ ዓለማዊ ሆነ ። እናቱም በጣም አዘነች ።

### ወጣትነቱ ።

አባቱ ግን በልጁ ሳይደሰትና ሳይኰራ አልቀረም ። ምክንያቱም በትምህርት ረገድ ብልጥ ነው ። ተቀባይ ነው ። ስለዚህ በኤለሜንተሪ ትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት አምጥቶ በ፲፯ ዓመት ዕድሜው በከፍተኛ ደረጃ እንዲማር ወደ ካርታጐ ተላከ ። ነገር ግን በመጥፎ ሥራና ልማድ ከተጸመዱ ልጆች ጋር ተቀላቀለና በእነርሱ ብልግና ወደ ውርደት ሥራ ተመራ ። አስጸያፊ በሆነ ሥራ ራሱን አረከሰ ። እናቱ በብዙ ምክርና ጸሎት ልታሳድገው ሞክራ ነበር ። መልካም የሆነ ምክርዋን ሁሉ ግን እርግፍ አድርጎ ጣለና ራሱን ወደ ኃጢአት ረግረግ ወረወረ ።

ከአንዲት ልጃገረድ ጋር ተዋውቆ ወደዳት ። በሕጋዊ መንገድም ሳያገባት እስከ አሥራ ሦስት ዓመት

ድረስ ከእርስዋ ጋር ኖረ ። ልጅም ከእርስዋ ወለደ ። በዚህ ሁሉ መካከል እናቱ ስለ ልጅዋ ሁኔታ እያሰበች በማልቀስ ወደ እግዚአብሔር ትጮኽ ነበር ። ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ እንዲድን ሌሊትና ቀን በጸሎት ትተጋ ነበር ።

## የተደሰተ ቢመስልም ሰላም አልነበረውም ።

አውግስጢኖስ አስተዋይ ተማሪ እንደ መሆኑ መጠን የጠቢባንንና የፈላስፋዎችን መጻሕፍት በትጋት ይመረምር ነበር ። ነገር ግን ከእነዚህ አዋቂዎች ሁሉ የልብን ሰላም ሊያገኝ አልቻለም ። በኃጢአት የሚደሰት ቢመስልም እውነተኛ ደስታ የለውም ። የዘመኑም ክርስቲያን ያልሆኑ ፍልስፍናዎች ሊረዱት አልቻሉም ። የእግዚአብሔርን ቃል ያልተማረና ያላመነ የዚህ ዓለም አዋቂ ሰውን ወደ እውነተኛ ነገር ለመምራት አለመቻሉን በኋላ እስከ መገንዘብ ደረሰ ። ክርስቲያን ከሆነ በኋላ ከጻፋቸው መጻሕፍት በአንዱ ላይ፡–እግዚአብሔር ሆይ ፣ የአንተ እንሆን ዘንድ ፈጠርኸን ፣ በአንተም እረፍት እስኪያገኝ ድረስ ለልባችን ሰላም የለውም ብሎ ጽፎአል ።

## ወደ ሮሜ ሄደ ።

በካርታጐ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ የንግግር አዋቂ ሆኖአልና በዚህች ከተማ የንግግርን ትምህርት ማስተማር ጀመረ ። ስምንት ዓመት ይህን ትምህርት ሲያስተምር ከቆየ በኋላ ግን ወደ ሮሜ እሄዳለሁ ብሎ ወሰነ ። እንዳይሄድ እናቱ ደጋግማ ለመነችው ። ክርስቲያን አይደለምና ወደ ታላቂቱ ወደ ሮሜ ከተማ ቢሄድ የባሰ ነገር ሊደርስበት ይችላል በማለት ልትከለክለው ትፈልግ ነበር ።

እርሱ ግን እሄዳለሁ በማለቱ ሐሳቡን ሳይለውጠው ቀረ ። እናቱም ልታስቀረው አለመቻልዋን ተገንዝባ ፣ እሺ እኔም ከአንተ ጋር ልሂድ አለች ። በመርከብ ወደ ሮሜ ለመጓዝ ተዘጋጅቶ ነበር ። መርከቡም ወዳለበት ወደብ አብረው መጡ ። አውግስጢኖስ ግን እናቱ ከእርሱ ጋር ወደ ሮሜ እንድትሄድ

አይፈልግምና ሴሊቱን በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንድታሳልፍ አባበላት ። ይህን ማድረጉ ሊያታልላት ስለ ፈለገ ነውና ወደ መርከቡ ሳትደርስ እርሱ ለማምለጥ እንዲችል ነበር ።

እንዳሰበም ሆነለት ። ሞኒካ በተባለችው ቤተ ክርስቲያን አደረች ። እርሱም ተለያት ። በማግሥቱ ወደ ወደቡ ብትደርስ ልጅዋን አጣች ። አውግስጢኖስ ወደ ሮሜ ለመድረስ መንገዱን ቀጥሎአል ። እናቱም ወደ ቤትዋ ተመለሰች ። ስለ ልጅዋም ስለ ደኅንነቱም መጸለይዋን ቀጠለች ።

## በሚላኖ የአምብሮሲዩስን ስብከት ይሰማ ጀመር ።

አውግስጢኖስ ግን በሮሜ በመኖርና በመሥራት አልተደሰተም ። ስለዚህ በሚላኖ ከተማ ሥራ ባገኘ ጊዜ ወደዚያ ተዛወረ ። በዚህች ከተማ የአምብሮሲዩስን ዜና ሰምቶ ስብከቱን ለመስማት መሄድ ጀመረ ። ነገር ግን በመጀመሪያ የተደሰተው ጳጳሱ ባቀረበው መልእክት ሳይሆን በአነጋገሩ ለዛና ውበት ነው ። አውግስጢኖስ በንግግሩ ችሎታ ተገረመ ። ይህን በሚያህል በታረመ አነጋገር ለመናገር የሚችል ሰው ልቡን አስደሰተው ።

ነገር ግን መስማቱን ሲቀጥል ሳለ ቀስ በቀስ የንግግሩን ውበት ረስቶ የመልእክቱን ቃል ልብ ማድረግ ጀመረ ። ክርስቲያን አይደለም ። ሰላምም የለውም ። የነፍሱን ራብ ለማስታገሥ ሲል ከብዙ ዓመት ጀምሮ የሚያረካውን ነገር ለማግኘት ተጣጥሮ ነበር ። እስከ አሁን ግን አላገኘም ። አምብሮሲዩስ ምንድር ነው የሚሰብከው ? ምናልባት የእውነት ቃል ይሆን ይሆናል እያለ ያመነታ ጀመር ።

በዚህም መካከል መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ጀመረ ። ቢሆንም ለጊዜው የቃሉ ምሥጢር አልገባ አለው ። ሆኖም በሚገባ የመጽሐፉን ቃል ለማስተዋል ጠለቅ ያለ ምኞት ስላደረበት ከሌሎች ጋር የክርስቲያንን ሃይማኖት አርእስተ ነገሮች ለመማር ለትምህርት ተመዘገበ ። መጽሐፍ ቅዱስንም ማጥናቱን ሲቀጥል ነገሩ ይገባው ጀመረ ። ቢሆንም ሙሉ ብርሃን ገና በነፍሱ አልበራም ነበር ።

## ስለ ነፍሱ ደኅንነት ተጨነቀ ።

ታገለ ። ኃጢአቱ ጕላ ብሎ ስለ ታየው በራሱ ሁኔታ አዘነ ። የእግዚአብሔርም ቍጣ ተሰማው ። በዚህ ዓይነት እየተጨነቀ ሲኖር ሳለ ከዕለታት አንድ ቀን፣ ምን አደርጋለሁ ? ምንስ እሆናለሁ ? ምን ይሻለኛል ? የሚለው ብርቱ ስሜት ልቡን ሞልቶት በአቅራቢያው ወዳለው ወደ አንድ የአትክልት ቦታ ሮጠ፦አምላኬ ሆይ እስከ መቼ ? አቤቱ ፣ እስከ መቼ ትቈጣኛለህ ? የልጅነቴን ኃጢአቶች አታስብብኝ ። እስከ መቼ ? እስከ መቼ ? ነገ ? ወይስ ተነገ ወዲያ ? ዛሬስ ለምን አይሆንም ? አሁን ስለ ምን አይሆንም ? በዚህች ሰዓት ለውርደቴ ፍጻሜ ለምን አይሆንም ? ብሎ እግዚአብሔርን ለመነ ።

## የልጁ መዝሙር ።

በዚያን ጊዜ በአቅራቢያው ካለ ከአንድ ቤት አንድ ትንሽ ልጅ ፣ ውሰድና አንብብ ፣ ውሰድና አንብብ ብሎ ሲዘምር ሰማ ። አውግስጢኖስም መጽሐፍ ቅዱሱን ለማግኘት ፈጠን ብሎ ተነሣ ። መጽሐፉንም ተርትሮ ፣ በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ ፣ በዘፈንና በስካር አይሁን ፣ በዝሙትና በመዳራት አይሁን ፣ በክርክርና በቅናት አይሁን ፣ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት ፣ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ የሚለውን ቃል በሮሜ ፲፫ ፣ ፲፫—፲፬ አነበበ ።

## የደኅንነት ብርሃን በራለት ።

ይህንን ቃል በተመለከተ ቅጽበት የልቡ ጨለማና ጭንቀት ተወገደለት ። ፍጹም ሰላምም ተሰማው ። የኃጢአትን ስርየት እንዳገኘ ለማመን ቻለ ። ወዲያውም ጌታ ኢየሱስን የመከተል ጥልቅ የሆነ ናፍቆት ተሰማው ።

ይህ ከመሆኑ በፊት እናቱ ሞኒካ ከልጅዋ ጋር ለመሆን ወደ ሚላኖ መጥታ ነበር ። አውግስጢኖስም ንስሐ መግባቱንና ወደ ክርስቶስ መምጣቱን በነገራት ጊዜ የተሰማት ደስታ ይህ ነው አይባልም ። ከብዙ ዓመ

ታት ጀምራ ስለ ደኅንነቱ ትጸልይ ነበር ። እግዚአብ ሔርም ጸሎትዋን ስለ ሰማት ምስጋናዋ ከፍ ያለ ሆነ ።

አውግስጢኖስ ንስሐ በገባ ጊዜ ሠላሳ ሦስት ዓመት ሆኖት ነበር ። በተከታዩም ዓመት ከእናቱ ጋር ወደ ሮሜ ለመመለስ ተነሣ ። ከዚያም ወደ ትውልድ አገሩ ወደ አፍሪካ መንገዳቸውን ለመቀጠል ጉዞ ጀመሩ ። ከሮሜ ወጣ ካሉ በኋላ ሞኒካ እንዲህ ብላ ልጅዋን አጫወተችው ።

## ሞኒካ ከመሞትዋ በፊት የተናገረችው ቃል ።

ልጄ ሆይ ፤ ከእንግዲህ ወዲህ በሕይወቴ የሚያ ምረኝ ነገር የለም ። በዓለም ውስጥ ምን እንደምሠራ አላውቅም ። ለምንስ እዚህ እኖራለሁ ? አላውቅም ። በምድር ለማግኘት የተመኘሁት ነገር ሁሉ ተፈጽሞ ልኛል ። በምድር ላይ ለመኖር የሚያስመኝ ምክንያት ነበረኝ ። የተመኘሁትም ከመሞቴ በፊት አንተ ያመነ ክርስቲያን እንድትሆን ለማየት ነበር ። እግዚአብሔር አሁን ከመጠን በላይ ይህን ፈጽሞልኛል ። የእግዚ አብሔር ፈቃድ ሆኖ የዓለምን መንገድ ትተህ የእ ርሱ አገልጋይ ለመሆን መብቃትህን አይቼአለሁ ። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ምን ለመሥራት እዚህ እቆ ያለሁ ?

ሞኒካ ይህንን ቃል ከተናገረች በኋላ ጥቂት ቀን ቆይታ ታመመች ። በአጭር ጊዜ ውስጥ በሽታዋ ስለ ጸናባት ጥቂት ቀን እንደ ቆየች በሞት ከዚህ ዓለም ተለየች ። የልጅዋን መዳን ለማየት በቃች ። የልብዋ ናፍቆት ተፈጸመላት ። ከዚያም በኋላ ከጌታዋ ጋር ለመሆን ወደ ወዲያኛው ዓለም ተሻገረች ።

## በአገሩ ያበረከተው ሰፊ አገልግሎት ።

አውግስጢኖስ እናቱን በመንገድ ላይ ከተለያት በኋላ ወደ አፍሪካ ለመመለስ መንገዱን ቀጠለ ። በዚያም በመጀመሪያ ቄስ ፤ ከዚያም በኋላ ሂፖ በተባለች ከተማ ጳጳስ ሆነ ።

አውግስጢኖስ ለቤተ ክርስቲያን ያበረከተው አገልግሎት ሰፊ ነው ። ዓርባ ዓመት ያህል ለወንጌል መስፋፋት በታማኝነት ሲያገለግል ቆይቶአል ። ለእውነት ቃል የተዋጋ እንደ መሆኑ መጠን የሐሰትን ትምህርት ይቃወም ነበር ።

ለምሳሌ ፣ ከአይርላንድ አገር ጴላጊዩስ የተባለ መነኰሴ ወደ አፍሪካ መጥቶ ፣ ሰው የተወረሰ ኃጢአት የለበትም ፣ በራሱ ኃይል በቅድስና ለመኖር ይችላል እያለ ባስተማረ ጊዜ አውግስጢኖስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ በማቅረብ የመነኰሴው ትምህርት ከእውነት የራቀ መሆኑን ገለጠበት ።

በስብከትና በትምህርት ብቻ ሳይሆን ጠቃሚ የሆኑ ልዩ ልዩ መጻሕፍት በመጻፍ ለቤተ ክርስቲያን ዋጋ ያለው ነገር አውርሶአል ። የአውግስጢኖስ መጻሕፍት እስከ ዛሬ ድረስ የሚጠኑ ናቸው ።

በእግዚአብሔር ጸጋ በረከት የሞላበት አገልግሎቱን እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ቀጠለው ።

ምድራዊ አገልግሎቱም ከተፈጸመ በኋላ በ፬፻፴ ዓ.ም. በሂፖ ከተማ በሞት ከዚህ ዓለም ተለየ ።

ጥያቄዎች ።

፩. የአውግስጢኖስ የወጣትነቱ ጊዜ እንዴት ነበር ?

፪. ወደ ክርስቶስ ተመልሶ እንዲድን እግዚአብሔር የመራበት አመራር እንዴት ነበር ?

፫. እኛ ከአውግስጢኖስ እናት ምን ምን ልንማር እንችላለን ?

ሠ ፣ የሌሎች መምህራን ታሪክ በአጭሩ ።

በጥንት ቤተ ክርስቲያን ዘመን እግዚአብሔርን በቃሉ በማገልገላቸው ሊጠቀሱ የሚገባቸው ሌሎችም መምህራን አሉ ።

## ፩ ኪፕሪያኑስ ።

የካርታጐ ጳጳስ ኪፕሪያኑስ በዘመኑ ስመ ጥሩ የሆነ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነበር ። ስለ ጳጳስ መን ፈሳዊ ሥልጣን የነበረው አስተያየት ግን ትክክለኛ ነው ለማለት አያስደፍርም ። ጳጳስና ቤተ ክርስቲያን አንድ ናቸው ። ጳጳስም ከሌለ ቤተ ክርስቲያንም ልት ኖር አትችልም በማለት ያስተምር ነበር ። ይህ ግን ልክ አይደለም ።

ኪፕሪያኑስ በዚህ ባይደገፍም ግን እስከ መጨ ረሻ ድረስ ያለ ፍርሃት ለክርስትና ሃይማኖቱ ተዋጊ በመሆኑ በምስጋና ልናስታውሰው ይገባናል ።

በ፪፻፶፰ ዓ.ም. በክርስቲያኖች ላይ በደረሰባቸው ስደት መካከል በካርታጐ ከተማ አቅራቢያ እንደ መጥ ምቁ ዮሐንስ ራሱን ተቈርጦ በሰማዕትነት ሞተ ።

## ፪ ፣ የእስክንድሪያው ክሌምናጦስ ።

በሁለተኛው መቶ ዘመን መጨረሻና በሦስተ ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ ዝናው እስከ ብዙ አገር በደረሰ በከፍተኛ ደረጃ መንፈሳዊ ትምህርት በሚሰጥበት ትምህርት ቤት ያስተምር ነበር ። መጽሐፍ ቅዱስን የሚያብራሩ ብዙ መጻሕፍትም ጽፎአል ።

የኖረበት ዘመን ክርስቲያኖች የተሰደዱበት ስለ ሆነ ክሌምናጦስም በእምነቱ ምክንያት መከራ ተቀ ብሎአል ። በ፪፻፪ ዓ. ም. በእስክንድሪያ ከተማ አስ ቃቂ በሆነ ስደት መካከል ከከተማ እንዲሸሽ ተገደደ ። በኋላ በ፪፻፳ ዓ. ም. ቂሣርያ በተባለች ከተማ በሞት ከዚህ ዓለም ተለየ ።

## ፫ ፣ ኦሪጊኔስ ።

ክሌምናጦስ ከሞተ በኋላ ኦሪጊኔስ በእስክንድሪያው ትምህርት ቤት ኀላፊ ሆነ ። መጽሐፍ ቅዱስን ከመጠን በላይ የሚወድ ሰው ስለ ሆነ ሌትና ቀን በብዙ ትጋት ያጠናው ነበር ። በጣም የተማረ ሊቅ ሆነ ። እውቀቱንም ለሰው ለማበርከት ሲል በብዛት መንፈሳዊ መጻሕ

ፍትን ጽፎአል ። እርሱ የጻፋቸው መጻሕፍት ጠቅላላ ቍጥራቸው እስከ ስድስት ሺህ የሚደርስ ይሆናል ይባ ላል ።

ብዙ ዓመት ካስተማረ በኋላ ክርስቲያን በመሆኑ በስደት ጊዜ በጢሮስ ከተማ ታስሮ ወደ ወኅኒ ቤት ተጨመረ ። በእስራቱም ጊዜ ብዙ ሥቃይ ስለ ደረሰ በት ተፈትቶ ከወኅኒ ቤት በወጣ ጊዜ ጤና የሌለው በሽተኛ ይመስል ነበር ።

ከተፈታ በኋላ ብዙ ጊዜ በሕይወት አልቆየም ። በ፪፻፶፬ ዓ. ም. ሞተ ። የተወለደውም በ፩፻፹፭ ዓ. ም. ነው ።

## ፬ ፤ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ።

ዮሐንስ አፈ ወርቅ ወይም ክሪሶስቶሞስ በ፫፻፵፯ ዓ.ም. በአንጾኪያ ከተማ ተወልዶ እስከ ፬፻፯ ዓ.ም. በሕይወት ኖረ ። በመጀመሪያ በአንጾኪያ ፣ ከዚያም በኋላ በቍስጥ ንጥንያ ጳጳስ በመሆን ቤተ ክርስቲያንን አገለገለ ።

ጥሩ መንፈሳዊ መሪና የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂ ከመሆኑም በላይ አስደናቂ የስብከትና የንግግር ስጦታ ስለ ነበረው አፈ ወርቅ የሚለው የቅጽል ስም ወጣለት ። በግሪክ ቋንቋ ዮሐንስ ክሪሶስቶሞስ ተባለ ።

ከዘመኑ ክርስቲያኖች ብዙዎቹ በአካሄዳቸው ከት ክክለኛው መንገድ ርቀው ሲገኙ ተመልክቶ ያለ ፍር ሃት በእግዚአብሔር ቃል ይዘልፋቸው ነበር ። በቤተ መንግሥት ያለው ዓለማዊነት ሳይቀር በእርሱ ስብከት ተወቀሰ።

በዚህ ምክንያት ፣– ዮሐንስ አፈ ወርቅ የሐሰት መምህር ነው ፣ ተሳዳቢ ነው ተብሎ ተከሰሰና ከቍስጥን ጥንያ እንዲሸሽ በጉባዔ ተፈረደበት ። ከከተማ እን ደ ወጣ ግን በማግሥቱ ኃይለኛ የመሬት መንቀጥቀጥ የከተማውን ሕዝብ አሸበረው ። የቤተ መንግሥት ባለቤት ኤቭ ዶክሲያ ፣ ጳጳሱን ስላባረርነው የእግዚአብሔር ፍርድ ይሆ ናል ብላ ዮሐንስ በቶሎ እንዲመለስ ላከችበት ። እር ሱም መጣ ። ቢመጣም ግን ኤቭዶክሲያ ከዓለማዊነት ዋና ከከንቱ ኑሮዋ አልተመለሰችም ።

ለራስዋ ክብር ስትል በከተማ መካከል ከብር የተሠራ የራስዋን ምስል አቆመች ። ምስሉም በተመረቀ ጊዜ የቍስጥንጥንያ ሕዝብ በብዙ ዘፈን ይፈነጥዝ ነበር ። ዮሐንስ አፈ ወርቅም ይህንን ሁሉ አይቶ ተቈጣና አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያን ስብከት ሲያደርግ ፤ ሄሮድያዳ እንደ ገና እየዘፈነች ናት ፤ እንደ ገና የዮሐንስን ራስ ትፈልጋለች ብሎ ጮኸ ።

በዚህም ምክንያት እንደ ገና አባረሩትና በስደተኝነት በአርመን አገር እንዲኖር ተገደደ ።

በዚያ ሳለ ግን ራቅ ባለ ስፍራ ከጥቁር ባሕር አጠገብ ስደተኛ ሆኖ እንዲኖር ተወሰነበት ። ወደዚያም ለመድረስ በእስረኝነት በመንገድ ላይ ሳለ ብዙ ተጕሳቍሎ ወደ ቦታው ሳይደርስ ከድካም የተነሣ በ፬፻፯ ዓ.ም. ሞተ ።

## ፫ ፤ ሂኤሮኒሙስ ።

በመጨረሻ የምንጠቅሰው ሂኤሮኒሙስ ነው ። በ፫፻፵ ዓ.ም. ዳልማቲያ በተባለ አገር ተወለደ ። እርሱም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዝነኛ ሊሆን የቻለው የቋንቋ አዋቂ በመሆኑና መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ላቲን ቋንቋ በመተርጐሙ ነው ። በሮማ መንግሥት የሕዝቡ ግማሽ የሚነጋገሩበትና የሚያውቁት ቋንቋ ስለ ሆነ ሂኤሮኒሙስ ይህንን ትርጕም በማዘጋጀቱ ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አገልግሎት ሰጥቶአል ።

ብዙ ዓመት በቤተ ልሔም በባሕታዊነት ከኖረ በኋላ በ፬፻፳ና ዓ.ም ሞተ ።

## ጥያቄዎች ።

፩. ጳጳስና ቤተ ክርስቲያን አንድ ናቸው ። ጳጳስም ከሌለ ቤተ ክርስቲያንም ልትኖር አትችልም ብሎ የተናገረው ማን ነው?

፪. እንዲህ ማለቱ ትክክለኛ ነው ወይስ ሐሰት ?

፫. ኦሪጌኔስን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከሌላ ነገር ሁሉ ይልቅ ስሙን የሚያስጠራው ምንድር ነው?

፬· የቍስጥንጥንያው ጳጳስ አፈ ወርቅ ተብሎ የተሰ የመው በምን ምክንያት ነው?

፭· የዘመናችን ሰባኪዎች ከዮሐንስ አፈ ወርቅ ምን ምን ሊማሩ ይችላሉ?

፮· ሂኤሮኒሙስ ምን በመሥራቱ ቤተ ክርስቲያንን ጠቀማት ?

## ምዕራፍ አሥራ ስድስት ።

## መደምደሚያ ።

### ሀ፣ የክርስትና ሃይማኖት መስፋፋት ።

ክርስቶስ በምድር ላይ ከተመላለሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ፭፻ ዓ.ም. ገደማ በጥንታዊው ዓለም ውስጥ የሆ ነው የወንጌል መስፋፋት አስደናቂ የሆነ ታሪክ ያለበት ነው ። ጌታ ኢየሱስ በምሳሌ የተናገረውን ቃል ሊያስታውሰን ይችላል ። የእግዚአብሔር መንግሥት በሰናፍጭ ቅንጣት ትመሰላለች ። በምድር በተዘራች ጊዜ በምድር ካለ ዘር ሁሉ ታንሳለች ፤ በኋላ ግን ትወ ጣለች ፤ ከአትክልትም ሁሉ የምትበልጥ ትሆናለች ፣ የሰማይ ወፎችም በጥላዋ ሊሰፍሩ እስኪችሉ ታላላቅ ቅርንጫፎች ታደርጋለች ብሎ አስተምሮናል ። ማር. ፬፣ ፴—፴፪ ።

እውነት ነው ፣ የወንጌል ዘር ቅንጣት በመጀመሪያ በአይሁድ አገር በተዘራች ጊዜ በጣም አነስተኛ ነበ ረች ። የወንጌል መስፋፋት በትንሹ ነው የተጀመረው። በመጀመሪያ ቃሉን ሰምተው ያመኑበት ጥቂቶች ናቸው።

በኋላ ግን የእግዚአብሔር ቃል ጥሩ ዘር ከመሆኑ የተነሣ በብዙዎች ሰዎች ልብ ውስጥ ሥር ሰድዶ ፍሬ ማፍራት ጀመረ ። አስገራሚ በሆነ ቅልጥፍናም የደ ኅንነት መልእክት ከአገር ወደ አገር ፣ ከሕዝብ ወደ ሕዝብ እየተስፋፋ ሄደ ።

በጥንታዊው ዓለም በሰሜን በኩል እስከ መካከለኛው አውሮጳ ፣ በምዕራብ እስከ አይርላንድ እስከ እንግሊዝ አገር ፣ በምሥራቅ እስከ ፋርስና እስከ ሕንድ አገር ፣ በደቡብም እስከ ዓረብና እስከ ኢትዮጵያ ድረስ የወንጌል መልእክተኞች ደርሰው የክርስቶስን ቃል አሠራጭተው ነበር ።

ጌታ በምሳሌ እንደ ተናገረው ያች ትንሽ ቅንጣት ትልቅ ዛፍ ሆነች ። የእግዚአብሔር ቃል በተስፋፋበት መጠን ደግሞ በየአገሩ ደስ የሚያሰኝ ብዙ ለውጥና መሻሻል ታየ ። የኅብረተ ሰብ ኑሮ በጥሩ አኳኋን ተለወጠ ። የክርስቲያን ቤት በሰላምና በንጽሕና የተጠበቀ በመሆኑ ስለ ክርስትና ሃይማኖት ኃይልና በረከት በመልካም ይመሰክር ነበር ። ክርስቲያኖችም የእግዚአብሔርን ቃል መመሪያ በማድረግ የታመሙትን በመጐብኘት ፣ የታረዙትን በማልበስ ፣ የተራቡትን በመመገብ ፣ ለታሰሩትም የቸርነትን እርዳታ በማድረግ ይህንንም በመሳሰለ ሁሉ እምነታቸውን በተግባር ሲተረጉሙ በቃል ብቻ ሳይሆን በሥራም ቤተ ክርስቲያንን ያስፋፉ ነበር ።

ለ፣ የቤተ ክርስቲያን መደራጀትና የጳጳሳት ሥልጣን።

በየአገሩ ተቋቁመው የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት በዘመን ብዛት በጳጳሳት የሚመሩ ሆኑ ። ይህ ሁኔታ ግን በቤተ ክርስቲያን ላይ መንፈሳዊ ጉዳት አመጣ ። የጳጳሱ ሥልጣን እያደገ በሄደበት መጠን የቦታው ቄስ ወይም ሽማግሌ ፣ ወይም ደግሞ የማኅበረ ምዕመናኑ መንፈሳዊ አገልግሎት እየመነመነና እየደከመ ሄደ ።

በሐዋርያት ዘመን የነበረው ጥሩ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ታፍኖ ሞተ ። ጳጳሱ ትልቅ ሹም መስሎ በሥልጣኑ ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት ነገር ሁሉ ውሳኔ የሚሰጥ ስለ ሆነ ለምዕመናን የጥሪ አገልግሎት የማይሰጣቸው ሆኑና መንፈሳዊ ሕይወት መዳከሙ ተከትሎ መጣ ።

በዘመን ብዛት ደግሞ በጳጳሳት መካከል የሥልጣን ሽሚያና ውድድር ሳይፈጠር አልቀረም ። በተለ

ይም የሮማ ከተማ ጳጳስ በማቴዎስ ወንጌል በምዕ ራፍ ፲፮ ቍጥር ፲፰ ላይ ጌታ ኢየሱስ ለጴጥሮስ የተና ገረውን ቃል በመተርጐም ፣ በሮማ ያለው ጳጳስ ከሁ ሁሉም በላይ መሆን አለበት ፣ የሮማ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ጳጳስ ጴጥሮስ ነበር ፤ እኔም የእርሱ ተከ ታይ ስለ ሆንሁ በጌታ ፈቃድ የሁሉም አለቃና መሪ መሆን ይገባኛል እያለ ይከራከር ነበር ።

የምዕራብ አገሮች አብያተ ክርስቲያናት የበላይ ነቱን ተቀብለው በማርቲን ሉተር ዘመን ቤተ ክርስ ቲያን እስከ ታደሰችበት ጊዜ ድረስ በሮማ ጳጳስ ሥል ጣን ሥር ይተዳደሩ ነበር ። ሉተር የነገሩን ስሕተት ተገንዝቦ ተቃወመው ። እውነትም ፣ ጌታ ኢየሱስ ለጴ ጥሮስ የተናገረው ቃል እርሱን ብቻ የሚመለከት ቃል አይደለም ። ሌሎችንም ሐዋርያት ጭምር ይመለከታል ። የሐ. ፰ ፣ ፳፫ ይመልከቱ ። ከሐዋርያትም አልፎ ማኅበረ ምዕመናንን ይመለከታል። ማቴ. ፲፰፣ ፲፭—፳ ይመልከቱ

## ሐ ፣ ክርስትና በሮማ የመንግሥት ሃይማኖት ሆኑ ያመጣው ጥቅምና ጉዳት ።

ከዚህ በፊት እንደ ሰማነው ቆስጠንጢኖስ ቄሣር በሆነበት ጊዜ ክርስትና በመንግሥት የተደገፈ ሃይማ ኖት ሆነ ። በአንድ በኩል ስንመለከተው ይህ ሁኔታ የክርስቲያኖችን እምነት በበለጠ የሚያስፋፋ ሆኖ ተገኘ ። አረመኔነትም እየጠፋ ሄደ ።

በሌላ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ግን የመን ግሥት ድጋፍ በቤተ ክርስቲያን ለመንፈሳዊ ግድ የለሽ ነትና ቸልተኝነት ምክንያት ሆነ ።

ክርስቲያን መሆን ቀላል ነገር ሆነና ብዙዎች ሰዎች ከልብ ሳይሆን እንዲያው መንግሥት የሚወድደውን ሃይማኖት መከተል ይሻላል በማለት ብቻ ለስም የክ ርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ሆኑ ። በዚህም ምክንያት በክርስቲያኖች መካከል ዓለማዊነት እየበዛ ሲሄድ ታየ ።

ከዚህም ሌላ ብዙዎች የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች በማይገባ በመንግሥት ድጋፍ እየተጠቀሙ አብ

ያተ ክርስቲያናትን በመንፈሳዊ መንገድ ሳይሆን በኃ ይልና በሥጋዊነት ይገዙአቸው ነበር ።

መ ፣ የሮሜ መንግሥት ስለ መውደቁ ።

አምስተኛው መቶ ዘመን በጥንታዊው ዓለም ላይ ትልቅ ለውጥ አመጣበት ። ይኸውም የሮሜ መን ግሥት በመውደቁ ነው ። ከብዙ መቶ ዓመታት ጀምሮ በዓለም ሕዝቦች መካከል የመጀመሪያው ማዕረግና ስፍራ ስትይዝ የቆየችው ገናናይቱ መንግሥት ከሰ ሜን በመጡ ባልሠለጠኑ ሕዝቦች ተወርራ ወደቀች ። በክብርና በሥልጣን ተወዳዳሪ ያልነበራት የጥንታዊው ዓለም ንግሥት ሮሜ ተዋረደች ፣ ደከመች ። በመጀመ ሪያ በ፬፻፲ ፣ እንደገናም በ፬፻፸፮ ዓ.ም በጠላት እጅ በመ ግባትዋ ፍጻሜዋ ደረሰ ። በልዩ ልዩ መንግሥታትም ተከፋፍላ ቀረች ።

ይህ መለዋወጥ ሁሉ በዘመኑ ሕዝብ ላይ ብዙ ችግር አስከተለበት ። ጦርነት ስለ በዛ ፣ የመንግሥትም ሁኔታ የማያስተማምን ሆኖ ስለ ተገኘ ፣ ብዙዎች ሰዎች ምን ይሻለናል ? ወዴትስ ለመሄድ እንችላለን ? እያ ሲጨነቁ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይጠጉ ነበር ። መን ሥት ቢፈርስም ቤተ ክርስቲያን አልፈረሰችም ። በዘመ ኑም የተቸገሩትን ፣ የተራቡትንና የታመሙትን ለመር ዳት እጅዋን የዘረጋች ቤተ ክርስቲያን ናት ። ብዙ ዎቹ በተስፋ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመለከቱ የነበር በዚህ ምክንያት ነው ።

ሠ ፣ እነሆ ፣ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእ ናንተ ጋር ነኝ ።

ማቴ. ፳፰ ፣ ፳ ።

በደረሰባት ሁሉ መካከል ቤተ ክርስቲያን ለምን አልጠፋችም? አረማውያን የሆኑ ባለ ሥልጣኖች ሊደ መስሱአት ሞከሩ ። አልሆነላቸውም ። ሐሳውያን መም ህራን ከትምህርት መሠረትዋ ሊያናጉአትና ሊያፈር ሱአት ተነሡ ። አልቻሉም ። ግን አንዳንድ ጊዜ በመሪ ዎችዋ መንፈሳዊ ጉድለት ምክንያት ፣ ወይም ደግሞ

በምዕመናን መስልቸትና ዓለማዊነት ምክንያት የሚያ ሠጋ ሁኔታ ተፈጠረባት ። ቤተ ክርስቲያን ግን አል ጠፋችም ።

ስለምን ?

እነሆ ፣ እስከ ዓለም ፍጻሜ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ የሚለው የኢየሱስ ቃል መልስ ሊሆን ይችላል። በብዙ ፈተናና መከራ መካከል ቤተ ክርስቲያን እንዳትጠፋ የጠበቃት እርሱ ነው ።

ወደ ፊትም እንደማትጠፋ ኢየሱስ ራሱ ቃል ገብቶላታል ።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ናት ። ለጊዜው ብት ጨነቅም በወዲያኛው ዓለም የማያልፈው ክብር በላ ይዋ ላይ እስኪገለጥ ድረስ ኃያል በሆነ ክንዱ እየመ ራና እየደገፈ ይጠብቃታል ።

ክርስቲያን ይህንን ያምናል ። ስለዚህ በተስፋ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እየተመለከተ ፣ በእርሱ ፣ በወደደን እናሸንፋለን እያለ ወደ ላይኛው አገር እስኪደርስ ድረስ በደስታ እግረ መንገዱን ይቀጥላል ። ሮሜ ፰፣ ፴፯ ።